# አማርኛ

እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ

# የመምህር መምሪያ መጽሐፍ

## 8ኛ ክፍል


**ፀሀፊዎች**

መላኩ ጽጌ

ትጃኒ ምትኩ

**አርታኢ**

ግሩም ጥበቡ

ከበደ በቀለ

**የጥራት ተቆጣጣሪዎች**

ይልፋሸዋ ጥላሁን

በርናባስ ደበሎ

ታምሩ ገለታ

**ግራፊክስ**

ሰለሞን ዓለማየሁ ጉተማ

# ማውጫ


ምዕራፍ አንድ ........ 1
የስራ ላይ ስነምግባር ........ 1
ምዕራፍ ሁለት ........ 15
ባህላዊ ቅርስ ........ 15
ምዕራፍ ሶስት ........ 31
ሰብአዊ እሴቶች ........ 31
ምዕራፍ  አራት ........ 47
አፄ ቴዎድሮስ ........ 47
ምዕራፍ አምስት ........ 65
የህዝብ ብዛት ........ 65
ምዕራፍ ስድስት ........ 84
በረሃማነት ........ 84
ምዕራፍ ሰባት ........ 95
የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ ........ 95
ምዕራፍ ስምንት ........ 105
ሰላም ........ 105
ምዕራፍ  ዘጠኝ ........ 117
የአየር ንብረት ........ 117
ምዕራፍ አስር ........ 128
ተውኔት ........ 128

# መግቢያ

ትምህርት ሚኒስቴር "ጥራቱ የተጠበቀና እኩል ተደራሽነት ያለው ትምህርት ለሁሉም ማዳረስ" በሚል አዲስ ስርዓተ ትምህርት ቀርጾ አቅርቧል። በዚህ ስርዓተ ትምህርት ውስጥም ከዚህ ቀደም የነበረውን ክፍተት ለመሙላት ያመች ዘንድ ምርምሮችን በማድረግ አዳዲስ ይዘቶችና አተገባበሮችን ስራ ላይ ለማዋል ተሞክሯል። በዚህም የአፍ መፍቻ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት መሳሪያ የሆኑት የይዘት ፍሰት፣ አነስተኛ የመማር ብቃትና መርሀትምህርት በአገሪቱ ስርዓተ ትምህርት ማእቀፍ ውስጥ ተመስርተው እንዲሰናዱ ተደርገዋል። እነዚህ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት መሳሪያዎች ዋና መነሻቸው የአፍመፍቻ ቋንቋ ልህቀትን ለማሻሻል ሲሆን በአውድ የተደገፈ፣ በህጻናት እድገት ላይ በተደረገው የምርምር ማስረጃና በመማር ላይ የተመሰረተ ትምህርታዊ ስኬታማነትን እንዲያረጋግጡ ተደርገው ተቀርጸዋል። በአውዱ የተሰጡት መነሻ ልምምዶችም የተማሪውን መማር የመጨረሻ ግብ የሚያሳኩ ናቸው ተብሎ ይታሰባል። የስርዓተ ትምህርት መሳሪያዎች በዋናነት እንዲቀረጹ የተደረጉት የመማር ውጤት፣ ብቃት፣ ይዘት፣ የመማር ስልቶች፣ ምዘናና ለእያንዳንዱ ይዘት ጊዜ በመስጠት ነው።

ይህ መጽሀፍ አስር ምዕራፎች ያሉት ሲሆን ለእያንዳንዱ ምእራፍ መተግበሪያነትም በአጠቃላይ የተሰጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት ያለ ሲሆን በየምእራፉ ላሉ ክፍለ ጊዜያትም ተከፋፍሎ ቀርቧል። እያንዳንዱ ምእራፍ በስድስት አበይት የቋንቋ የትምህርት ይዘቶች እንዲዋቀርም ተደርጓል። የትምህርት ይዘቶቹም ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብ፣ መጻፍ፣ ቃላት እና ሰዋሰው ናቸው። በእነዚህ የትምህርት ይዘቶች ስርም የተለያዩ ንዑሳን የትምህርት ይዘቶችም ተካትተዋል። በማዳመጥ ስር ለማዳመጥ ክሂል ማጎልበቻ በምንባብነት የተዘጋጁ የተለያዩ ጽሁፎች ቀርበዋል። ለማዳመጥ ትምህርት የተመረጡ ጽሁፎቹን ለተማሪዎች በማንበብ የቅድመ ማዳመጥ፣ የማዳመጥ ጊዜና አዳምጦ መረዳት መልመጃዎችና ተግባራት እንዲሰሩ ቀርበዋል። በመናገር የትምህርት ይዘት ተማሪዎች የመናገር ክሂላቸውን እንዲያጎለብቱ የሚረዱ የተለያዩ ተግባራት ቀርበዋል። በአንብቦ መረዳት የትምህርት ይዘት ስር ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ክሂላቸው እንዲጎለብት ያስችላሉ ተብለው የታሰቡት ቅድመ ንባብ፣ የንባብ ጊዜና የአንብቦ መረዳት መልመጃዎችና ተግባራት ተሰናድተዋል። በመጻፍ የትምህርት ይዘት ስርም እንዲሁ ተማሪዎች የመጻፍ ክሂላቸውን ያዳብሩባቸዋል ተብለው የታለሙ የተለያዩ ንዑሳን ይዘቶች፣ መልመጃዎችና ተግባራት ተሰናድተዋል። በቃላት የትምህርት ይዘት ስር

ተማሪዎች የቃላት እውቀታቸው እንዲያድግ ያስችላሉ ተብለው የታሰቡ የተለያዩ ንዑሳን የትምህርት ይዘቶች፣ መልመጃዎችና ተግባራት ቀርበዋል። በመጨረሻ የቀረበው የትምህርት ይዘትም ሰዋሰው ሲሆን በዚህ የትምህርት ይዘት ስር የተተኳሪውን ቋንቋ መዋቅር ለማስገንዘብ የሚረዱ ንዑሳን የትምህርት ይዘቶች፣ መልመጃዎችና ተግባራት ተካትተዋል።

በአጠቃላይ መጽሀፉ ተማሪዎች በእያንዳንዱ ምእራፍ ስር የቀረቡ አነስተኛ የመማር ብቃቶችን ከግብ ያደርሳሉ ተብለው የታሰቡ የትምህርት ይዘቶችን እንዲማሩ በተለያዩ የማስተማር ስልቶች፣ ዘዴዎችና ምዘናዎች ተደግፎ ቀርቧል። ተማሪዎችም የታለሙትን አነስተኛ የመማር ብቃቶች እንዲጎናጸፉ በግል፣ በጥንድ፣ በቡድንና እንደ ክፍል በጋራ በመቀናጀት እንዲማሩ የሚበረታቱ ይሆናል።

# ምዕራፍ አንድ

# የስራ ላይ ስነምግባር

(የክፍለጊዜ ብዛት 9)

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- በጥሞና አዳምጠው ምላሽ ይሰጣሉ፤
- የእንግዳ አቀባበል ስርዓትን በሚና ጨዋታ ያንጸባርቃሉ፤
- አንብበው የስራ ላይ ስነምግባር ጽንሰሀሳብን ያብራራሉ፤
- አዳዲስ ሀሳቦችን በማሰስ አንቀጽ ይጽፋሉ፤
- የጽሁፍን አጠቃላይ ሀሳብ ለማግኘት ያነባሉ፤
- በተለያዩ አውዶች ውስጥ ተዘውታሪ ቃላትን ይጠቀማሉ፤
- አዳዲስ ሀሳቦችን በማካተት አንቀጽ ይጽፋሉ፤
- የአረፍተነገር መዋቅሮችን ለይተው ይጠቀማሉ።

## 2. የትምህርት ይዘት

### 2.1 ማዳመጥ

- የሚነበበውን ጽሁፍ ማዳመጥ
- የተጓደሉትን ሀሳቦች ማሟላት
- ሰዎች መከባበርን በመካከላቸው እንዴት እንደሚፈጥሩ ማዳመጥ

### 2.2 መናገር

- የመከባበር መገለጫዎችን መናገር
- የሰው ልጆች እንዴት እንደሚከባበሩ መናገር

### 2.3 ማንበብ

- የስራ ላይ ስነምግባር የሚለውን ምንባብ ማንበብ
- የየአንቀጾችን መልዕክት ለማግኘት ማንበብ
- የቃላትን አውዳዊ ፍች ለማግኘት ማንበብ

## 2.4 ቃላት

- ተዘውታሪ ቃላትን በአውድ ውስጥ መጠቀም

## 2.5 መጻፍ

- የቋንቋውን ስርዓት ተከትሎ አንቀጽ መጻፍ
- በሰንጠረዥ ውስጥ የቀረበላቸውን ሀሳቦች መነሻ አድርገው ድርሰት መጻፍ
- በትምህርት ቤታቸው የሚተገበሩ የሥራ ስነምግባሮች ላይ መሰረት አድርገው ድርሰት መጻፍ

## 2.6 ሰዋስው

- በአረፍተ ነገር ውስጥ ባለቤትና ማሰሪያ አንቀጽ መለየት
- ባለቤትና ማሰሪያ አንቀጽ ያላቸውን አረፍተ ነገሮች መመስረት

# 3. የማስተማሪያ ዘዴ

- የተለያዩ የማዳመጥ ትምህርት ክንውኖችን ተግባር ላይ በማዋል ትምህርቱን ማቅረብ
- የአንብቦ መረዳት ማስተማሪያ ስልቶችን በመጠቀም የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ማበረታታት
- ቀስቃሽ ጥያቄዎችን በማቅረብ እንዲወያዩ ማድረግ
- ምሳሌ አቅርቦ ተዘውታሪ ቃላትን በአውድ ውስጥ እንዲጠቀሙ መቀስቀስ
- ተዘበራርቀው የቀረቡትን ዓረፍተነገሮችን ምሳሌ በመስጠት ቅደምተከተላቸውን አስተካክለው አንቀጽ እንዲጽፉ ማገዝ
- የቋንቋውን ስርዓት ተከትለው አንቀጽ እንዲጽፉ፣ በሰንጠረዥ ውስጥ የቀረበላቸውን ሀሳቦች መነሻ አድርገው መግቢያ፣ ዋና አካልና ማጠቃለያ ያለው ድርሰት እንዲጽፉ ማትጋት
- ስለአንቀጽ ምንነትና ምሳሌ በማቅረብ በትምህርት ቤታቸው የሚተገበሩ የሥራ ስነምግባሮች ላይ መሰረት አድርገው አንቀጽ እንዲጽፉ ማገዝ
- ጠቃሚና ትርጉም ያለው ግረ መልስ መስጠት
- ምሳሌ በማቅረብ በአረፍተነገር ውስጥ ያሉ ባለቤቶችንና ማሰሪያ አንቀጾችን እንዲለዩ ማድረግ

- ሰዋስዋዊ ትክክለኛነትን ጠብቀው መጻፋቸውን ማረጋገጥ

ክፍለጊዜ አንድ

# ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-

- በጥሞና አዳምጠው ምላሽ ይሰጣሉ።

## ቅድመ ማዳመጥ

በትምህርት አንድ ስር የተማሪዎችን የማዳመጥ ተነሳሽነት የሚጨምሩና የቀረበውን ይዘት ከቀደመ ዕውቀታቸው ጋር እንዲያዛምዱ የሚረዱ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል። እባክዎ መምህር ተማሪዎቹ እነዚህን ጥያቄዎች እንዲመልሱ ያበረታቷቸው። በመቀጠልም ወደ ዋናው የማዳመጥ ተግባር ይሸጋገሩ። በመጀመሪያ የቀረበውን ምንባብ ሁለት ጊዜ በተለያየ ፍጥነት ያንብቡላቸው። በመጀመሪያው ንባብ አጠቃላይ ሀሳብ ላይ በሁለተኛው ንባብ ዝርዝር ሀሳቦች ላይ ትኩረት ሰጥተው እንዲያዳምጡ ይንገሯቸው።

## መከባበር

የሰው ልጅ ከእንስሳት የተለየ ባህሪና የማሰብ ችሎታ አለው። **መብትና ግዴታውን** ያውቃል። መብቱ እንዲከበርለት ግዴታውን መወጣት እንዳለበትም ይገነዘባል። መከበር ከራስ እንደሚጀምር ከማወቅም በላይ **ለመከበር ሌላውን ሰው ማክበር** እንደሚገባውም ይረዳል። ሌላውን ሰው ማክበር በተለያየ መልኩ ሊገለጽ የሚችል ሲሆን ለምሳሌ ሀሳብን፣ አመለካከትን፣ የተለያዩ ውሳኔዎቹን ወዘተ አወንታዊ በሆነ መልኩ መቀበልን ይመለከታል። የሌሎች ሀሳብ፣ አመለካከትና ውሳኔ ከእኛ ሀሳብ፣ አመለካከትና ውሳኔ ጋር ባይመሳሰል እንኳ የሃሳቡን ባለቤቶችና ሀሳቦቻቸውን ማክበር ግድ ይለናል። ሀሳብን በሀሳብ ማሸነፍ በማህበራዊ መስተጋብር ውስጥ ተቀባይነት ያለው አካሄድ ቢሆንም አልሸነፍም ያለ ሀሳብን ደግሞ በልዩነት ተቀብሎ መሄድ የስልጣኔ አንዱ መገለጫ ነው። ከዚህ ባለፈ አታካሮና ከፍ ሲልም አካላዊ ግጭት ውስጥ መግባቱ በኋላ ላይ ትርፉ ከማንወጣበት ፀፀት ውስጥ መዘፈቅና በዚህም የተነሳ የማህበራዊ የግንኙነት መስመራችንን ማበላሸትም ይሆናል።

ለምሳሌ: በገጠሩ የሀገራችን አካባቢ ሰዎች ተፈጥሮ ሀብትን በመጠቀም ክንውን ወቅት በስፋት ይገናኛሉ። ይህ ግንኙነታቸውም በአግባቡና በመመካከር ካልተመራ ለእርስበርስ

አለመተማመንና ለግጭት ይዳርጋል። ለምሳሌ: በግጦሽ መሬት፣ በእርሻ ቦታዎች እንዲሁም ምንጮችና ኩሬዎች አካባቢ በጋራ ተከባብሮ መጠቀም የግድ የሚል ይሆናል። በእነዚህና በመሳሰሉት የጋራ መጠቀሚያ አካባቢዎች ግጭቶች ቢፈጠሩም በመደማመጥና **የጋራ የሆነ የመፍትሄ ሀሳብ** በማስቀመጥ ችግሮችን ማስወገድ ያሻል። አብሮ በመኖር ማህበራዊ ህይወትን በጤናማ አካሄድ ለመምራት መመካከር፣ መወያየት፣ የጋራ ግንዛቤን መፍጠርና መተግበርን ይጠይቃል።

## የማዳመጥ ጊዜ

***እባክዎ መምህር እዚህ ጋ ማንበብዎን ገታ አድርገው የሚከተሉትን የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች ተማሪዎችዎን ይጠይቋቸውና መልስ ከተቀበሉ በኋላ የማዳመጥ ተግባራቸውን እንዲቀጥሉ ያሳስቧቸው።***

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. የሰው ልጅ _______ እና _______ ያውቃል።
2. የሰው ልጅ ለመከበር _______ ማክበር አለበት።
3. ግጭቶች እንዳይፈጠሩ ለማድረግ _______ እና የጋራ የሆነ _______ ማስቀመጥ ያሻል።
4. መከባበር ከ _______ ይጀምራል።

መከባበር ከግለሰብ ይጀምራል። ሰው መብቱ እንዲነካ አይፈልግም። ማግኘት የሚገባውን ጥቅም አሳልፎ አይሰጥም። ድንበሩ ሲደፈር በዝምታ አይመለከትም። መብቱ ሲነካበትም በቸልታ አያልፍም። ያልጠበቀው ጥቃት ሲደርስበትም የአቅሙን ያህል ጥቃቱን ለመከላከል ይውተረተራል። ጥቃትን ከመከላከያ መንገዶች አንዱ የፍትህ አውዱን መጠቀም ነው። አንድ ሰው የደረሰበትን ጥቃት ለማመልከት ባህላዊን (ሽምግልና) ወይም ዘመናዊ (ፍርድቤት) አካሄድን ሊከተል ይችላል። ፍትህንም ተቀባይነት ባለው መንገድ ያገኛል። ከዚህ ውጪ በራስ ፍትህ ለማስፈን የሚደረግ ሌላ የበቀል ጥቃትን አይቀበልም። እንደዚህ አይነቱ ሰው የህግን ልዕልና የተረዳ ነው። በመሆኑም የሌላውን መብት ያከብራል። የሌሎች ጥቅሞችንም አይጋፋም። የሌላውን ድንበር ሊገፋ አይሞክርም። ጠብ አያጭርም። የመከባበርን ዋጋ ለይቶ ያውቃልና አክብሮ ይከበራል።

(ምንጭ፡ አማርኛን እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ ለማስተማር ከተዘጋጀ ከቀድሞ የ8ኛ ክፍል የተማሪ መጽሀፍ ተሻሽሎ የተወሰደ)

መምህር ምንባቡን ደግመው በማንበብ ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎቹ መልመጃ አንድን በአዳመጡት መሰረት የድህረ ምንባብ ጥያቄዎቹን እንዲመልሱ ያበረታቷቸው።

**ክፍለጊዜ ሁለት**

**ማሳሰቢያ፡ መምህር እባክዎ በተለመደው አካሄድ መሰረት፡-**

**1ኛ. ሁሉም ክፍለጊዜዎች የመግቢያ (ማስተዋወቂያ)፣ የአቅርቦትና የመደምደሚያ(ክለሳ) ክፍል ያላቸው መሆኑን እና**

**2ኛ. በሁሉም ክፍለጊዜዎች ጅማሮ ወቅት ያለፈውን ክፍለጊዜ ትምህርት ማስታወስና የክለሳ ጥያቄዎች ወይም ነጥቦች ማቅረብ የማይታለፍ መሆኑን አይዘንጉ::**

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡**

- እንዴት እንደሚከባበሩ ይናገራሉ።

በዚህ ክፍለ ጊዜ የቀረበው ትምህርት ተማሪዎች እንግዳ አቀባበልን በተመለከተ የእስካሁን ልምዳቸውን መሰረት አድርገው በሚና ጨዋታ መልክ ክፍል ውስጥ የሚያቀርቡበት ነው። እባክዎ መምህር ተማሪዎቹን የተወሰነ ቁጥር ባላቸው ቡድኖች ያደራጇቸው (አራት አራት ወይም አምስት አምስት)። በመቀጠልም የተወሰኑ ተማሪዎች እንደእንግዳ የተወሰኑት ደግሞ እንግዶቹን እንደሚቀበሉ የቤተሰብ አባላት በመሆን ሚና እንዲይዙና ልምምድ እንዲጀምሩ የተወሰነ ጊዜ ይስጧቸው። ከዚያም ምን ምን ምልልሶች ሊካሄዱ እንደሚችሉና ምን ምን ተግባራት ሊከናወኑ እንደሚችሉ እንዲለዩና በወረቀት ላይ ማስታወሻ እንዲያደራጁ ያድርጉ። ምልልሶቹና ተግባራቱ በየቡድኑ የተለያዩ እንደሚሆኑ ይጠበቃል። በመጨረሻም የሚና ጨዋታውን (የእንግዳ እና እንግዳ ተቀባይን) ተራ በተራ በክፍል ውስጥ ይከውኑ። በክወና ወቅት በእጃቸው እና በክፍል ውስጥ ያሉ የመማሪያና ሌሎች ቁሳቁሶች እንደየቤት እቃ መጠቀም እንደሚችሉም ይንገሯቸው።

ክፍለጊዜ ሶስት

# ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

## ተማሪዎች በዚህ ንዑስ ትምህርት ክፍል

- የጽሁፍን አጠቃላይ ሀሳብ ለማግኘት ያነባሉ።

### ቅድመ ንባብ

መምህር ተማሪዎችዎ በቀጥታ ወደ ንባብ ተግባሩ ከመግባታቸው በፊት ለማንበብ የተነሳሱ እንዲሆኑ በመጀመሪያ ‹‹ስነምግባር›› የሚለው ቃል የያዘው ፍቺ ምን እንደሆነ እንዲገምቱና መልሳቸውንም ለክፍሉ በቃል እንዲያሰሙ ይጋብዟቸው። በማስከተል ሰዎች መደበኛ የቢሮ/የንግድ/ ስራ ሲሰሩ ምን ምን የስራ ላይ ስነምግባሮችን ሊከተሉ እንደሚገባ በተመለከተ ይሆናሉ የሚሏቸውን ምላሾች እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፤ ቢቻልም ምክንያቶቻቸውንም አብረው እንዲጠቁሙ ያድርጉ። ከዚህ በተጓዳኝም ርዕሱን ተመልክተው ምንባቡ ስለምን እንደሆነ እንዲገምቱና ከ'ስነምግባር' በተጨማሪ ለተማሪዎችዎ ይከብዱ ይሆናል የሚሏቸውን ሁለት ወይም ሦስት ተጨማሪ ቃላትን አቅርበው ፍቻቸውን እንዲገምቱ ማድረግም ይችላሉ።

ለቅድመ ማንበብ ተግባር ከ5-6 ደቂቃዎችን ከተገለገሉ በኋላ ተማሪዎችዎ በቀጥታ ምንባቡን ወደ ማንበቡ እንዲገቡ ያድርጓቸው። ተፈጻሚነቱንም እየተዘዋወሩ ይመልከቱ።

### የንባብ ጊዜ

ተማሪዎች የምንባቡን ሶስት አንቀጾች አንብበው ካጠናቀቁ በኋላ የተነበቡትን ሶስት አንቀጾች መሰረት በማድረግ የተዘጋጁትን ጥያቄዎች ይመልሳሉ። ስለሆነም እባክዎ መምህር ተማሪዎች ንባባቸውን ገታ እንዲያደርጉ በመጠየቅ የቀረቡትን ጥያቄዎች እንዲሰሩ ያበረታቷቸው። ጥያቄዎቹን ከመለሱና ከተነጋገሩባቸው በኋላም ቀሪውን የንባብ ክፍል አንብበው እንዲያጠናቅቁ ይንገሯቸው።

በመጀመሪያው ዙር ሁሉም አንቀጾች ተነብበው ከተጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎች ምንባቡን አንዴ ፈጠን ባለ መልኩ ደግመው እንዲያነቡት ይንገሯቸው (በዚህ ጊዜ የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎቹ ይታለፉሉ)። አንብበው ሲጨርሱም ሙሉውን ምንባብ መሰረት በማድረግ

የድህረ ምንባብ ጥያቄዎቹን እንዲሰሩ ይጋብዟቸው። **መልመጃ ሁለት** ምንባቡ በተነበበት እለት ጥያቄዎቹን በመጻፍ እንዲመልሱ የሚደረግ ሲሆን፣ በተማሪዎቹ የማንበብ ደረጃ ላይ ተመስርቶም በየቤት ስራ መልክ ሰርተው እንዲመጡ ማድረግ ይቻላል።

### ክፍለጊዜ፡ አራት

መልመጃ ሦስትና አራት በክፍለጊዜ አራት ተማሪዎቹ ወይም እርስዎ አንዴ ምንባቡን ድምጽ እያሰሙ ካነበቡላቸው በኋላ የሚሰሩ ናቸው። ክሂሎችን እያቀናጁ ለመጠቀም ያመች ዘንድም መልመጃዎቹ በተማሪዎቹ መለማመጃ ደብተር ላይ ተጽፈው የሚመለሱ ናቸው። እባክዎ መምህር በዚሁ መሰረት እየተከታተሉ ያስፈጽሙ። ማበረታቻ፣ ማበልጸጊያና ምጋቤ ምላሽም እንደየሁኔታው እያስማሙ ይስጧቸው።

### ክፍለጊዜ አምስት

# ትምህርት አራት፡ ቃላት

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-**

- ለቃላት አውዳዊ ፍቺ ይሰጣሉ።
- በተለያዩ አውዶች ውሰጥ ተዘውታሪ ቃላትን ይጠቀማሉ።

## መልመጃ አምስት

በቃላት ትምህርት ክፍል ውስጥ ሁለት ክንውኖች ቀርበዋል። የመጀመሪያው የተሰጡ ቃላትን በመጠቀም ባዶ ቦታዎችን ማሟላት ሲሆን፣ ለዚህም አውድ የመረዳት እውቀታቸውን ተማሪዎቹ ተግባራዊ ያደርጉበታል። ሁለተኛው ክንውን ከምንባብ የወጡ ቃላትን ተዘውታሪ ከሆኑ ፍቻቸው ጋር ማዛመድን የተመለከተ ይሆናል። በመሆኑም እባክዎ መምህር አስቀድመው ስለተዘውታሪና ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላት አጭር ማብራሪያና ምሳሌዎች ይስጧቸው። እንደመነሻም በቀጣዩ ሳጥን ውስጥ ያሉ ነጥቦችን ይጠቀሙ።

| ተዘውታሪ ቃላት | ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላት |
|---|---|
| በእለት ከእለት የቋንቋ አጠቃቀማችን ወቅት ተግባቦትን ለማከናወን የምንጠቀምባቸው ቃላት ናቸው፡፡ (በአካባቢም በትምህርት ቤት ውስጥም ሊሆን ይችላል)። ምሳሌ፡- ምግብ፣ መንገድ፣ ልጅ፣ ገበያ፣ ጨዋታ፣ ተማሪ፣ ፈተና… | በእለት ከእለት ተግባቦት ወቅት የማንጠቀማቸው፤ የሙያ (የስራ መስክ) ቃላት ምሳሌ፡- ስነልሳን፣ ልሳነክልኤ፣ ምጣኔ ሀብት፣ ሙስና፣ ዋርድ ወዘተ |

ክፍለጊዜ ስድስት

# ትምህርት አምስት፡ መጻፍ

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-**

- አዳዲስ ሀሳቦችን በማሰስ አንቀጽ ይጽፋሉ።
- የአረፍተነገር መዋቅሮችን ለይተው ይጠቀማሉ።

## አንቀጽ መፃፍ

በክፍለጊዜ ስድስት የመጻፍ ክሂልን የተመለከተ ይዘት ቀርቧል። መምህር እባክዎ በተማሪ መጽሀፍ ላይ የቀረበውን ማስታወሻ መነሻ በማድረግ ስለአንቀጽ ማብራሪያ ይስጡ። ከዚያም ለመነሻ ይሆናቸው ዘንድ በመልመጃ ስድስት ስር የቀረቡ አረፍተነገሮችን በቅደም ተከተል አስቀምጠው አንቀጽ እንዲመሰርቱ ያድርጓቸው።

## መልመጃ ስድስት

መምህር አስቀድመው ተማሪዎችን በጥንድ በጥንድ ያቀናጇቸውና እየተወያዩ አረፍተነገሮቹን በቅደም ተከተል እንዲያደራጁ ያትጓቸው፤ እየተዘዋወሩም ይከታተሏቸው። ሲያጠናቅቁም ከሌላ ጥንድ ጋር በመሆን አራት አባላት ያለው አነስተኛ ቡድን ይመስርቱ። በማስከተልም አስቀድመው በጥንድ ሆነው ቅደም ተከተል ያስያዟቸው አረፍተነገሮችን እያነጻጸሩ ይመልከቱ፤ ማስተካከያ የሚያስፈልጋቸው ላይም ውይይት ያድርጉ። ስምምነት ላይ ያልደረሱበት ነጥብ ካለ ለክፍሉ ያቅርቡ። በመጨረሻም እያንዳንዱ የቡድን አባል ስምምነት የተደረሰበትን ቅደም ተከተል በመንተራስ አረፍተነገሮቹን በማያያዝ በደብተር ላይ አንቀጽ ይጻፉ፡፡

ክፍለጊዜ ሰባት

# አንቀጽ መጻፍ

## ተግባር ሁለት

መምህር በዚህ ክፍለጊዜ ተማሪዎች ስለቀረበላቸው ጉዳይ ሀሳብ አደራጅተው አንቀጽ መጻፍን የሚለማመዱበት ነው። በዚህም የመጻፍ ክሂላቸውን ለማጎልበት እድል ያገኙበታል ተብሎ ይጠበቃል። በመሆኑም እርስዎ አስቀድመው ዝግጅት በማድረግ በአንድ ችግር ላይ የመፍትሔ ሀሳብን የሚጠቁም ወይም ሌላ ማንኛውንም አንቀጽ በምሳሌነት ለተማሪዎችዎ በማቅረብ የእለቱን ትምህርት ይጀምሩ። በማስከተልም ስለአርፋጅ የሀሳብ ጓደኛቸው እንዲወያዩና ማርፈዱን ለማስቀረት ምን ምን የመፍትሔ ሀሳቦች እንደሚጠቁሙ፣ በውይይት እንዲያደራጁ በማበረታታትና የመፍትሔ ሀሳቦቹንም በአንቀጽ መልክ በየግላቸው በደብተራቸው ላይ ጽፈው እንዲያቀርቡ ያድርጉ። በመጨረሻም ደብተሮቻቸውን ሰብስበው እርማት ይስጡበት። ከሁሉ የተሻሉ ናቸው ያሏቸውን አንቀጾች መርጠውም ጸሐፊዎቹ በንባብ ለክፍል እንዲያቀርቡ ያድርጉ። የተማሪዎች ቁጥር ከፍ ባለበትና ክፍለጊዜው ረዘም ያለ ጊዜ በፈጀበት ክፍል ምጋቤ ምላሹ በተከታዩ ክፍለጊዜ የሚሰጥ ይሆናል።

ክፍለጊዜ ስምንት

## ተግባር ሦስት

ተግባር ሦስት እንደተግባር ሁለት ሁሉ ተማሪዎች አንቀጽ መጻፍን የሚለማመዱበት ወቅት ነው። ስለሆነም መምህር አንቀጽን በተመለከተ (ስለሀይለቃልና ዝርዝር አረፍተነገሮች፣ ስለሀሳብ አንድነት፣ ስለተለጣጣቂነት ወዘተ) አጠር ያለ የክለሳ ገለጻ ለተማሪዎችዎ ያቅርቡላቸው። በማስከተልም በየቡድናቸው ሆነው መልካም ስነምግባር የሌለው ተማሪ ስለሚያንጸባርቃቸው/ስለምታንጸባርቃቸው ባህሪያት እንዲወያዩ ያበረታቷቸው። ውይይታቸውን መነሻ በማድረግም አንቀጽ ጽፈው እየተለዋወጡ በማንበብ እንዲተራረሙ ያትጓቸው።

ክፍለጊዜ ዘጠኝ

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

### ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡

- ባለቤትንና ማሰሪያ አንቀጽን ይለያሉ።

መምህር በዛሬው ክፍለጊዜ ተማሪዎችዎ አረፍተነገር ምን እንደሆነ፣ የአረፍተነገር ተዋቃሪዎችም እነማን እንደሆኑ ለይተው የሚያውቁበት ነው። በመሆኑም አረፍተነገር አንድ ሙሉ ሀሳብን የያዘ የጽሑፍ ክፍል ሲሆን በቃላት የሚዋቀር ከሀረግ ከፍ ያለ የቋንቋ አሃድ መሆኑን ይንገሯቸው። በማስከተልም ምሳሌዎችን ያቅርቡላቸው።

ምሳሌ፡ **እኔ ጎበዝ ነጋዴ ነኝ።**

**ታናሽ እህቴ የኮሌጅ ትምህርቷን አጠናቃለች።**

ከላይ ያሉት የአረፍተነገር ምሳሌዎች እንደሆኑና ተማሪዎቹ ደግሞ ሶስት ምሳሌዎችን እንዲጨምሩ ይጠይቋቸው።

በማስከተልም አረፍተነገሮች የተለያዩ ተዋቃሪዎች እንዳሏቸውና በሁሉም አረፍተነገሮች ውስጥ የግድ መገኘት ያለባቸው ደግሞ ***ባለቤትና ማሰሪያ አንቀጽ*** እንደሆኑ ይንገሯቸው።

እርስዎ በሰጧቸውና ተማሪዎቹ ባቀረቧቸው ምሳሌዎች ውስጥ ያሉ ባለቤቶችንና ማሰሪያ አንቀጾችን ከተማሪዎችዎ ጋር በመሆን ለዩአቸው።

**ለምሳሌ፡** እኔ ጎበዝ ነጋዴ ነኝ። **(እኔ - ባለቤት፤ ነኝ - ማሰሪያ አንቀጽ)**

ታናሽ እህቴ የኮሌጅ ትምህርቷን አጠናቃለች። **(ታናሽ እህቴ - ባለቤት፤ አጠናቃለች - ማሰሪያ አንቀጽ)...**

## መልመጃ ሰባት (ሀ እና ለ)

**በማስከተል መልመጃ ሰባት 'ሀ' እና 'ለ'ን** በየትዕዛዛቸው መሰረት ደብተራቸው ላይ በመጻፍ እንዲመልሱ ይንገሯቸው። አፈጻጸማቸውንም እየተዘዋወሩ ይመልከቱ፤ ግብረመልስም ይስጧቸው።

እባክዎ መምህር ያለፈውን ክፍለጊዜ አጠር ባለመልኩ ይከልሱላቸው (ስለአረፍተነገር ምንነትና ስለተዋቃሪዎቹ)።

በመልመጃ ሰባት ሐ ስር በሳጥን ውስጥ ቢጣመሩ አረፍተነገሮች ሊሆኑ የሚችሉ ቃላትና ሀረጋት ተሰጥተዋል። መምህር እባክዎ ተማሪዎችዎ ሳጥኑ ውስጥ ያሉትን ቃላትና ሀረጋት በመጠቀም አረፍተነገሮች እንዲመሰርቱ ይንገሯቸው፡፡

# 4. ግምገማ

- በጥሞና አዳምጠው ምላሽ መስጠታቸውን ያረጋግጡ፡፤
- የስራ ስነምግባር ምንነት ጽንሰሀሳብን ማብራራታቸውን ይከታተሉ።
- አዳዲስ ሀሳቦችን በማሰስ አንቀጽ መጻፋቸውን ይከታተሉ።
- የስራ ስነምግባር ማሳያዎችን ማመልከታቸውን ይከታተሉ።
- የመጀመሪያ ቋንቋ ተገቢ መዋቅሮችን ተጠቅመው አንቀጽ መጻፋቸውን ያረጋግጡ።
- የጸሁፍ አጠቃላይ ሀሳብ ለማግኘት ማንበባቸውን ይጠይቋቸው፡፤
- በተለያዩ አውዶች ውሰጥ ተዘውታሪ ቃላትን መጠቀማቸውን ይከታተሉ።
- በአረፍተነገር ውስጥ ባለቤትና ማሰሪያ አንቀጽ መለየታቸውን ይመልከቱ

# 5. የመልመጃዎች መልስ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

### ቅድመማዳመጥ

1. **መከባበር ምን እንደሆነ የየራሳቸውን መልስ ይሰጣሉ (ለምሳሌ፡ አንዱ አንዱን አለመናቅ፤ በመተሳሰብ መኖር…)**
2. **የተለያየ መልስ (ለምሳሌ፡ ሰላም ያመጣል፣ አብሮ ለመኖር ጠቃሚ ነው፣ ለአካባቢና ሀገራዊ እድገት ወሳኝ ነው…)**
3. **የየተማሪዎች የየቤት ልምድ**

### የማዳመጥ ጊዜ

1. መብትና ግዴታውን
2. ሌላውን
3. መደማመጥና የመፍትሔ ሀሳብ
4. ከራስ/ከግለሰብ

### የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

1. ገበያ፣ መሰብሰቢያ ስፍራ፣ የእምነት ስፍራዎች፣ የእረኛ ቦታ፣ የቀብር ስፍራ

2. መነጋገር፣ መተባበር፣ በህግ የበላይነት ማመን፣ ማህበረሰብን ማዘመን (በትምህርት) ወዘተ
3. ተማሪዎች የሚሰጡ የተለያዩ መልሶች (**ለምሳሌ፡** በቡድን ውይይት ወቅት እንደማመጣለን፣ ጥፋት የሚጠፉትን እንገስጻለን፣ ትኩረት ሁሉ ወደ ትምህርት እንዲሆን እንመካከራለን…)

## መልመጃ አንድ

ሀ. መከባበርና ተስማምቶ መጠቀም

ለ. ሌሎችን ማክበር

ሌሎችን በዚሁ መሰረት ያሰሯቸው።

ለ. ባዶ ቦታዎችን ሙሉ

1. መብትና ግዴታውን
2. መመካከር፣ መወያየትና የጋራ ግንዛቤን መፍጠር
3. ማንነታቸውንና ስነልቦናቸውን
4. ሀሳብ ማክበር

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

## ተግባር አንድ

ተማሪዎቹ ያዘጋጇቸውን ምልልሶችና ክንውኖች መሰረት አድርጎ ሚና መጫወት

# ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

## ቅድመማንበብ ጥያቄዎች

1. የተለያዩ መልሶች (**ለምሳሌ፡** ስነምግባር ማለት ከአንድ ሰው የሚጠበቅ መልካም ጠባይ ነው…)
2. የተለያዩ መልሶች (**ለምሳሌ፡** ሰዓት ማክበር፣ ታማኝ መሆን፣ ውጤታማ መሆን፣ የአገልጋይነት ስሜት መላበስ፣ በመከባበር መስራት…)

## የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. መልካም ስነምግባር እና ውጤታማነት
2. ውጤታማ የሆኑት

3. **እምነት የሚጣልባቸው መሆን እና ቀናነትን መላበስ** ከፍ ያለ ብቃት ያላቸው ሰራተኞች የሚጎናጸፏቸው መለያዎች ናቸው ብለው ስለሚያምኑ

## የድህረማንበብ ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

1. መ
2. ሀ
3. ሐ
4. መ
5. ለ
6. ሐ
7. ለ

### መልመጃ ሦስት (ክፍለጊዜ አራት)

1. መ
2. ሐ
3. ሠ
4. ሀ
5. ለ

### መልመጃ አራት

ተማሪዎቹ ይሆናሉ የሚሏቸውና በሌሎች ዘንድም ተቀባይነት ያላቸው ማናቸውም መልሶች

## ትምህርት አራት፡ ቃላት

### መልመጃ አምስት

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሀ. 1. ጎረቤታሞች | 5. ትምህርት ቤት | ለ. 1. በ | 5. ሀ | 9. መ |
| 2. ገበያ | 6. ሀገር | 2. ሠ | 6. ቀ | 10.ሐ |
| 3. ውሃ | 7. መንገድ | 3. ሰ | 7. ረ | |
| 4. ወላጆች | 8. ምግብ | 4. ሽ | 8. ለ | |

# ትምህርት አምስት፡ መጻፍ

## መልመጃ ስድስት

ትክክለኛው ቅደም ተከተል፡ 3፣ 1፣ 6፣ 4፣ 8፣ 2፣ 9፣ 7፣ እና 5

## ተግባር ሁለት

ተማሪዎቹ አርፋጅ ጓደኛቸውን በተመለከተ የሚጽፏቸው የተለያዩ አንቀፆች

## ተግባር ሦስት

መልካም ስነምግባር የሌለው ተማሪ የሚያሳያቸውን ባህሪያት በተመለከተ ተወያይተው የሚይዙትን ማስታወሻ በመንተራስ ተማሪዎች የሚጽፏቸው የተለያዩ አንቀጾች

# ትምህርት አምስት፡ ስዋስው

## መልመጃ ሰባት

**ሀ.**

1. **ባለቤት፡** ሀኪሞች **ማሰሪያ አንቀጽ፡** ይደሰታሉ
2. **ባለቤት፡** መረዳዳት **ማሰሪያ አንቀጽ፡** ነው
3. **ባለቤት፡** በርካታ ህጻናት **ማሰሪያ አንቀጽ፡** ይገደዳሉ
4. **ባለቤት፡** የኮሮና በሽታ **ማሰሪያ አንቀጽ፡** ሆኗል
5. **ባለቤት፡** የስራ ላይ ስነምግባር **ማሰሪያ አንቀጽ፡** ነው

**ለ. ተማሪዎች የሚጽፏቸው የተለያዩ አረፍተነገሮች**

| | | |
|---|---|---|
| ላሚቱ | አምስት ሌትር ወተት | በየቀኑ ትታለባለች |
| ኢትዮጵያ | በአፍሪካ ቀንድ | ትገኛለች |
| ቶለሳ | በርትቶ ስለምያጠና | በትምህርቱ ውጤታማ ሆኗል |
| ባህላዊ ምግቦች | በተለያዩ ክብረበዓላት | ይዘጋጃሉ |
| የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች | ከተወሰኑ ወራት በኋላ | ለክልላዊ ፈተና ይቀመጣሉ |
| መገርቱና ሂርጳ | በትምህርታቸው | ጎበዞች ናቸው |
| ታላቅ እህቴ | በኮምፒውተር ጥገና ሙያ | በከፍተኛ ማዕረግ ተመረቀች |

# ምዕራፍ ሁለት

# ባህላዊ ቅርስ

(የክፍለጊዜ ብዛት 12)

## 1. የሚጠበቁት ውጤቶች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- የሌሎችን ሀሳብ በጥልቀት ያዳምጣሉ፤
- የቃላትን ፍቺ ከምንባቡ በመነሳት ይረዳሉ፤
- የባህልንና ቅርስን ጽንሰ ሀሳብ ያብራራሉ፤
- ባለሶስት አንቀጽ አመዛዛኝ ድርሰት ይጽፋሉ፤
- በተለያዩ አውዶች ውስጥ አዳዲስ ቃላትን ይጠቀማሉ፤
- ውስብስብ ሁነቶችን በቅደምተከተል ይተርካሉ።

## 2. የትምህርት ይዘት

### 2.1 ማዳመጥ

- የሚነበበውን ምንባብ ማዳመጥ
- ስለአባጅፋር ለመረዳት ማዳመጥ
- ዝርዝርና ዋና ሀሳቦችን ለመለየት ማዳመጥ
- ምንባቡን መሰረት አድርገው የወጡ ጥያቄዎችን ለመመለስ ማዳመጥ

### 2.2 መናገር

- በጥያቄዎች ላይ ተወያይቶ ንግግር ማድረግ
- የባሌ ብሔራዊ ፓርክ ከሌሎች ፓርኮች በምን በምን እንደሚለይ መናገር
- ቅርስን ጎብኝቶ ወይም ባለሞያዎችን ጠይቆ ስለቅርስ ንግግር ማድረግ
- ተዘበራርቀው የተቀመጡ ሁነቶችን ቅደምተከተላቸውን በማስያዝ መናገር

### 2.3 ማንበብ

- "የገዳ ስርዓት ባህላዊ ቅርስ "በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ማንበብ
- የተቀረው የምንባብ ክፍል ስለምን እንደሚያወሳ ማንበብ

- የምንባቡን ዝርዝርና ዋና ሀሳቦች ለመለየት ማንበብ
- ምንባቡን መሰረት አድርገው የወጡ ጥያቄዎችንና መመለስና ተግባራትን መከወን

## 2.4 ቃላት

- አዳዲስ ቃላትን በተለያየ አውዶች አውዳዊ ትርጉም መስጠት
- የአዳዲስ ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ

## 2.5 መጻፍ

- በቀረቡት ርዕሶች ሶስት አንቀጽ ያለው አመዛዛኝ ድርሰት መጻፍ
- የስዕልን ማጠቃለያ  መጻፍ።
- አንድ ባህላዊ ቅርስን ጎብኝቶ ስለቅርሱ መጻፍ

## 2.6 ሰዋስው

- የአሁን ጊዜ የግስ አንጻርን መለየት

# 3. የማስተማሪያ ዘዴ

- የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎችን እንዲሰሩ መጠየቅ
- አዎንታዊ ምላሽ መስጠት
- ያዳመጡትን መሰረት አድርገው የተወያዩበትን እንዲናገሩ ማበረታታት
- ያዳመጡትን መሰረት አድርገው ጥያቄዎች ላይ በቡድን በመሆን ከተወያዩ በኋላ የደረሱበትን ድምዳሜ ለክፍል ጓደኞቻቸው በቃል እንዲያቀርቡ ማነሳሳት
- ችግርን የማቃለል ተግባራትን ሰጥቶ መፍትሄ እንዲያመነጩ ዕድል መስጠት
- ተዘበራርቀው የተቀመጡትን ተግባራት ቅደም ተከተል በማስያዝ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲተርኩ ማበረታታት ።
- ከክፍል ውጪ የሚሰሯቸው መስተጋብርን የሚፈጥሩ ተግባራትን መስጠት
- ስለገዳ ስርዓት ባህላዊ ቅርስ የሚያውቁትን እንዲናገሩ ማነሳሳት
- ስለገዳ ስርዓት ባህላዊ ቅርስ የተመለከቱትን እንዲናገሩ ማበረታታት
- የአንብቦ መረዳት ስልቶችን ተግባራዊ አድርገው ‹‹የገዳ ስርዓት ባህላዊ ቅርስ›› የሚለውን ምንባብ እንዲያነቡ ማድረግ

- ማብራሪያ የሚፈልጉ ጥያቄዎችን ማቅረብ
- ምንባቡን መሰረት አድርገው የወጡ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ማበረታታት
- በአረፍተነገር ውስጥ ያሉ ቃላትን አውዳዊ ትርጉም እንዲሰጡ አቅጣጫ ማሳየት
- በቀረበላቸው ርእስ መነሻነት ሶስት አንቀጽ ያለው አመዛዛኝ ድርሰት ምሳሌ አቅርቦ እንዲጽፉ ማገዝ
- ስዕል ተመልክተው የስዕሉን ማጠቃለያ እንዲጽፉ ማድረግ
- የአሁን ግስ አንጻርን ተጠቅመው እንዲጽፉ ማበረታታት

**ክፍለጊዜ አንድ**

# ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-**

- የሌሎችን ሀሳብ በትኩረት አዳምጠው ምላሽ ይሰጣሉ።

## ቅድመ ማዳመጥ

በትምህርት አንድ ስር የተማሪዎችን የማዳመጥ ፍላጎት የሚያነሳሱ የተለያዩ ተግባራት ቀርበዋል፡፡ ተማሪዎቹ እነዚህን ተግባራት እንዲያከናውኑ ያድርጓቸው፡፡ ተግባራቱም፡-

- በሀገራችን የሚገኙ ጥንታዊ ቅርሶችን እንዲዘረዝሩ ያድርጉ፤
- የቀረበውን የአባ ጅፋር ቤተመንግስት ፎቶግራፍ በመመልከት የተገነዘቡትን ለጓደኞቻቸው እንዲያጋሩ ያበረታቱ፤

የአባጅፋር ቤተመንግስትን የሚያሳይ ተንቀሳቃሽ ምስል ያሳዩአቸው፡፡ በመቀጠል ካዩት ምስል ምን እንደተረዱ እየጠየቋቸው መልስ ይቀበሉ፡፡ ከዚያም ወደ ዋናው ትምህርት ይግቡ፡፡ አስቀድመው ከዚህ በታች የቀረበውን ምንባብ ሁለት ጊዜ ያንብቡላቸው፡፡ በመጀመሪያው ንባብ አጠቃላይ፣ በሁለተኛው ንባብ ዝርዝር ጉዳዮች ላይ ትኩረት ሰጥተው እንዲያዳምጡ ያድርጉ፡፡

# የአባ ጅፋር ቤተመንግስት

የአባ ጅፋር ቤተመንግስት በኦሮሚያ ክልል ጅማ ከተማ የሚገኝ ታሪካዊ እና ባህላዊ ቅርስ ነው:: ቤተመንግስቱ በጅማ ከተማ ሰባት ኪሎሜትሮች ያህል ወጣ ብሎ በ1880ዎቹ አካባቢ የተመሰረተ ሲሆን የቆሮቆሩት ንጉስ አባ ጅፋር ሁለተኛ ናቸው፡፡ የአባ ጅፋር ቤተመንግስት ከባህር ጠለል 2000 ሜትሮች ከፍታ ላይ ይገኛል፡፡ ከዚህ ከፍታ ላይ በመሆን ጠላትን ከሩቅ ሲመጣ መከታተል ከማስቻሉም በላይ የወባ ትንኝን ለማራቅ ያመቻል፡፡

የአባ ጅፍር ግዛት በቀጠናው ጠንካራ ከነበሩት ግዛቶች ቀዳሚው ነበር፡፡ ለዚህም ምክንያት የሆነው በወቅቱ ከፋ ይባል የነበረውን የደቡብ ግዛት አካባቢን መቆጣጠር በመቻሉ ነበር፡፡ እንዲሁም ግዛታቸው ከሰሜናዊ ሱማሊያ ዳርቻ ወደብ ጋር ትስስር የነበረው ሲሆን ትስስሩም የህንድን ባህር ከሚሻገረው ዋነኛ የንግድ መስመር ጋር ይያያዝ ነበር፡፡

የአባ ጅፋር ቤተመንግስት በርካታ ቅርሶች ያሉት እና ከፍተኛ ጥበቃ የሚደረግለት ጥንታዊ ቅርስ ነው፡፡ የዚህ ቤተመንግስት የኪነህንጻ ስራት አብዛኛው ግብዓቱ እንጨት ሲሆን አሁንም ድረስ ባህላዊ ቅርስነቱን ጠብቆ ይገኛል፡፡ ቤተመንግስቱ ከፍተኛ ባህላዊ እና ታሪካዊ ጠቀሜታ ያለው ቅርስ ከመሆኑ የተነሳም በከፍተኛ ጥንቃቄ የእድሳት ተግባሩ ወቅቱን ጠብቆ እየተከናወነለት ይገኛል፡፡ ስነህንጻው የደቡብ ምእራብ ባህላዊ የቤት አሰራር እና የኢንዶ አረባዊ የኪነህንጻ ጥበብን አጣምሮ ያዘ ነው፡፡ የግንባታው ጥበብ በአብዛኛው በህንድ ባህር የሰፈሩ ሰዎች ከሚጠቀሙት ጋር የተቀራረበ ነው ማለት ይቻላል፡፡

የንጉስ አባ ጅፋር ቤተመንግስት በየዓመቱ በበርካታ በሀገር ውስጥና በውጭ ቱሪስቶች የሚጎበኝ ሲሆን ለክልሉ እና ለሀገሪቷ የገቢ ምንጭ በመሆን እያገለገለ ይገኛል፡፡

እባክዎ መምህር በተማሪ መማርያ መጽሀፍ የቀረቡትን ጥያቄዎች ተማሪዎች ደብተሮቻቸው ላይ እንዲጽፉ ያድርጉ፤ ይህም ምንባቡ ከመነበቡ አስቀድሞ ይሁን። ጥያቄዎቹንም እያዳመጡ በግል መስራታቸውን ይከታተሉ፡፡ የማዳመጥ ጽሁፉን አንብበው ከጨረሱ በኋላ ወደ የአዳምጠ መረዳት ጥያቄዎች ከመግባታቸው አስቀድመው መልሶቻቸውን በጥንድ ወይም በአነስተኛ ቡድን እንዲወያዩበት ጊዜ ይስጧቸው፡፡

# የድህረማዳመጥ ጥያቄዎች

## መልመጃ አንድ

በመልመጃ አንድ ስር ከምንባቡ የወጡ አምስት ያህል ጥያቄዎች ቀርበዋል። መምህር እባክዎ ተማሪዎች እነዚህን ጥያቄዎች እንዲመልሱ ይረዳቸው ዘንድ የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎችን ከመለሱና ምንባቡንም ለሁለተኛ ጊዜ ካዳመጡ በኋላ ጥያቄዎቹን እንዲያነቧቸው ያድርጉ። ጥያቄዎቹን ካነበቡ በኋላም መጀመሪያ በግል ቀጥሎም ጥንድ ጥንድ እየሆኑ መልሶቻቸውን እንዲያነጻጽሩ ያሳስቧቸው። በጥያቄዎቹ ምላሾች ላይ እርግጠኝነት የሚጎላቸው ከሆነ *የአባ ጅፋር ቤተመንግስትን* የተመለከተውን ምንባብ አንድጊዜ ደግመው ያንብቡላቸው። በመጨረሻም ጥያቄዎቹን እንደክፍል በጋራ በመመለስ ወደ ተግባር አንድ ተሸጋገሩ። ተግባር አንድ የአባጅፋርን ቤተመንግስት አሁናዊ ሁኔታ የተመለከተ ሲሆን ተማሪዎች ውይይት ካደረጉ በኋላ የቃል ዘገባ የሚያቀርቡበት ነው።

### ክፍለጊዜ ሁለት

## መልመጃ ሁለት

በዚህ ክፍል ተማሪዎች የአባጅፋርን ቤተመንግስትና አጠቃላይ የቅርሶች መኖር ለአካባቢውና ለሀገር የሚኖረውን ጠቀሜታ በተመለከተ ውይይት የሚያደርጉበት ነው። እባክዎ መምህር ተማሪዎች በቅርስ ጥበቃ ሊኖራቸው የሚችለውን ሚና በተመለከተና ቅርሶች ስለሚሰጡት ጠቀሜታ አስቀድመው እንዲወያዩ በማድረግ ሀሳቦቻቸውን እንዲጋሩ ያድርጉ። ቀጥሎም ከዚህ በታች በቀረቡት ሀሳቦች ላይ (በተማሪ መጽሐፍ ላይም ተገልጸዋል) በአነስተኛ ቡድን ሆነው በመወያየት ጽብረቃ እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው።

ሀ. የአባ ጅፋር ቤተመንግስት መገኛ ስፍራ

ለ. የአባ ጅፋር ግዛት መጠናከር ምክንያት

ሐ. የአባ ጅፋር ቤተመንግስት አሁናዊ ሁኔታ

መ. የአባ ጅፋር ቤተመንግስት ጥቅም

ክፍለጊዜ ሶስት

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-**

- በተለያዩ ተጋባራት ላይ ተወያይተው ንግግር ያደርጋሉ።
- ውስብስብ ሁነቶችን በቅደምተከተል ይተርካሉ።

## ተግባር ሁለት

እባክዎ መምህር ተማሪዎች ከተለያዩ ምንጮች በሀገር አቀፍ ደረጃ ፣ በክልላቸው ወይም በአካባቢያቸው ስለሚታወቁ ጥንታዊ ቅርሶች መረጃ እንዲያሰባስቡና ያሰባሰቡትንም በማደራጀት ዝግጅት አድርገው የቃል ዘገባ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው። የተሻለ የሰሩትንም በስም በመጥቀስ የዕለቱ ጥሩ ፈጻሚዎች መሆናቸውን ያውጁላቸው።

ክፍለጊዜ አራት

## ተግባር ሦስት

መምህር ተማሪዎችዎ ተጨማሪ ዝግጅት አድርጎ የመናገር እድል የሚሰጣቸው ተግባር ተሰናድቶላቸዋል። በመሆኑም አሁን ካሉበት አካባቢ በመነሳት የአባ ጅፋርን ለመጎብኘት ቢፈልጉ በየትኛው አቅጣጫ መጓዝ እንደሚኖርባቸው እንዲናገሩና በጉዟቸው ወቅትም ሊያልፉ የሚችሉባቸውን ከተሞች፣ የገጠር መንደሮች ወይም ቦታዎች በየቡድናቸው በመሆን ተወያይተው ሀሳብ በማውጣጣት እንዲመልሱ ያበረታቷቸው። ምላሾቻቸውን በየግላቸው መልሰው ለቡድኑ ካቀረቡ በኋላ በተወካያቸው በኩል ደግሞ ለክፍሉ ያሰማሉ። መምህር ከዚህ የመወያያ ርዕስ በተጓዳኝ ሌላ በተማሪዎች ዘንድ በስፋት የሚታወቅ የጉብኝት ስፍራን በተመለከተ እንዲናገሩም በአማራጭነት መያዝ ይችላሉ።

ክፍለጊዜ አምስት

## ተግባር አራት

መምህር ተማሪዎች ስለአካባቢያቸው ይበልጥ እንዲያውቁና ማህበራዊ ግንኙነታቸውንም እንዲያጠናክሩ፣ ከሁሉም በላይ ግን ሰፋ ያለ ተግባቦት እያካሄዱ የንግግር ክሂላቸውን

በተግባር እንዲያጎለብቱ ያመች ዘንድ ሁኔታዎችን በማመቻቸት የመስክ ላይ ጉብኝት እንዲያደርጉ ማቀድ ተገቢ ይሆናል። በዚህም መሰረት ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚገኝን ተፈጥሯዊ ወይም ታሪካዊ ወይም ባህላዊ ቅርስ እንዲጎበኙ እርስዎ አስቀድመው በማቀድና የጉብኝት ጊዜውን በማመቻቸት (ከትምህርት ሰዓት ውጪ ሊሆን ይችላል) የመጎብኘት እድል ይፍጠሩላቸው፤ እራስዎንም የጉብኝቱ ተሳታፊ ማድረግዎ ለውጤታማነቱ ወሳኝ ነው። በቀጣዩ ክፍለጊዜም የቃል ዘገባቸውን ተራ በተራ እንዲያቀርቡ ያድርጉ። ለተሳትፏቸውም ያመስግኗቸው። አካባቢን/ሀገርን የማወቅ ጥቅምንም ይንገሯቸው።

**ክፍለጊዜ ስድስት**

# ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-**

- የምንባብን ሀሳብ ለመረዳት ያነባሉ።

መምህር በዚህ ክፍለጊዜ ተማሪዎችዎ ማንበብን በክፍል ውስጥ በተግባር የሚለማመዱበት ነው። ይህ ልምምድም በወደፊቱ የእውኑ አለም ህይወታቸው አንባቢዎች እንዲሆኑና በተሰማሩበት መስክም ስኬታማ እንዲሆኑ ፈር ይቀድላቸዋል። በትምህርት ሦስት የማንበብ ተግባሩን በሶስት ደረጃዎች ከፍለው ማቅረብ የሚጠበቅብዎ ሲሆን ቀጥለን አንድ በአንድ እንያቸው።

**ቅድመ ንባብ**

በዚህ ቀዳሚ ክፍል ተማሪዎች የሚያነቡትን ይዘት በተመለከተ የቀደመ እውቀታቸውን በመቀስቀስና ተነሳሽነታቸውን በመጨመር ለማንበብ ዝግጁ እንዲሆኑ የሚደረግበት ነው። በመሆኑም እባክዎ መምህር የተወሰነ ደቂቃ ወስደው የቀረቡትን ሦስት የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች ተማሪዎችዎ በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ፤ የተማሪዎችዎን ዳራዊ እውቀት መነሻ በማድረግም ይከብዷቸዋል ብለው ያሰቧቸውን ውስን ቃላት (ሁለት ወይም ሦስት) ከምንባቡ በመውሰድ ፍቺያቸውን እንዲገምቱ ያድርጉ። ይህንን ሲጨርሱም ተማሪዎችዎ ወደ ማንበብ ተግባሩ በትኩረት እንዲገቡ ያበረታቷቸው።

## የንባብ ጊዜ

በምንባብ ጊዜ ተማሪዎች ‘ሉኮ’ ስለተሰኘ ባህላዊ የእርቅ ስርኣት የሚያነቡ ይሆናል። ምንባቡን ባጠቃላይ ለሁለት ጊዜ የሚያነቡት ሲሆን፣ በመጀመሪያው ማንበብ አፍታ ጊዜ ወስደው በምንባቡ ውስጥ የቀረቡትን የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ። የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎቹ በቁጥር ሰባት ሲሆኑ መምህር እባክዎ የተነበበውን የምንባብ ክፍል መሰረት አድርገው እንዲመልሱ ያበረታቷቸው፤ ጊዜም ሰጥተው በተያዙት ደቂቃዎች እንዲያጠናቅቋቸው ያድርጉ። ያንን ሲጨርሱ ቀጣዩን ክፍል ወደ ማንበቡ እንዲመለሱ ያድርጓቸው። ሲጨርሱ ምንባቡን አንዴ መለስ ብለው በቀለጠፈ መንገድ እንዲያነቡት ያድርጓቸው።

**ክፍለጊዜ ሰባት**

## የአንብቦመረዳት ጥያቄዎች/ድህረ ማንበብ/

### መልመጃ ስስት

ምንባቡ ተነቦ ሲጠናቀቅ በጽሑፍ የሚመለሱ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ቀርበዋል። መምህር እባክዎ በዚህ ክፍለጊዜ ምንባቡን አንድ ጊዜ እንዲነበብ ያድርጉና (በአማራጭነት እርስዎም ድምጽ አሰምተው ሊያነቡላቸው ይችላሉ) በመልመጃ ሁለት ስር ያሉ ጥያቄዎችን ሁሉም ተማሪዎች በደብተራቸው ላይ ጽፈው መልስ እንዲሰጡባቸው ይጠይቋቸው። በመቀጠልም ከጎናቸው ካሉ የክፍል ጓደኞች ጋር ጥንድ ጥንድ እየሆኑ የጻፉትን እንዲያነጻጽሩ ያበረታቷቸው፤ አፈጻጸሙንም እየተዘዋወሩ ይመልከቱ።

## ተግባር አምስት

መምህር ተማሪዎችዎ አስራ አንዱን የድህረ ማንበብ ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት አድርገው ከመለሱና እንደክፍል ምላሾቹ ላይ ከተነጋገራችሁ በኋላ የሚቀጥለው በተግባር 5 ስር በተቀመጠው መሰረት የግጭት ማስወገጃ ደረጃዎች የተባሉትን ለይተው በማውጣት ስለምንነታቸው ከተወያዩ በኋላ የደረሱበትን በየቡድን ተወካያቸው አማካኝነት ለክፍሉ በቃል እንዲያቀርቡ ያትጓቸው። እንደተለመደውም በውይይት ወቅት በክፍሉ ውስጥ እየተዘዋወሩ እንደየሁኔታው ማበልጸጊያ ወይም ድጋፍ ይስጧቸው።

ክፍለጊዜ ስምንት

## ትምህርት አራት፡ ቃላት

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-**

- በተለያዩ አውዶች ውስጥ አዳዲስ ቃላትን ይጠቀማሉ።
- ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ይሰጣሉ።

### መልመጃ አራት

በቃላት ትምህርት ክፍል ተማሪዎች አውድን መሰረት አድርገው የሚሰሯቸው ጥያቄዎችና ቀደም ሲል ሉኮ በሚል ርዕስ ካነበቡት ምንባብ የወጡ ቃላትን ከፍቻቸው ጋር እንዲያዛምዱ የሚጋብዝ ተግባር ቀርቧል። በመሆኑም መምህር ተማሪዎችዎ መጀመሪያ በ **ሀ** ስር የቀረቡትን አረፍተነገሮች ደብተራቸው ላይ እንዲገለብጡና የተሰመረባቸውን ቃላትና ሀረጋት ፍቺ አውዱን መሰረት አድርገው እንዲመልሱ ያበረታቷቸው። ሲጨርሱም መልሶቻቸውን ከብጤዎቻቸው ጋር ያነጻጽሩ። በመጨረሻም እንደክፍል ምላሾቹ ላይ ተነጋገሩባቸው። በማስከተል በ **ለ** ስር በአዛምድ መልክ (**ሀ** እና **ለ**) የቀረቡትን ቃላት በመጻፍ ከፍቻቸው ጋር እንዲያዛምዱ ያድርጓቸው። ምላሾቻቸውንም እንደክፍል ተነጋገሩበት። ለተሳትፏቸው አመስግነውም የእለቱን ትምህርት ያጠናቅቁ።

ክፍለጊዜ ዘጠኝ

## ትምህርት አምስት፡ መጻፍ

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-**

- ሶስት አንቀጾች ያሉት ድርሰት ይጽፋሉ።
- የስዕል ማጠቃለያ ይጽፋሉ።

### መጻፍ

የዕለቱ ትምህርት አንቀጽ መጻፍ እንደሆነ በመግለጽ በተማሪው መጽሀፍ ላይ የቀረበውን ማስታወሻ መነሻ በማድረግ ስለአመዛዛኝ ድርሰት ሰፋ ያለ ማብራሪያ ይስጡ። እርስዎ ለአመዛዛኝ ድርሰት የመረጡትን ምሳሌ አቅርበው ካነበቡላቸው በኋላም ተማሪዎችዎ ስለአመዛዛኝ ድርሰት የተረዱትን መልሰው እንዲናገሩና በመጽሐፋቸው ላይ ያለውን ማስታወሻ እንዲጽፉ ይንገሯቸው። ከዚያም ‹‹ከእርስዎ ጋር በመሆን

አመዛዛኝ ድርሰት ሊያጽፈን ይችላል ብለው በመረጡት ርዕስ መነሻነት አመዛዛኝ ድርሰት በቤታቸው ጽፈው እንዲመጡና ለክፍል በንባብ እንዲያቀርቡት ይዘዟቸው።

**ክፍለጊዜ፡ አስር**

# አመዛዛኝ ድርሰት መጻፍ

## ተግባር አምስት

የዕለቱ ትምህርትም አመዛዛኝ ድርሰት መጻፍ እንደሆነ በመግለጽ በባለፈው ክፍለ ጊዜ የተሰጣቸውን ማብራሪያና ከጻፉት አመዛዛኝ ድርሰት ያገኙትን ዕውቀትና ግብረ መልስ ተጠቅመው በመግሪያ መጻፋቸው ላይ ከቀረቡት ርእሶች አንዱን መርጠው በመደገፍ ወይም በመቃወም ሶስት አንቀጽ ያለው አመዛዛኝ ድርሰት እንዲጽፉ ይዘዙ። ከዚያ በፊት የሚከተለውን ማስታወሻም ማብራሪያ ያድርጉላቸው።

**አመዛዛኝ ድርሰት፡** አንድ ጸሀፊ አንድ የሚያከራክር ሀሳብን ይዞ በመነሳት በሀሳቡ ዙሪያ ያለውን የግል አመለካከት ሌላው ሰው እንዲቀበለው ወይም እንዲያምን በማድረግ ይጽፋል። በዚህም ጸሀፊው ያመነባቸውን ምክንያቶች፣ ማብራሪያዎችና እውነታዎች አቅርቦ ለማሳመን ጥረት የሚደረግበት የድርሰት አይነት ነው። በመጨረሻም አንባቢው የጸሀፊውን አመለካከት ተቀብሎ ያምናል።

**ምሳሌ፡ *ስነጥበብ***

ብዙ ሰዎች በትምህርት ቤት ውስጥ ጥሩ ያልሆነ የፈጠራ ጥበብ ልምድ አላቸው።ልክ እንደ ሙዚቃ ወይም ስፖርት የተለየና ተደራቢ የትምህርት አይነት አድርገው ያዩታል። በትምህርት ቤት ውስጥ ለስነጥበብ የሚሰጠው ጊዜ አነስተኛ ነው። ለሂሳብና ሳይንስ የተለየ ቦታ ለመስጠት ሲባል ስነ-ጥበብ ከስርዓተ ትምህርቱ ለመውጣት የታሰበ ይመስላል። በብዙዎቹ እይታ ይህ ትልቅ ስህተት ነው። ስነጥበብ ለህጻናት ትምህርት በጣም ጠቃሚ ስለመሆኑ ብዙ ማሳመኛ ምክንያቶች አሉ። የመጀመሪያው ህጻናትን ለየት ባለ መንገድ እንዲያስቡ ያስተምራል። ሌላው የስነ-ጥበብ ትምህርት ጠቀሜታ ሁሉም ሊሰራው የሚችል መሆኑ ነው።...

ከላይ በቀረበው አንቀጽ ውስጥ ጸሀፊው የስነ-ጥበብ ትምህርት በትምህርት ቤት ውስጥ የተሰጠው ትኩረት አናሳ መሆኑን በመግለጽ ይህም ትክክል አለመሆኑን የራሱን ምክንያት በማቅረብ በሱ ሀሳብ በተቃራኒው ያሉ ሰዎችን ለማሳመን ጥረት ያደርጋል።

በተጨማሪም ጸሀፊው ባነሳው ጉዳይ ላይ ያለውን ምን አይነት አቋም እንዳለው ያሣያል። በዚህም አንባቢው የስነ-ጥበብ ትምህርት ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ምን ያህል ትኩረት እንደተሰጠው ይረዳል።

በዚህ ጊዜም ይከታተሏቸው፤ ዕገዛም ያድርጉላቸው። በክፍለጊዜው መጨረሻም የዚህኑ ይዘት ትምህርት የሚያጎለብቱ ተግባራትን ተማሪዎች በቤት ስራ መልክ ሰርተው እንዲመጡ ይዘዟቸው።

**ክፍለጊዜ አስራ አንድ**

# ስለስዕል መጻፍ

## ተግባር ስድስት

በዚህ የትምህርት ጊዜ ተማሪዎች መጻፍን እንዲለማመዱ ይጠበቃል። በመሆኑም የቀረበውን የአቴቴ ስነስርኣት አፈጻጸም የተመለከተ ጽሑፍ ይጽፋሉ። መምህር አስቀድሞ ግን ተማሪዎችዎ ስዕሉ ስለምን እንደሆነ እንዲገምቱና የገመቱትንም ለጓደኞቻቸው በመንገር ሀሳብ እንዲዋወጡ ያበረታቱ። የተማሪዎቹ ግምት ትክክል ከሆነ በዚሁ በስዕሉ ስለተመለከቱት ተግባራት ቅደምተከተል ይጻፉ ግምታቸው ስህተት ያለበት ከሆነ ግን እርስዎ ጥቆማ በመስጠት ጉዳዩን ከገለጡላቸው በኋላ ወደ መጻፍ ተግባሩ ያስገቧቸው። ሲጽፉም እየተዘዋወሩ እርማትና ግብረመልስ ይስጧቸው።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት**

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

### ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-

- በጽሁፍ ውስጥ የአሁን ጊዜ አንጻርን ይለያሉ።

በሰዋስው ትምህርት ክፍል የቀረበው የትምህርት ይዘት ‹‹የአሁን ጊዜ የግስ አንጻርን መለየት›› የሚል ነው። እባክዎ መምህር የሚከተለውን አጭር ማስታወሻ መነሻ አድርገው ማብራሪያ ይስጧቸው። ለዚህ ርዕሰጉዳይ ተጨማሪ ምሳሌና ማብራሪያ የሚሰጥዎ የማጣቀሻ መፅሐፍ (ለምሳሌ፡ የባየ ይማምን ወይም የጌታሁን አማረን **የአማርኛ ሰዋስው** መጽሐፍ) በተጓዳኝ በመጠቀምም አጠር ያለ ማስታወሻ ይስጧቸው።

ለምሳሌ፡

የአሁን ጊዜ የግስ እንጻር፡ የተጠቀሰው ድርጊት አሁን የተፈጸመ ወይም እየተፈጸመ ያለ መሆኑን ያሳያል፤ ይህም ተናጋሪው እየተናገረ ባለበት ሰዓት ድርጊቱ እየተከናወነ ያለ መሆኑን ያመለክታል።

**ምሳሌ፡-**

ምሳዬን እየበላሁ ነው።

መኪናው ከአዲስ አበባ እየመጣ ነው።

መምህሩ ተማሪዎቹን እያስተማረ ነው።

ከዚያም መልመጃ ሶስትን ያሰሯቸው። መልመጃውን እንዲሰሩ ሲያደርጓቸው መልሶቻቸውን እየተቀበሉ ስህተት የሆነውን እያረሙ ጥያቄዎቹን እንዲያጠናቅቁ ያድርጉ። መልመጃዎቹም፡-

ሀ. ከቀረቡት አረፍተነገሮች በአሁን ጊዜ የግስ አንጻር የተመሰረቱትን አረፍተ ነገሮች መለየት

ለ. በአሁን ጊዜ የግስ አንጻር አረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ ማድረግ ናቸው።

## 4.ግምገማ

- በጥሞና አዳምጠው ምላሽ መስጠታቸውን ያረጋግጡ፡፤
- የስራ ስነምግባር ምንነት ጽንሰሀሳብን ማብራራታቸውን ይከታተሉ።
- አዳዲስ ሀሳቦችን በማሰስ አንቀጽ መጻፋቸውን ይከታተሉ።
- የስራ ስነምግባር ማሳያዎችን ማመልከታቸውን ይከታተሉ።
- የመጀመሪያ ቋንቋ ተገቢ መዋቅሮችን ተጠቅመው አንቀጽ መጻፋቸውን ያረጋግጡ።
- የጸሁፍ አጠቃላይ ሀሳብ ለማግኘት ማንበባቸውን ይጠይቋቸው፡፡
- በተለያዩ አውዶች ውስጥ ተዘውታሪ ቃላትን መጠቀማቸውን ይከታተሉ።
- በአረፍተነገር ውስጥ ባለቤትና ማሰሪያ አንቀጽ መለየታቸውን ይመልከቱ።

# 5 በምዕራፉ የተካተቱ ጥያቄዎች መልስ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

### ቅድመማዳመጥ

1. የሀረር ግንብ፣ የፋሲል ቤተመንግስት፣ የሼክ ሁሴን ዋሻ፣ ላሊበላ፣ የአክሱም ሀውልቶች…
2. ፎቶ ግራፉን አይተው የሚሰጡት የየራሳቸው ምላሾች

### የማዳመጥ ጊዜ

1. ታሪካዊ እና ባህላዊ 2. 2000 3. እንጨት

### የድህረማዳመጥ

#### መልመጃ አንድ

1. በኦሮሚያ ክልል ጅማ ዞን፣ ጅማ ከተማ 8 ኪ. ሜትሮች ወጣ ብሎ
2. የደቡብ ምእራብ ባህላዊ የቤት አሰራር እና የኢንዶ አረባዊ የኪነህንጻ ጥበብን አጣምሮ ያዘ ነው
3. ጠላትን ከሩቁ ለማየት የሚያመች መሆኑና ውሃ የማያቁር አካባቢ (ዳገታማ) በመሆኑ ለወባ ትንኞች መራባት አመቺ ስላልሆነ
4. በወቅቱ ከፉ ይባል የነበረውን የደቡብ ግዛት አካባቢንን መቆጣጠር በመቻሉ እና ከሰሜናዊ ሱማሊያ ዳርቻ ወደብ ጋር ትስስር ስለነበረውና በዚህም የህንድን ባህር ከሚሻገረው ዋነኛ የንግድ መስመር ጋር መገናኘቱ
5. የተለያዩ መልሶች (ከባህል አንጻር በወቅቱ የነበረውን ባህላዊ አለባበስ፣ አመጋገብና የተለያያዩ መገልገያ ቁሳቁሶችን ማቆየቱ፣ ከታሪክ አንጻር በወቅቱ ምን ምን ክስተቶች እንደነበሩ ማመላከቱ…

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

ተግባር ሁለት፣ ተግባር ሦስትና አራት በየትዕዛዛቱ መሰረት ይሰራሉ፤ የሚሰጡት መልሶችም በተማሪዎቹ አተያዮች ላይ የተመሰረቱ ይሆናሉ። ምክንያታዊ እስከሆነና ከየትዕዛዛቱ እስካላፈነገጠ ድረስ ማንኛውም ከጉዳዩ ጋር የተያያዘ ምላሽ ተቀባይነት ይኖረዋል።

## ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

### የቅደመንባብ ጥያቄዎች

1.ማንኛውም ምላሽ (ለምሳሌ፡-ለሀገር ሽማግሌዎች፣ለፖሊስ፣ ለወረዳ/ቀበሌ አስተዳደር…)

2. የተለያዩ ምላሾች (ሽምግልና፣ ጉማ፣ ሉኮ…)

3. የተለያዩ መልሶች

### የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች

1 የአፋንኦሮሞ

2. ሽነቻ እና የቦ

3. አምስት

4. ዘጠኝ

5. ካላመነ

6. ከ3 እስከ 5

7. የተለያዩ ግምቶች (ምላሹን ከተከታዩ የምንባብ ክፍል ያገኛሉ)

### የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

#### መልመጃ ሁለት /ሀ/

1. ያለ አግባብ ሀብት ለማካበት፤ በቅናት፤ በምቀኝነት፤ በቂም በቀል፤ በድንገት (በስህተት) ወዘተ
2. በህብረተሰብ ውስጥ ጥፋት ፈጽሟል ተብሎ የተጠረጠረ ሰው ወንጀሉን ሲክድ ያንን ለማጣራት ተግባራዊ የሚደረግበት ነው፡፡
3. አቤቱታ ማዳመጥ፣ ጥፋተኛውን መለየት፣ ቃለመሀላ ማስደረግ፣ ከቤተዘመድ ዋስ ማስጠራት (ሉከ ደበርፈዱ)፣ … መረጃ ላይ ተመስርቶ ውሳኔ መስጠት ወይም ተበዳይ እንዲካስ ማድረግ (በካሳ ወይም ያለ ካሳ ሊሆን ይችላል)
4. ከአካባቢው ራሱም እንዳይጠፋ (እንዳይሰወር) ወይም በንዴት ተነሳስቶ ሌላ ወንጀል እንዳይፈጽም
5. ዘመዳቸው የተጠረጠረበትን ጉዳይ ፈጽሞ ከሆነ እንዲያምንና ምክር ቤቱን ይቅርታ ጠይቆ የሚወሰንበትን ቅጣት እንዲቀበል ያደርጉታል።
6. መላው ህብረተሰብ ኃላፊነቱን እንዲወስድ ይደረጋል። ህብረተሰቡ ውስጡን ፈትሾ ሌላ የሚጠረጥረውን ሰው ለምክር ቤቱ ይጠቁማል። ምክር ቤቱ ሀቁን

ለማውጣት አዲስ በተጠረጠሩት ላይም የሌኮ ስሌቱን ይተገብራል።

7. አጥፊው የሚከፍለውን ካጣ እርዳታ ጠይቆ እንዲከፍል ባህሉ ይፈቅድለታል።
8. ጉማ ወይም የሰው ህይወት ካጠፋ ደግሞ ሂርጳ /እርዳታ/ ጠይቆ የሰው እጅ አይቶ፤ ተጸጽቶ፤ እርዳታ ሲጠይቅም “በእኔ የደረሰው አይድረስባችሁ” ብሎ መክፈል አለበት
9. ገንዘብ የሌለው ሰው ወንጀል ቢፈፅም እንኳን የምሰጠው ካሳ የለኝም ብሎ ወንጀሉን እንዳይደብቅ እና ተበዳዩ ያለካሣ እንዳይቀር ለማድረግ
10. እኔ አጥፍቻለሁ እናንተ ከኔ ተማሩ፤ የሰው ህይወት አታጥፉ፤ እኔ ተጸጽቻለሁ ለማለት ወንጀሉን አለመፈጸሙን ሲናገር (ሲክድ)

## ተግባር አምስት

ምንባቡን መሰረት አድርገው ስለሸነቻና የቦ ከጓደኞቻቸው ጋር ከተወያዩ በኋላ አስፋፍተው ሀሳባቸውን መልሰው ለክፍሉ ያቀርባሉ።

## ትምህርት አራት፡ ቃላት

### መልመጃ ሦስት

1. የሚደነግገው - የሚያወጣው
2. በረቀቀ - በማይታወቅ/ውስብስብ በሆነ
3. ትልቅ ቦታ አለው - ይከበራል/ዋጋ ይሰጠዋል
4. ቀልባቸው እያወቀ - እውነቱን እየተረዱ/ ውስጣቸው እያወቀ
5. ውስጡን ፈትሾ - አጣርቶ/ አባላቱን ገምግሞ
6. ሀቁን - እውነቱን/ ትክክለኛውን

**ለ.** 1. ሠ
2. መ
3. ሐ
4. ለ
5. ሀ

## ትምህርት አምስት፡ መጻፍ

ተግባር ስድስት (ሶስት አንቀጽ ያለው አመዛዛኝ ድርሰት መጻፍ) እና ተግባር ሰባትን (ስዕልን አንብቦ መግለጽ) በየትዕዛዛቱ መሰረት ይሰራሉ፤ የተለያዩ ስራዎችም ይቀርባሉ።

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

### መልመጃ አራት

**ሀ.** ተራ ቁጥር፡ 2፣ 3፣ 7፣ 8፣ 10

**ለ.**

1. ሰውዬው ሀኪም ቤት እየሄደ ነው።
2. እናቴ ገበያ እየሄደች ነው።
3. ጓደኞቼ የቤት ስራ እየሰሩ ናቸው፡፤
4. ቤተሰቦቼን ለመጎብኘት ወደ አዲስ አበባ እየሄደ ነው።
5. ወንድሜ በዲግሪ ተመርቆ ወደ ስራ እየገባ ነው።
6. ዜናው እየተላለፈ ነው።
7. ቶሎሳ ከእህቱ ጋር እያጠና ነው።
8. ጫልቱ ገበያ እየሄደች ነው።
9. ቀነኒሳ የማራቶን ሩጫ እያሸነፈ ነው።
10. ነጋሳ ትምህርቱን እያጠና ነው።

# ምዕራፍ ሶስት

# ሰብአዊ እሴቶች

(የክፍለጊዜ ብዛት 12)

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- አድምጠው ጽሁፍን ይገመግማሉ፤
- ከሌሎች ጋር ምልልስ ያከናውናሉ፤
- ጥምር ቃላትን በአውድ ይጠቀማሉ፤
- የነጠላ እና የብዙ ቁጥር ስሞችን ይለያሉ፤
- አራት አንቀጽ ያሉት ገምጋሚ አንቀጽ ይጽፋሉ።

## 2. የትምህርት ይዘት

### 2.1. ማዳመጥ

- የሚነበበውን ምንባብ ማዳመጥ
- ዝርዝርና ዋና ሀሳቦችን ለመለየት ማዳመጥ
- ምንባቡን መሰረት አድርገው የወጡ ጥያቄዎችን ለመመለስ ማዳመጥ
- በኢትዮጵያ ስርዓተ ጾታ ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ማዳመጥ

### 2.2. መናገር

- ስርዓተ ጾታ ላይ ተወያይቶ ንግግር ማድረግ
- ስለስርአተ ጾታ ጠይቀው ያገኙትን በቃል ማቅረብ
- በስርዓተ ጾታ ላይ የማጠቃለያ ንግግር ማድረግ
- የሀገራችን ስርአተ ጾታ ምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ መናገር
- የስርዓተ ጾታ አተገባበርን በማወዳደርና በማነጻጸር ገምግሞ መናገር
- ያከናወኑትን ቃለመጠይቅ በምልልስ ማቅረብ

### 2.3. ማንበብ

- ሰብአዊ እሴቶች በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ማንበብ
- ሰብአዊ እሴቶች የሚባሉት ምን ምን እንደሆኑ ማንበብ

- የሰብአዊ እሴቶች መከበር ለሰው ልጆች የሚያስገኛቸውን ጠቀሜታ ማንበብ
- የምንባቡን ዝርዝርና ዋና ሀሳቦች ለመለየት ማንበብ
- የቢጋር ሰንጠረዡን ለማሟላት ማንበብ

## 2.4. ቃላት

- ጥምር ቃል

## 2.5. መጻፍ

- አዳዲስ ሀሳቦች በመጠቀም አንድ አንቀጽ መጻፍ
- አራት አንቀጾች ያሉት አንድ ድርሰት መጻፍ
- የምንባቡን ፍሬ ሀሳብ በአንድ አንቀጽ መጻፍ

## 2.6. ሰዋስው

- ነጠላና ብዙ ቁጥር ቃላትን መለየት
- ነጠላ ቁጥር ቃላትን ወደ ብዙ ቁጥር ቃላት ማርባት

# 3. የማስተማሪያ ዘዴ

- የቀደመ እውቀታቸውን ተጠቅመው ስርዓተ ጾታ ምን ማለት እንደሆነ፣ ርዕሱን ተመልክተው ምንባቡ ስለምን እንደሚያወሳ እንዲናገሩ መቀስቀስ
- ተማሪን ማዕከል ያደረጉ የማስተማር ዘዴዎችን መተግበር።
- ከዝርዝር ወደአጠቃላይ ወይም ከአጠቃላይ ወደዝርዝር የማስተማሪያ ብልሐቶችን መጠቀም።
- ለቅድመ ማዳመጥ የቀረቡትን ጥያቄዎች አቅርቦ በቃል እንዲመልሱ ማድረግ
- የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎችን ማቅረብ
- ለአዳምጦ መረዳት የቀረበውን ጽሁፍ ሁለት ጊዜ እንዲያዳምጡ ማዘዝ
- የአዳምጦ መረዳትን ተግባራት ማቅረብ
- የመጻፍ መልመጃዎችን አቅርቦ ማለማመድ
- የንባብ ትምህርት አቀራረብን መተግበር
- በቅድመ ንባብ ወቅት የገመቱትን እንዲያረጋግጡ ማሳሰብ
- ያነበቡትን መሰረት አድርገው የተቀረው የምንባብ ክፍል ስለምን እንደሚያወሳ እንዲገምቱ ማድረግ

- ምንባቡን መሰረት አድርገው የወጡ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ማበረታታት
- ከክፍል ውጪ የሚሰሩ መስተጋብርን የሚፈጥሩ ተግባራትን እንዲሰሩ ማድረግ
- በአረፍተ ነገር ውስጥ ላሉ አዳዲስ ቃላት በምንባቡ ውስጥ ያላቸውን አውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ ፍንጭ መስጠት
- ሞዴል ሆኖ ማሳየትና ቀስ በቀስ ራን የማስቻል ስልትን መጠቀም
- ለቃላት ተመሳሳይ ትርጉም እንዲሰጡ መጠየቅ
- የስራ ላይ ስነምግባር በሚለው ምንባብ ውስጥ ያገኙትን አዳዲስ ሀሳቦች በአስተዋጽኦ መልክ ካደራጁ በኋላ አንቀጽ እንዲጽፉ ማበረታታት
- ሂደታዊ የአንቀጽ መጻፊያ ስልትን ተጠቅመው አራት አንቀጾች ያሉት ተራኪ ድርሰት እንዲጽፉ ማነሳሳት
- ጥምር ቃላትን ተጠቅመው ሀሳቦቻቸውን እንዲገልጹ ማድረግ
- ነጠላ ቁጥር ስሞችን ወደ ብዙ ቁጥር ቃላት እንዲቀይሩ ማነሳሳት

## 4.ግምገማ

- ያዳመጡትን መረዳታቸውን መጠየቅ
- የሰብአዊ እሴቶችን ጽንሰ ሀሳብ ማስረዳታቸውን መከታተል
- የሰብአዊ እሴቶችን ጽንሰ ሀሳብ መረዳታቸውን መለየት
- ነጠላ ቁጥር ቃላትን ወደ ብዙ ቁጥር ቃላት መቀየራቸውን ማረጋገጥ
- ያነበቡትን መረዳታቸውን መመዘን
- በተለያዩ አውዶች ውስጥ ያሉ አዳዲስ ቃላትን ለይተው በማውጣት አውዳዊ ፍቺ መስጠታቸውን ያረጋግጡ
- ለቃላት ተመሳሳይ ትርጉም መስጠታቸውን መከታተል
- ጥምር ቃላትን ተጠቅመው ሀሳቦቻቸውን መግለጻቸውን ይከታተሉ
- አንቀጽና ድርሰት መጻፋቸውን ያረጋግጡ
- ነጠላ ቁጥር ቃላትን ወደ ብዙ ቁጥር ቃላት መቀየራቸውን ያረጋግጡ።
- ጥምር ቃላትን ተጠቅመው ሀሳቦቻቸውን መግለጻቸውን ይከታተሉ፡

ክፍለጊዜ አንድ

# ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-**

- የተነበበውን ምንባብ አዳምጠው መልዕክቱን ይመዝናሉ።
- ከሌሎች ጋር ምልልስ ያከናውናሉ።

መምህር በዚህ ትምህርት ክፍል ተማሪዎችዎ ማዳመጥን በተግባር እንዲለማመዱ የሚደረግበት ነው። በመሆኑም እርስዎ ለማዳመጥ ተመርጦ የቀረበውን ምንባብ ቢያንስ ሁለት ጊዜ እንዲያነቡላቸው ይጠበቃል። ጽሑፉን ከማቅረብዎ በፊት ግን ተማሪዎቹ ለማዳመጥ ሂደቱ ዝግጁ ይሆኑ ዘንድ እንዲረዳቸው የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎቹን እንዲመልሱ ያድርጉ። የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎቹን ከሰራችሁ በኋላም የቀረበውን ጽሁፍ ለሁሉም ተደራሽ በሆነ የድምጽ መጠን ያንብቡላቸው። የመጀመሪያዎቹን ሁለት አንቀጾች ካነበቡላቸው በኋላም ማንበቡን ቆም አድርገው የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች ያቅርቡላቸው። ምላሻቸውን ከተቀበሉና ግብረመልስ ከሰጡበት በኋላ ቀጣዩን የጽሁፍ ክፍል ያቅርቡላቸው። በመጨረሻም አሳታፊ በሆነ መንገድ የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎቹን ያሰሯቸው። ይህ ከመከናወኑ በፊት ግን ጽሁፉን ቢያንስ አንድ ጊዜ ደግመው ያስደምጧቸው።

## ቅድመ ማዳመጥ

በትምህርት አንድ ስር የተማሪዎችን የማዳመጥ ፍላጎት የሚያነሳሱ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል። እነዚህም፡-

- በአካባቢያቸው ያለ ጾታን መሰረት ያደረገ የስራ ክፍፍል እንዲናገሩ
- በመገናኛ ብዙሃን የሚተላለፉ ስርዓተ ጾታ ተኮር ጉዳዮች አስታውሰው እንዲያብራሩ

## ሥርዓተ ፆታ

በኢትዮጵያ ውስጥ ስለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ሴቶች የተደረጉ ጥናቶች በእጅጉ ውስን ናቸው። ነገር ግን ብዙ አስተዋይ ኢትዮጵያውያን ሴቶች በህይወት ዘመናቸው ምን አይነት አስቸጋሪ ኑሮ እንደሚኖሩ አስተያየቶቻቸውን አቅርበዋል።

ኑሮን አስቸጋሪ ከሚያደርጉባቸው አድካሚ ሥራዎች መካከል በየዕለቱ ረጅም መንገድ እየተጓዙ እንጨትና ውሃ ማመላለስ፣ በእጅ መፍጨት፣ የቤት ውስጥ ሥራ ማከናወን፣ ልጆች መንከባከብ ይገኙበታል። በዚህና መሰል ምክንያቶች የተነሳም በትምህርት ጎልብተው ራሳቸውን በማጠናከር ረገድና በሥራ ቅጥር ላይ ከወንዶች ያነሰ ዕድል አላቸው፤ ምንም እንኳ አሁን አሁን መሻሻሎች እየታዩ ቢሆንም። መሻሻሎቹ ግን በአብዛኛው ማህበርሰብ ዘንድ ያለው የስርዓተ ጾታ አተያይ አድልዎ ያለበት በመሆኑ እምብዛም አጥጋቢ ናቸው ማለት አይቻልም።

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

**ማዳመጣቸውን ገታ አድርገው ቀደም ብለው ያዳመጡትን በማስታወስ የሚከተሉትን የማዳመጥ ጊዜ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ያድርጓቸው።**

- የኢትዮጵያን ሴቶች ኑሮ አስቸጋሪ የሚደርጉት ምን ምን እንደሆኑ
- ያዳመጡትን የጽሁፍ ክፍል መነሻ አድርገው የተቀረው የጽሁፉ ክፍል ምን ሊያወሳ እንደሚችል እንዲገምቱ ይጠይቋቸው።

በኢትዮጵያ ከሰማንያ አምስት በመቶ በላይ የሚሆኑት ሴቶች ከእጅ ወደ አፍ በሆነ የእርሻ ሥራ በሚተዳደሩ የአርሶ አደር ቤተሰቦች ውስጥ በገጠራማ አካባቢ እንደሚኖሩ ይነገራል። የገጠር ሴቶች ደግሞ ሰፊ የሰው ጉልበት በሚጠይቀውና ሕጻናትን ጨምሮ ሁሉም ሰው አድካሚ የጉልበት ሥራ ጥቅም ላይ በሚውልበት የገጠሩ የግብርና ስራ ላይ የተሰማሩ ናቸው። በዚህም የሴቶቹ ህይወት አጅግ አስቸጋሪ ከሆኑ ተግዳሮቶች ጋር የተቆራኘ ነው። ሥር በሰደደው የቆየ ባሕላዊ እምነት የተነሳ የመሬት ስሪት ማሻሻያውም የሴቶችን የተቀጢላነት ደረጃ አላሻሻለውም። ምክንያቱም ብዙ የእርሻ መሬቶች በባለቤትነት የተያዙት በወንዶቹ በመሆኑ ነው። ይህ በህግ አግባብ ቦታ ባይኖረውም፤ የቆየው ማህበረሰባዊ አተያይ ግን አሁንም አተያዩን ያሻሻለ አይመስልም። ሴቶችም እራሳቸው ማህበራዊ ፍትሁን በየኔነት ስሜት ተቀብለውት ይኖራሉ። ይሁን እንጂ ከዚህ ኢፍትሃዊ አሰራር መላቀቅ ለአጠቃላይ ማህበረሰባዊ እድገት ወሳኝ ይሆናል። እውነተኛውን ለውጥ ለማምጣት ግን በሴቶች እና ሴቶች በማህበረሰቡ ውስጥ ባላቸው የስራ ድርሻ ላይ ያለንን አመለካከት ወደ ተሻለ ደረጃ ማሸጋገርን ይጠይቃል።

ስለሆነም የኢትዮጵያ ሴቶች በግብርናው ዘርፍ ያላቸውን የጎላ ድርሻ አጠናክሮ ለመቀጠል በሌሎች ታዳጊ አገሮች እንደሚኖሩት ሴቶች ሁሉ አስፈላጊ የሆኑ የግብርና ሀብቶች ማለትም መሬት፣ እንስሳት፣ የእርሻ መሳሪያ፣ ጥሬ ገንዘብ፣ ዕውቀትና መረጃ የማግኘትና የመቆጣጠር ዕድላቸውን ከፍ ማድረግ ይገባል። ለዚህም ማህበረሰቡን ማንቃት፣ ማስተማርና ህጋዊ ማዕቀፎችን እያዘጋጁ መጠቀም ይገባል። ይህ ሳይሆንና ጉዳዩን በቸልታ የምናስቀጥለው ከሆነ በግብርና ውጤቶች ምርት ማሳደግና ሴቶች በገበያው ውስጥ ያላቸውን አስተዋጽዖ ወይም ሚና እንዳሳነስን እንቀጥላለን። በዚህም የምንመኘው ሁለንተናዊ ለውጥ ሳይሳካ ይቀራል።

## መልመጃ አንድ

በመልመጃ አንድ ተማሪዎች ያዳመጡትን መሰረት አድርገው የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃል መመለስን የሚጠይቅ ነው።  ሁለተኛው ያዳመጡትን መሰረት አድርገው ተጓድለው የቀረቡትን አረፍተነገሮችን ከቀረቡት ቃላት በመምረጥ የሚያሟሉበት ሲሆን፣ መምህር ተማሪዎቹ ደብተራቸው ላይ ጽፈው እንዲመልሱ ያድርጓቸው። መምህር እባክዎ ለሁሉም ጥያቄዎች ምሳሌ ይስሩላቸውና የተቀሩትን ተማሪዎች ትክክለኛ መልስ ከበቂ ምክንያታቸው ጋር እንዲመልሱ ያበረታቱዋቸው። ግብረ መልስም ይስጧቸው።

ተግባር አንድ

መምህር በአገራችን ኢትዮጵያ የሴቶችን ህይት ከማሻሻል/ከመለወጥ አንፃር መደረግ እንዳለበት የመፍትሄ ሀሳብ የሚሉትን እንዲያመነጩ ያበረታቷቸው፡፡ ሀሳብ ሲሰነዝሩም በተሰነዘሩት ሀሳቦች ላይ ሎሎች ሀሳባቸውን እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡

ክፍለጊዜ ሁለት

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

### ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-

- ከጓደኞቻቸው ጋር ውይይት ያደርጋሉ።

### ተግባር ሁለት

መምህር ተማሪዎችዎ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ አስቀድመው በተሰጡት ትዕዛዛት መሰረት ውይይት ያደርጋሉ፡፡ በውይይቱ ወቅትም ማስታወሻ መያዝ የሚጠበቅባቸው

ስለሚሆን ተፈጻሚነቱን እርስዎ ይከታተሉ። ውይይታቸውን ሲያጠናቅቁም የያዙትን ማስታወሻ መሰረት አድርገው ለክፍሉ የቃል ዘገባ ያቀርባሉ፤ አቀራረቡም በፍላጎት ወይም በቡድን ተወካይ አማካይነት ይሆናል።

**ክፍለጊዜ ሶስት**

### ተግባር ሶስት

የስነ ዜጋ መምህራቸውን ስለስርዓተ ጾታ ጠይቀው ወይም ከማህበራዊ ድረ-ገጽ አንብበው ያገኙትን በቡድን ሆነው ከተወያዩ በኋላ በቡድን ተወካያቸው አማካኝነት ሁሉም ቡድኖች እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው። እዚህ ላይ ለክርክር በር የሚከፍቱ ተጨማሪ ሀሳቦችን መምህር ሊያቀርቡላቸው ይችላሉ። (ለምሳሌ፡ ወንድ እንጀራ መጋገር፣ ወጥ መስራት የመሳሰሉ የቤት ስራዎችንም በመስራት ሴቶችን ከጓዳ ስራ ማላቀቅ ይገባዋል)

### ተግባር አራት

በተግባር ሶስት ከመምህር ጠይቀው ያገኙትን እንዲሁም የተለያዩ መፃህፍትን አንብበው ያገኙትን ሀሳብ በአካባቢያቸው ካለው ነባራዊ ሁኔታ አንፃር እየገመገሙ ሀሳብ እንዲሰጡ ያድርጓቸው።

**ክፍለጊዜ አራት**

# ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

### ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-

- የጽሁፍን ሀሳብ አንብበው ከራስ ጋር ያዋህዳሉ።

መምህር እባክዎ ተማሪዎችዎ ማንበብን በተግባር ይለማመዱት ዘንድ ዝግጅት አድርገው በንቃት ወደ ማንበብ ተግባሩ እንዲገቡ ያበረታቷቸው። የማንበብ ትምህርቱ በደረጃ ተከፋፍሎ የሚቀርብ ሲሆን በመግቢያው ክፍል የቅድመማንበብ ጥያቄዎችን፣ በማቅረቢያ ጊዜ ደግሞ ማንበብንና የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎችን እና በማጠቃለያው ክፍል የድህረ ማንበብ ጥያቄዎችን ያሰሯቸው።

### ቅድመ ንባብ

ተማሪዎች በቀጥታ ወደ ንባብ ከመግባታቸው በፊት ለማንበብ የተነሳሱ እንዲሆኑና የማንበብ አላማ እንዲይዙ የሚከተሉትን ተግባራት እንዲያከናውኑ ያድርጉ።

- ምን ምን ተግባራትን በመፈጸም አረጋውያን እንደሚያከብሩ
- አረጋውያንን ማክበር በልጆች የወደፊት ስነምግባር ላይ የሚኖረውን ጠቀሜታ ምን እንደሆነ እንዲናገሩ

ከዚያም ‹‹አረጋውያንን ማክበር›› በሚል የቀረበውን ምንባብ በትኩረት እንዲያነቡ ይዘዟቸው።

## የንባብ ጊዜ

ተማሪዎች የምንባቡን ሶስት አንቀጾች አንብበው ካጠናቀቁ በኋላ የንግግር አቅራቢው አላማ ምን እንደሆነና ቀሪው የምንባቡ ክፍል አረጋውያንን ስለማክበር ምን ምን ነጥቦችን ሊያነሳ እንደሚችል ንባባቸውን ገታ አድርገው እንዲገምቱ ያበረታቷቸው። ከዚያም ንባባቸውን እንዲቀጥሉ ይዘዟቸው።

## ድህረ ንባብ

### መልመጃ አንድ

በዚህ መልመጃ ተማሪዎች በምንባቡ የቀረቡ ሀሳቦችን መሰረት አድርገው ምላሽ የሚሰጡባቸው ጥያቄዎች ቀርበዋል። ለጥያቄዎቹ ምላሽ የሚሰጠው በጽሑፍ ሲሆን፣ ሲጨርሱ ምላሻቸውን እያነበቡ ለክፍሉ ያቀርባሉ። መምህር በዚህ ክፍለጊዜ ሁሉም ተማሪዎች አቅርበው ስለማይጨርሱ የተወሰኑ ተማሪዎችን በብድግ ብድግ እጣ ያሳትፏቸው፤ ግብረመልስም ይስጡ።

**ክፍለጊዜ አምስት**

## ተግባር አምስት

መምህር በተግባር አምስት ስር ሦስት ጥያቄዎች ቀርበዋል። የጥያቄዎቹ ምላሾች የሚሰጡት በወቅቱ የሚደረግ ውይይት መሰረት አድርጎ ሲሆን፣ ተማሪዎችዎ በውይይቱ ወቅት ማስታወሻ እንዲይዙ ማበረታታት ይጠበቅብዎታል። በማስከተልም የተያዘውን ማስታወሻ መነሻ በማድረግ ተማሪዎቹ አንቀጽ ጽፈው አንዱ ለሌላው ያነባል። በመጨረሻም እርስዎ የተማሪዎችን ደብተር ሰብስበው እርማት ይሰጡበታል፤ ይህ እንደሚሆን ግን እባክዎ መምህር ተማሪዎችዎን አስቀድመው ያሳውቋቸው።

## ተግባር ስድስት

መምህር በተግባር ስድስት ስር የተሰጠውን እንዲያከናውኑ እባክዎ አስቀድመው ምስሉን (አረጋዊያንን ስለማክበርና ስለሚኖረው ጠቀሜታ) መለማመጃ ደብተራቸው ላይ እንዲያሰፍሩ ይጠይቋቸው። በሳጥኖቹ ውስጥ የቀረቡትን መነሻ በማድረግም ቀሪዎቹን እንዲያሟሉ ያበረታቷቸው፤ እየተዘዋወሩም ምላሾቻቸውን ይመልከቱ። ተጨማሪ ድጋፍ ለሚሹትም ድጋፍ አድርጉላቸው።

**ክፍለጊዜ ስድስት**

# ትምህርት አራት፡ ቃላት

### ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-

- ሀሳባቸውን ለመግለጽ ጥምር ቃላትን ይጠቀማሉ።

## መልመጃ ሶስት

መምህር በዚህ መልመጃ ስር ከምንባብ የወጡ ቃላትና ሀረጋት ቀርበዋል። ተማሪዎችዎ አስቀድመው ቃላቱ በምንባቡ ውስጥ የያዙትን ፍቺ እንዲገምቱ ያድርጉ። በማስከተልም እነዚህኑ ቃላትና ሀረጋት እየተጠቀሙ የየራሳቸውን አረፍተነገሮች ይመስርቱ፤ ታዲያ አረፍተነገሮቻቸው ቃላቱ በምንባቡ ውስጥ ያላቸውን ፍቺ ሳይለቁ እንዲጠቀሟቸው ያሳስቧቸው። በመጨረሻም የተጻፉትን አረፍተነገሮች ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያጋሩና እርስዎም ምጋቤ ምላሽ የሚሰጡባቸው ይሁን።

## መልመጃ አራት

በማስከትል ስለጥምር ቃላት በተማሪዎቹ መጽሐፍት ውስጥ የቀረበውን ማስታወሻ መሰረት በማድረግ ጥምር ቃላት ምን እንደሆኑና እንዴት እንደሚመሰረቱ ለተማሪዎችዎ ገለጻ ያቅርቡ። በመቀጠልም በመልመጃ አራት ስር በሰንጠረዡ ከቀረቡት መካከል ጥምር ቃላት የሆኑትን እንዲለዩና ደብተራቸው ላይ እንዲጽፉ ያበረታቷቸው። መልሶቻቸውንም በምክንያት እያስደገፉችሁ በጋራ ተወያዩበት።

**ጥምር ቃል፡** ከአንድ በላይ ቃላት ተቀናጅተው አንድ ትርጉም /ፍቺ የሚሰጡበት ነው። ቃላት ተጣምረው የሚፈጥሩት አዲስ አሃድ (ቃል) ቀድሞ ተዋቃሪዎቹ በተናጠል ካላቸው ፍቺ የተለየ ፍቺ ይይዛል። እንደሌሎቹ ቃላትም ጥምር ቃሉ በራሱ መንገድ

ለተለያዩ እርባታዎች ቅርጹን ይቀያይራል። ለምሳሌ፡- ቁምሳጥን – ቁምሳጥኖች፣ ቁምሳጥኑ እየተባለ ቃሉን ማርባት ይቻላል።

ክፍለጊዜ ሰባት

## መልመጃ አምስት

መምህር ይህንን ማስታወሻ መነሻ አድርገው ስለጥምር ቃል ከነገሯቸው በኋላ ከቀረቡት ቃላት ጥምር ቃላት እንዲለዩ ያደርጉ። በመረጧቸው ጥምር ቃላትም አረፍተነገር እንዲመሰርቱ ያበረታቷቸው።

ክፍለጊዜ ስምንት

# ትምህርት አምስት፡ መጻፍ

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-**

- በስራ ስነምግባር ላይ አንቀጽ ይጽፋሉ።
- አራት አንቀጾች ያሉት ገምጋሚ ድርሰት ይጽፋሉ።
- ያገኙትን መረጃ በአንቀጽ አደራጅተው ይጽፋሉ።

## አንቀጽ መጻፍ

### ተግባር ሰባት

የዕለቱ ትምህርት አንቀጽ መጻፍ እንደሆነ በመግለጽ በምዕራፍ ሶስት ‹‹የስራ ላይ ስነምግባር›. በሚል ርዕስ በቀረበው ምንባብ ውስጥ ያሉትን ሀሳቦች ተጠቅመው አንቀጽ እንዲጽፉ ያድርጓቸው። በዚህ ጊዜም ይከታተሏቸው፣ ዕገዛም ያድርጉላቸው። በመቀጠልም "አረጋውያንን ማክበር" በሚል ርዕስ በቀረበ ጽሁፍ የአንቀጾችን ፍሬሀሳቦች በአስተዋጽኦ መልክ እንዲጽፉ ያድርጉ። የጻፉትን የአንቀጾችን ፍሬሀሳቦች መነሻ አድርገው የምንባቡን ፍሬ ሃሳብ የሚያሳይ አንቀጽ በመጻፍ ለእርስዎ እንዲያሣዩ ያድርጉ። ሲጽፉም ለአንቀጻቸው ዋና ዓረፍተነገር (ሀይለቃል) እንዲያመለክቱ ያድርጉ። የጻፉትንም በመሰብሰብና እርማት በማድረግ አስተያየት ይስጧቸው።

መምህር እባክዎ አስቀድመው በተግበር ስምንት ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች አስቀድመው ያንብቡና ተማሪዎቹ በቀጣዩ ክፍለጊዜ እነዚህን እንደሚከውኑና ለዚህም መረጃ አሰባስበው እንዲመጡ ያሳስቧቸው።

ክፍለጊዜ ዘጠኝ

# ድርሰት መጻፍ

## አራት አንቀጽ ያለው ገምጋሚ ድርሰት መጻፍ

### ተግባር ስምንት

መምህር በዛሬው ትምህርት ተማሪዎችዎ የመጻፍ እድል ተፈጥሮላቸው መጻፍን በተግባር የሚለማመዱበት ጊዜ ነው። በመሆኑም በቀደመው ክፍለጊዜ የተሰጣቸውን ማሳሰቢያ (መረጃ አጠናክሮ መምጣትን) ተከትለው የተሰጡትን ሁለት ተግባራት (ሀ እና ለ) እንዲያከናውኑ ያበረታቷቸው። ስራዎቻቸውን ሲያጠናቅቁም ከጎናቸው ካሉ ተማሪዎች ጋር እየተለዋወጡ እንዲናበቡ ያድርጓቸው። የመጻፍና የመገማገም ሂደቶቹንም በንቃት ይከታተሉ። አስፈላጊ በሆነበት ወቅትም ምጋቤ ምላሾች ይስጧቸው።

ክፍለጊዜ አስር

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡**

- ነጠላና የብዙ ቁጥር ቅርጾችን በአግባቡ ይጠቀማሉ።

### መልመጃ ስድስት

በሰዋስው ትምህርት ንዑስ ክፍል የቀረበው የትምህርት ይዘት ነጠላ ቁጥርና ብዙ ቁጥር ስሞች የሚል ነው ። በቅድሚያ ተማሪዎችን ስለነጠላና ብዙ ቁጥር ቃላት የሚያውቁትን እንዲናገሩ ያድርጉ። ቀጥሎም በተማሪው መማሪያ መጽሀፍ ላይ የቀረበውን አጭር ማስታወሻ መነሻ አድርገው ሰፋ ያለ ማብራሪያ ያድርጉላቸው። ማስታወሻውም፡

**ነጠላ ስም፡** በቁጥር አንድ የሆነ ስም ማለት ነው።

**ብዙ ስም፡** በቁጥር ከአንድ በላይ የሆነ ስም ነው። ምሳሌ፡

| ነጠላ ቁጥር ስም | ብዙ ቁጥር ስም |
|---|---|
| ተማሪ | ተማሪዎች |
| ወላጅ | ወላጆች |
| ሰው | ሰዎች |
| ቤት | ቤቶች |

ከዚያም የሚከተሉትን ጥያቄዎች ያሰሯቸው። መልመጃውን እንዲሰሩ ሲያደርጓቸው መልሶቻቸውን እየተቀበሉ ስህተት የሆነውን እያረሙ ጥያቄዎቹን እንዲያጠናቅቁ ያድርጉ። ጥያቄዎቹም

1. ከቀረቡት ቃላት ነጠላና ብዙ ቁጥር ስም በማለት ለይተው እንዲጽፉና
2. ነጠላ ቁጥር ስሞችን ወደ ብዙ ቁጥር ስሞች እንዲቀይሩና በተቀየሩት ብዙ ቁጥር ስሞችም አረፍተነገር እንዲመሰርቱ ማድረግ ናቸው።

**ክፍለጊዜ አስራ አንድ**

## መልመጃ ሰባት

እባክዎ መምህር በክፍለጊዜ አስር የቀረቡትን ማብራሪያዎችና መልመጃዎች መነሻ አድርገው በክፍለጊዜ አስራ አንድ ላይ በመልመጃ ሰባት ስር የቀረቡትን ስሞች ደብተራቸው ላይ በመጻፍ ወደ ብዙ ቁጥር እንዲመልሷቸው ያድርጉ። የበዙትን ስሞች በጋራ ከተመለከታችሁና ትክክለኛነታቸውን ካረጋገጣችሁ በኋላ ተማሪዎቹ በቃላቱ አረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ ይጋብዟቸው። በመጨረሻም እዚያው ክፍል ውስጥ እንደአጨራረስ ቅደምተከተላቸው ደብተሮቻቸውን እየተቀበሉ እርማት ይስጧቸው፤ በቀጣዩ ቀንም በክለሳ መልክ ስሞች እንዴት እንደሚበዙ ምሳሌዎችን በመስጠት ያቅርቡ።

**ክፍለጊዜ አስራ ሁለት**

# ቃላትን ማርባት

## መልመጃ ስምንት

በዚህ ክፍለጊዜ ተማሪዎች ነጠላ ቁጥር ቃላትን በድጋሚ እንዲለዩና የለዩአቸውን ነጠላ ቁጥር ቃላት ወደ ብዙ ቁጥር ቃላት እንዲለውጡ የሚጠየቁበት ነው። በመሆኑም ተማሪዎች መጀመሪያ ቢያንስ አስር ነጠላ ቃላትን (ስሞችን) ይጠይቋቸው።

በማስከተልም የጻፏቸውን ስሞችና ወደ ብዙ ቁጥር የረቡበትን ሁኔታ ጥንድ ጥንድ በመሆን እንዲናበቡ ይደረግ። በማስከተልም ወደ ብዙ ቁጥር የተቀየሩትን ስሞች በመጠቀም አረፍተነገሮች ጽፈው እንዲያቀርቡ ይዘዟቸው። መልሶቻቸው ላይም በጋራ ተወያዩ፤ ምጋቤ ምላሽም ገንቢ በሆነ ሁኔታ ይሰጣቸው።

# 5 የመልመጃ መልሶች

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

### የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

1. የተለያዩ መልሶች (ሊስትሮ - ለወንድ፣ የማድቤት ስራ - ለሴት፣ ገበያ ሄዶ መሸመት - ለሴት፣ ንግድና እርሻ- ለወንድ ወዘተ)
2. የተለያዩ መልሶች (ለምሳሌ፡- የስራ ማስታወቂያ ሲነገር ቅድሚያ ለሴቶች (ሴቶች እንዲያመለክቱ ይበረታታሉ) ወዘተ ማለቱ)

### የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

**ሀ. የተለያዩ ጥያቄዎችን በቃል መመለስ**

1. ብዙ አስተዋይ ኢትዮጵያውያን ሴቶች
2. የግብርና ስራዎች፣ ውኃ መቅዳት፣ እንጨት መልቀም፣ ልጅ ማሳደግ፣ ምግብ ማዘጋጀት…

**ለ. ዐረፍተነገሮችን ማሟላት**

1. ከእጅ ወደ አፍ
2. የተቆረጕ
3. የኃላ
4. ሰር የሰደደው
5. ማሸጋገርን
6. ዕድል
7. ሚና
8. ሁለንተናዊ

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

### ተግባር ሁለትና ተግባር ሦስት

ትዕዛዛቱን መሰረት ያደረጉ ተቀባይነት ያላቸውና የተማሪዎቹን የተለያዩ ልምዶች (ተጋልጦዎች) መሰረት ያደረጉ መልሶች ይጠበቃሉ።

# ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

## የቅድመማንበብ ጥያቄዎች

1. በእድሜ የገፉ ሰዎች፣ አዛውንቶች፣ የሌሎችን ድጋፍ በሚሹበት የእድሜ ክልል ያሉ ሰዎች
2. የተለያዩ መልሶች (ቅድሚያ መስጠት፣ መታዘዝ፣ በአክብሮት ማስተናገድ፣ የሚሉትን መስማት...)
3. የተለያዩ መልሶች (የህይወት ዑደትን ማስቀጠል፣ ማህበራዊ ደህንነትን ማስቀጠል፣ የቡራኬያቸው ተካፋይ መሆን...)

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. አረጋዊያንን የማክበር ጠቃሚነትን ማሳየት
2. ለአረጋዊያን ተገቢውን እንክብካቤና ጥበቃ ማድረግ
3. የተለያዩ መልሶች (የህይወት ዑደትን ማስቀጠል፣ ማህበራዊ ደህንነትን ማስቀጠል፣ የእውቀትና ልምዳቸው ተካፋይ መሆን...)

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት


**ሀ. በጽሁፍ የሚመለሱ የተለያዩ ጥያቄዎች**

1. በእድሜ የገፉ ሰዎች
2. ቅድሚያ በመስጠት፣ በመታዘዝ፣ በአክብሮት በማስተናገድ፣ የሚሉትን በመስማት፣ ተገቢውን እንክብካቤ በማድረግ...
3. አረጋዊያንን
4. ቅድሚያ ስንሰጥ፣ የአክብሮት ሰላምታ ስናቀርብ፣ ከመቀመጫችን በመነሳት አክብሮታችንን ስንገልጽ
5. ሁለቱም ደስተኞች፣ ሰላማዊና ጤናማ ይሆናሉ
6. ታናናሽን መውደድ ታላላቅን ደግሞ ማክበር ተገቢ መሆኑን
7. አረጋዊያንን መውደድና መንከባከብ
8. ተፈላጊና "ጠቃሚ ሰው ነኝ" የሚል ስሜት በውስጣቸው ይፈጠራል፤ ስለእኛ የወደፊት ተስፋ ርግጠኛ ይሆናሉ።

## ተግባር አምስት

ልዩልዩ መልሶች ሊቀርቡ ይችላሉ።

## ተግባር ስድስት




# ትምህርት አራት፡ ቃላት

### መልመጃ ሦስት

1. በወጣትነት
2. አዛውንት/አረጋዊያን
3. ከዳበረው/የትየለሌ ከሆነው
4. ያከማቹት/ያዳበሩት
5. ተግዳሮቶች/ችግሮች/መከራዎች
6. ተቀያይረውባቸዋል
7. ውድ/ብርቅ
8. ያልተነኩ
9. ስሜት/ተነሳስዖት

**(ከላይ ያሉትን ቃላት/ሀረጋት በመጠቀም የሚመሰረቱ የተለያዩ አረፍተነገሮች)**

### መልመጃ አራት

| | | | |
|---|---|---|---|
| የእንጨት አልጋ | ጥቁር ሰሌዳ | አሳት እራት | አርሶ አደር |
| ጥቅል ጎመን | ትምህርት ቤት | ሆድና ጀርባ | ብርድ ልብስ |
| ጥሩ ሰው | መልካም ሀሳብ | ሽክላ ሰሪ | ውሀ ወለድ |
| ጸረኤድስ | ብረት ድስት | ኪነጥበብ | አዋቂ ልጅ |

**(ከጠቆሩት በስተቀር ሁሉም መልስ ይሆናሉ)**

### መልመጃ አምስት

(ጥያቄ 1 እና 2) የተለያዩ ተቀባይነት ያላቸው መልሶች ሊሰጡ ይችላሉ።

# ትምህርት አምስት፡ መጻፍ

## ተግባር ሰባት እና ተግባር ስምንት

(የተለያዩ ተቀባይነት ያላቸው መልሶች በተማሪዎቹ ሊቀርቡ ይችላሉ፤ በትዕዛዙ መሰረት የተሰሩ መሆናቸውን ግን ማረጋገጥ ይገባል)

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

## መልመጃ ስድስት

### ነጠላ ስሞች

ምርት፣ መሬት፣ ጠረጴዛ፣ ልብስ

### ብዙ ቁጥር ስሞች

ሀገራት፣ ነጋዴዎች፣ አናብስት፣ አእዋፍ፣ ዶሮዎች፣ ባለሞያዎች፣ ወረቀቶች፣ ጥያቄዎች፣ ክፍሎች፣ እንስሳት፣ ምግቦች፣ ሰዎች

## መልመጃ ሰባት 1.

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀረጋት/ሀረጎች | መንግስታት/መንግስቶች | አልባሳት/ልብሶች | ደብተሮች |
| ፈተናዎች | ቃላት/ቃሎች | አድባራት/አድባሮች | |
| ጨዋታዎች | ፈረሶች | ቤተሰቦች | |

**በነዚህ ቃላት የተመሰረቱ ተቀባይነት ያላቸው የተለያዩ አረፍተነገሮች**

**2. በተማሪዎች የሚቀርቡ የተለያዩ መልሶች**

# ምዕራፍ አራት

# አጭር ልቦለድ

(የክፍለጊዜ ብዛት 18)

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

**ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-**

- አዳምጠው ተመሳሳይ ታሪኮችን ይናገራሉ፣
- የአጭር ልቦለድ ጽንሰ ሀሳብን ያብራራሉ፣
- በጽሁፋዊ ቅርፅ ውስጥ አውዳዊ እና ተዘውታሪ ያልሆኑ ይጠቀማሉ፣
- የሀረጋት አይነቶችን ይለያሉ።

## 2. የትምህርት ይዘት

### 2.1 ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

- የሚነበበውን አጭር ልቦለድ ማዳመጥ
- የአጭር ልቦለድ አላባውያንን ለመለየት ማዳመጥ
- የአጭር ልቦለድ ታሪክ የተፈጸመው መቼ እንደሆነ ለመለየት ማዳመጥ
- ምንባቡን መሰረት አድርገው የወጡ ጥያቄዎችን ለመመለስ ማዳመጥ
- በአጭር ልቦለድ ውስጥ ያሉ ግጭቶችን ለመለየት ማዳመጥ

### 2.2 መናገር

- የአጭር ልቦለድ ታሪክን መልሶ በቃል መናገር
- እንደገገርና ሻጭ ሆኖ ሚና መጫወት
- የአረፍተነገሮችን ፍቺ መናገር
- ተወያይተው ያገኙትን መናገር

### 2.3 ማንበብ

- "ክቡር ውርስ" የሚለውን አጭር ልቦለድ ማንበብ
- የአጭር ልቦለድ ዋና ዋና ባለታሪኮችን ለመለየት ማንበብ

- ለመረዳት ማንበብ

## 2.4 ቃላት

- የቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍቺ
- ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላት ፍቺ
- ተዘውታሪ ባልሆኑ ቃላት ዓረፍተነገር መመስረት

## 2.5 መጻፍ

- መሸጋገሪያ ቃላትን ተጠቅሞ አረፍተነገር መጻፍ

## 2.6 ሰዋስው

- በሀረጎች አረፍተ ነገር መመስረት
- ሀረጎችን መለየት

# 3. የማስተማሪያ ዘዴ

- የአጭር ልቦለድ አላባውያንን እንዲለዩ ማበረታታት
- የአጭር ልቦለድ ታሪክ የተፈጸመው መቼ እንደሆነ አዳምጠው እንዲለዩ መጠየቅ
- በአጭር ልቦለድ ውስጥ ያሉ ግጭቶችን አዳምጠው እንዲለዩ ፍንጭ መስጠት
- የአጭር ልቦለድ ታሪክን እንዲተርኩ ምሳሌ ማቅረብ
- በአጭር ልቦለዱ ውስጥ የተፈጸሙ ተግባራትን ቅደምተከተል አስይዘው በቃል እንዲናገሩ ማበረታታት
- ስላነበቡት አጭር ልቦለድ እንዲናገሩ ማትጋት
- የቃላትን ፍቺ አንብበው እንዲለዩ ምሳሌ መስጠት
- ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላትን ፍቺ ከአውድ አንብበው እንዲረዱ ምሳሌ ማሳየት
- መሸጋገሪያ ቃላትን ተጠቅሞ አረፍተነገር እንዲመሰርቱ ማድረግ
- በሀረጎች አረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ ማድረግ
- ከአረፍተነገሮች ውስጥ ሀረጎችን እንዲለዩ ማበረታታት

ክፍለጊዜ አንድ

# ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

## ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡

- አዳምጠው ተመሳሳይ ታሪኮችን ይናገራሉ።

መምህር በትምህርት አንድ ስር የተማሪዎችን የማዳመጥ ፍላጎት የሚያነሳሱና ከአጭር ልቦለድ ጋር የሚያስተዋውቋቸው የተለያዩ ተግባራት ቀርበዋል። በዚህም ተማሪዎቹ **አፋልጉኝ** በሚል ርዕስ የሚያነቡላቸውን ምንባብ ያዳምጣሉ፤ ከማዳመጣቸው በፊት፣ በማዳመጥ ጊዜና ካዳመጡ በኋላም የተለያዩ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ። ስለሆነም በመጀመሪያ በቅድመማዳመጥ ደረጃ የቀረቡትን ሁለት ጥያቄዎች (አጭር ልቦለድ አንብበው ያውቁ እንደሆነና ስላነበቡት አጭር ልቦለድ የሚያስታውሱትን) እንዲመልሱ ያድርጉ። ቀጥሎም በማንበብ ጊዜ ተግባሩ የቀረቡ ጥያቄዎችን ያሰሯቸውና ማንበቡን ካቆሙበት ይቀጥሉ፤ ምንባቡ ቢያንስ ሁለት ጊዜ እንደሚነበብ ልብ ይበሉ። በመጨረሻም ከምንባቡ የወጡ የድህረማንበብ ጥያቄዎች እንደየትዕዛዛቸው እንዲመልሱ ያድርጉ።

**ቅድመ ማዳመጥ**

1. አጭር ልቦለድ ምን አይነት ልቦለድ ነው?
2. አጭር ልቦለድ አንብባችሁ ታውቃላችሁ? መልሳችሁ አዎ ከሆነ የአጭር ልቦለዱን ታሪክ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በአጭሩ ንገሩ?

መምህር ቅድመ ማንበብ ጥያቄዎቹን ከተማሪዎችዎ ጋር በመሆን ከሰራችሁ በኋላ ቀጣዩን ምንባብ በተለያየ ፍጥነት ድምጽዎትን እያሰሙ ያንብቡላቸው (በመጀመሪያው ንባብ ዝግ ብለውና በሁለተኛው በመደበኛው አነባበብ (ትንሽ ፈጠን ብለው)።

# አፋልጉኝ

ወርሃ ሰኔ ላይ አስቀድሞ የሚደርሰው የዲንሾ የመስኖ በቆሎ እሸት በዚህ ወቅት በየመንገዱ ዳር እየተጠበሰ ይሸጣል። ቤቱ ወስዶ መጥበስ ለሚፈልግም እንዲሁ በየመንገዱ ዳር የጉልት ገበያ እሸት በቆሎ ተከምሮ የገኘ ያለህ ይላል። በቆሎ ሻጮች ለአላፊ አግዳሚው፣ “አለች እሸት... እሸት እሸት ቀመሱ፤ ጋሼ ጣፋጭ እሸት ነው”

በማለት ከማሻሻጣቸው ሌላ፣ የሚጠበሰው በቆሎ እንደ ርችት፣ "ደሽ... ደሽ... ደሽ ደሽ..." እያለ በራሱ ገኸ ይጠራል።

"እቴ የበቆሎውን እሸት ስንት ስንት እያልሽው ነው?" አልኳት የተጠቀለለውን የበቆሎ እሸት ለመምረጥ ሸብረክ ብዬ ቁጭ እያልኩ። ከመብራት ምሰሶ ጥግ በቆሎ እሸት የሚሸጡት ሴት በዕድሜ የገፉ አዛውንት መሆናቸውን ልብ አላልሁም ነበር።

**የንባብ ጊዜ**

**በመቀጠልም እስከአሁን ባዳመጡት የአጭር ልቦለድ ክፍል ውስጥ ገጸባህርያት እነማን እንደሆኑ፣ ታሪኩ የተፈጸመው በምን አይነት የአየር ፀባይ አካባቢ እንደሆነ ጠይቀው የተቀረውን የአጭር ልቦለዱን ክፍል ያንብቡላቸው። በትኩረትም እንዲዳምጡ ይንገሯቸው።**

1. ባዳመጣችሁት አጭር ልቦለድ ውስጥ ገጸባህርያት እነማን ናቸው?
2. ታሪኩ የተፈጸመው በምን አይነት የአየር ፀባይ ውስጥ ነው?

"ይቅርታ የእኔ እናት እንደ ልጅ እግር ቆጥሬ አንጠልጥየ ጠራሁዎት" አልሁ ለድፍረቴ ይቅርታ እንዲያደርጉልኝ በማሰብ።

"ግዴለም የኔ ልጅ ከገዛኸኝ ይበቃኛል። ከዚህ ወዲያ ማክበር አለ ብለህ ነው! በዚህ ውሽንፍር ገዝቶኝ ከሚሄድ ሰው ሌላ አክባሪ አይኖረኝም። ደግሞ ጥሩ የባህር እሸት በመስኖ የበቀለ ትኩስ እሸት ነው። ጣፋጭ ነው በኔ ይሁንብህ።"

የሴትዮዋ "እባክህን ግዛኝ" የሚለው ተማፅኖ በቆሎ እሸቱን ሳልገዛቸው እንዳልሄድ ቀፍድዶ አሰረኝ።

"እና ሶስቱን ስንት እያሉት ነው?" "ይኸው ሶስቱ እነዚህ በአንድ ላይ የታሰሩት አስር ብር ነው የሚሸጡት።"

"ስድስቱ ሃያ ብር ማለት ነው?" "መሆኑ ነው። ስድስት ከገዛኸኝማ ምን ቀረኝ ብለህ ነው። ብዙ ገዛኸኝ ማለት ነው እኮ የኔ ልጅ።"
"ለነገሩ ለነገም ልግዛ ብዬ ነው እንጅ ለዛሬማ ሶስቱ በቂ ነው፤ ለእኔና ለሚስቴ።"
"ግዴለህም ለነገ ማለት መልካም ነው የኔ ልጅ።" አሉ።
"ቢሆንም ከሰነበተ ደግሞ ይደርቃል፣ እሸትነቱ ይጠፋል።"

“ሸለፈቱን አትግለጠው እንጅ አይደርቅም።” “እርስዎ ካሉ መልካም ልግዛዎት የእኔ እናት።

ቀጠሉና በስሜት “ተባረክ፣ ብርሀ እንደዚህ በቆሎ ይንሾርቀቅ። ይኸን ወጀብ የፈጠረ፣ ይኸን ባለግርማ ደመና እንዲህ እንደተራራ የቆለለው አምላክ ይርዳህ። የመጨረሻውን ዕድሜህን የተሻለ ያድርግልህ።” በማለት ምርቃቱን ደረደሩት።

https://taza.debreyaredpublisher.com/

**ድህረ ማዳመጥ**

## መልመጃ አንድ

ተማሪዎች ያዳመጡትን የአጭር ልቦለዱን ክፍል መሰረት አድርገው የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃል ይመልሳሉ። መምህር እባክዎ ሁሉንም ጥያቄዎች ተማሪዎች ትክክለኛ መልስ ከበቂ ምክንያታቸው ጋር እንዲመልሱ ያበረታቷቸው። ግብረ መልስም ይሥጧቸው።

**ክፍለጊዜ ሁለት**

## ተግባር አንድ

መምህር ሰዎች በኑሮ ውጣ ውረድ ውስጥ በበርካታ ነገሮች ሊፈተኑ ይችላሉ። ይህ የማይቀር የህይወት ዑደት ነው። ስለሆነም ተማሪዎች ወደፊት በሚኖሩት ህይወት ተግዳሮት ሊገጥማቸው እንደሚችል አምነው ከወዲሁ ስነልቦናዊ ዝግጅት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። አንደኛው እቅዳቸው ባይሳካላቸው ያንን በጸጋ እንዲቀበሉና ሌላኛውን የህይወት አማራጭ እንዲቃኙ ልምድ ሊጋሩ ይገባል። ስለሆነም በተግባር አንድ ስር እንደተጠቆመው በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሆነው ኑሮን ለማሸነፍ የሚፍጨረጨሩ ሰዎች የሚገጥሟቸውን ችግሮች እንዴት ሊወጡ እንደሚችሉ ተማሪዎቹ አማራጭ መፍትሄዎችን በማቅረብ የሀሳብ ድጋፍ እንዲያደርጉ ተጠይቀዋል። መምህር እባክዎ ተማሪዎችን በአነስተኛ ቡድን በማደራጀት በአካባቢያቸው የህይወት ውጣ ውረድ ያለባቸው ሰዎች ምን ምን ተግዳሮቶች እንደሚገጥማቸው እንዲዘረዝሩ ያድርጉ፤ ለዘረዘሯቸው ተግዳሮቶችም የመፍትሄ ሀሳብ እንዲጠቁሙ ያበረታቷቸው (እነሱ ቢሆኑ ምን ያደርጋሉ?)።

**ክፍለጊዜ ሶስት**

## ተግባር ሁለት

መምህር በተግባር ሁለት ተማሪዎችዎ በማዳመጥ ተግባር ስር ያዳመጡትን ምንባብ ዋና ዋና ክንውኖች በማስታወስ የሚጽፉበትና ስለክንውኖቹም የሚናገሩበት ነው። ስለሆነም ተማሪዎች መለማመጃ ደብተራቸውን እንዲያዘጋጁ ያድርጉ፤ በመቀጠልም አዳምጠውት የነበረውን ታሪክ አበይት ክንውኖች በቅደም ተከተል እንዲያሰፍሩ ያበረታቷቸው፤ የጻፉትንም ለቡድን ጓደኞቻቸው (ተራ በተራ) እንዲያቀርቡ ያበረታቱ።

**ክፍለጊዜ አራት**

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-**

- የአጭር ልቦለድ ጽንሰሀሳብን ያብራራሉ።
- የአጭር ልቦለድ ታሪክን ይተርካሉ።
- የአጭር ልቦለድ አላባውያንን ያስረዳሉ።

## ተግባር ሶስት

መምህር በዛሬው ክፍለጊዜ ተማሪዎች የገገርና ሻጭ ሚናን ተላብሰው አስቀድመው በመለማመድ ምልልሱን በክፍል ውስጥ የሚያቀርቡበት ነው። ስለሆነም እርስዎ ያለፈውን ክፍለጊዜ ከከለሱላቸው በኋላ በእለቱ ትምህርት ደግሞ ምንምን እንደሚያከናውኑ ይንገሯቸው (የእለቱ ትምህርት መናገርን የሚለማመዱበት ስለመሆኑ፣ በዚህም አብዩ ጉዳይ ገዥና ሻጭ በመሆን ሚና የሚጫወቱ መሆኑን፣ ለዚህም ቅድመዝግጅት ማስፈለጉን፣ ምልልሱን (የገገርና ሻጭ) ከ5-7 ደቂቃ ወስደው በወረቀት ላይ እንዲያሰፍሩ፣ (ለምሳሌ መግዛት የፈለጉት አዲስ ሞባይል ነው እንበል፤ ሻጭ ስለሞባይሉ ጥራት፣ ሲመጣ ስለተከፈለበት ዋጋ…ገገር ስለዋጋው ክርክር) ወዘተ)። በመጨረሻም የጻፉትን ምልልስ ለተወሰነ ጊዜ አጥንተው ለክፍሉ ያቅርቡ፤ በአቅርቦት ወቅት ምልልሱ እንዳይጠፋባቸው የጻፉትን መልከት ማድረግ ይችላሉ። መምህር ሁሉንም አቅራቢዎች አመስግነው ተማሪዎች ይበልጥ የተሻለ ነው ያሉትን ጥንድ አቅራቢዎች እንዲመርጡ በማድረግና የእለቱ አሸናፊዎችን በማወጅ ትምህርቱን ማጠናቀቅ ይችላሉ። በቀጣዩ ክፍለጊዜም አንድ አጭር ልቦለድ አንብበው ታሪኩን

በክፍል ውስጥ በቃል የሚያቀርቡ መሆኑን ይጠቁሟቸው። ለዚህም በአማራጭነት እርስዎ ያዘጋጁላቸው የልብወለድ መጽሐፍ ካለ መጠቀምና ወይም በቤተመጽሐፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ አስቀድመው ማመቻቸትዎን አይርሱ።

**ክፍለጊዜ አምስት**

## ተግባር አራት

መምህር ባለፈው ክፍለጊዜ ተማሪዎች በሚና ጨዋታ መልክ ንግግርን ሲለማመዱ እንደነበር አስታውሰው፣ ቀደም ሲል የሰጧቸውን ጥቆማ (አጭር ልቦለድ አንብቦ የመምጣት) መሰረት አድርገው ደግሞ በክፍል ውስጥ ስለተነበበ ታሪክ አቅርቦት እንደሚያደርጉ ያስተዋውቋቸው። ልቦለድ ታሪክን መልሶ የመናገሩ ተግባር በግል ወይም ጥንድ ጥንድ በመሆን ተካፍለው ሊሆን ይችላል። በአቅርቦት ወቅትም ባለታሪኮቹ እነማን እንደሆኑና ምን አይነት ባህሪ እንደተላበሱም እንዲናገሩ ያበረታቷቸው። አቅራቢዎቹ የተመጣጠነ ጊዜ ያገኙ ዘንድ የማቅረቢያ ደቂቃውን ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ያደላድሏቸው።

**ክፍለጊዜ ስድስት**

## ተግባር አምስት

እንደምን አሉ መምህር! በዛሬው ክፍለጊዜ መሰረታዊ ክሂሎችን እያጣመሩ ለመሄድ ያመች ዘንድ የተዘጋጀ አጭር ታሪክ በምንባብ መልክ በተማሪዎቹ መጽሐፍ ላይ ሰፍሯል። በመሆኑም ተማሪዎችዎ ታሪኩን በማንበብና ካነበቡ በኋላ መጽሐፋቸውን በመዝጋት መልሰው በማስታወስ እንዲናገሩ ያበረታቷቸው። ይህም በሚደራጀው አነስተኛ ቡድን አማካኝነት የሚከናወን ነው፡፡ (4 ወይም 5 አባላት ያሉት ቡድን)። እርስዎ እንደተለመደው ክፍለጊዜው የመግቢያ፣ የማቅረቢያና የመደምደሚያ ክፍል እንዲኖረው አድርገው ያዘጋጁት። በምዘናውም ቡድኑና አባላቱ ያላቸውን አፈጻጸም እያዩ በነጥብ መመዝገቢያ ወረቀትዎ ላይ በምልከታ ወቅት ያስፍሩ።

**ክፍለጊዜ ሰባት**

## ተግባር ስድስት

ሀ. ተማሪዎችዎ ባለፈው ክፍለ ጊዜ ያነበቡትን ታሪክ እያስታወሱ መልሰው እንዲጽፉትና የጻፉትንም ለክፍል ጓደኞቻቸው መልሰው የሚያነበቡት ነው። ስለሆነም መምህር በተማሪዎችዎ ዘንድ መሰላቸት እንዳይፈጠር ታሪኩን መልሶ መጻፉ በምክንያት እንደሆነ (የማስታወስ ችሎታን ለማጎልበትና የመጻፍ ክሂልን ለማሻሻል

መሆኑን) በመንገር በንቃት እንዲሳተፉ ያትጓቸው። በዚህም ለመጻፊያና ለማቅረቢያ የሚሆን ደቂቃ በመመደብ በትኩረት እንዲሰሩ ያሳስቧቸው። እየተዘዋወሩም አፈጻጸሙን ይመልከቱ፡ ምዘናም ያካሂዱ።

ክፍለጊዜ ስምንት

# የአጭር ልቦለድ ምንነትና ባህርያት

## መልመጃ ሁለት

ለ. መምህር የዕለቱ ትምህርት **የአጭር ልቦለድ ምንነትና ባህርያትን የተመለከተ እንደሆነ ይግለጹላቸው።** ከዚያም በመማሪያ መጻፋቸው ላይ ስለአጭር ልቦለድ አላባውያን የቀረበውን ማስታወሻ አንብበው ባገኙት ሀሳብ ላይ በቡድን እንዲወያዩ ሁኔታዎችን ያመቻቹ። ማስታወሻውንም መነሻ አድርገው የቀረቡ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያትጓቸው።ግብረ መልስም ይስጧቸው። የመግቢያ፣ የማቅረቢያና የመደምደሚያ ደረጃ ያለው ክፍለጊዜ እንደሆነም አስቀድመው ምን ምን ተግባራትን እንደሚከውኑ ማቀድዎን አይርሱ፤ ይህንን በዕለታዊ ትምህርት እቅድዎ ቅጽ ላይ የተማሪና የመምህር ሚናን ለይተው በማስፈር ያመልክቱ።

ክፍለጊዜ ዘጠኝ

## ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

### ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-

- አጭር ልቦለድን ያነባሉ።
- አንብበው አዳዲስ ዘይቤያዊ አገላለጾችን ይለያሉ።

መምህር የማንበብን ክሂል በዋነኝነት ትኩረቱ ያደረገው ትምህርት በዚህ ክፍል ይቀርባል። የማንበብ ክሂል ደግሞ ሊጎለብት የሚችለው በማንበብ ነው። የክፍል ውስጥ ማንበብ እንደመነሻ የሚያገለግል እንጂ በራሱ ምሉዕ አይደለም፤ ስለሆነም መምህር ተማሪዎችዎ ይህንን አጠቃላይ ህይወታቸውን የሚመሩበትን ክሂል (ሌሎች የትምህርት አይነቶችንም ለመካን እጅግ ወሳኝ ነው) እንዲያጎለብቱ ከክፍል ውጪ ባለው አለም ማንበብን ሆነኝ ብለው ደጋግመው እንዲከውኑት በአጽንዎት ይምከሯቸው።

መምህር ተማሪዎችዎ የቅድመማንበብ ጥያቄዎችን ከሰሩ በኋላ የቀረበላቸውን **ክቡር ውርስ** የተሰኘ ምንባብ እንዲያነብቡ ያድርጓቸው፤ በማንበብ ወቅትም የቀረቡትን

የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች ይስሩ። አንብበው ሲጨርሱም መልሰው ምንባቡን እያዩ የድህረማንበብ ጥያቄዎቹን (**መልመጃ** 2) በጽሑፍ እንዲመልሱ ያበረታቷቸው። አፈጻጸሙንም እየተዘዋወሩ ይመልከቱ። በእለቱ ጥያቄዎቹን መልሰው ካልጨረሱም በአማራጭነት በየቤት ስራ መልክ ሰርተው እንዲመጡና ሲመጡም እርስዎ ደብተሮቻቸውን ሰብስበው በማረምና ምጋቤ ምላሽ በመስጠት ማስኬድ ይችላሉ።

**ክፍለጊዜ አስር**

## ተግባር ሰባት

ውድ መምህር ተማሪዎችዎ በዚህ ተግባር የነቃ ተሳትፎ ይኖራቸው ዘንድ የእለቱ ትምህርት አላማ አስቀድሞ የተነበበ ታሪክ ላይ ውይይት እያደረጉ ጥያቄዎችን በመመለስ የመናገርና የማዳመጥ ክህሎትን ለመካን መሆኑን በማስተዋወቅ ይጀምሩ። በዚህም በቀደመው ክፍለጊዜ ያነበቡትን ምንባብ መልሰው አንድ ጊዜ እንዲያነቡ ያድርጉ ወይም ተገቢውን አገላለጽ ተጠቅመው እርስዎ ያንብቡላቸው። ከዚያም የቀረቡላቸውን ሦስት ጥያቄዎች በትዕዛዙ መሰረት ይስሩ።

**ክፍለጊዜ አስራ አንድ**

## መልመጃ ሶስት

**ሀ.** ይህ መልመጃ በአንድ ታሪክ ውስጥ የተፈጸሙ ሁነቶችን በቅደም ተከተል ማስፈርን ለመለማመጃነት የተዘጋጀ ነው። በአዕምሯችን ውስጥ መረጃ በየፈርጁ ይደራጃል። መረጃ ከሚደራጅበት መንገድ አንዱ ደግሞ የአፈጻጸም ቅደም ተከተል ነው። ስለሆነም ተማሪዎችዎ በይፋ ይህንን እንዲለማመዱ እድል ስለሚሰጣቸው ተግባሩን በንቃት እንዲያከናውኑ ያሳስቧቸው። የእለቱን ትምህርትም ማነቃቂያ ቀልድ እርስዎ ወይም ተማሪዎችዎ ካላቸው እንዲናገሩ በማድረግ ማስጀመር ይችላሉ። ክስተቶቹን በቅደም ተከተል በየግላቸው ካስቀመጡ በኋላ በአንስተኛ ቡድን በመሆን እርስበርስ እንዲገማገሙ በማድረግ በመጨረሻ የተስማሙበትን በቡድን ተወካያቸው አማካኝነት ለክፍሉ እንዲያቀርቡ ይሁን።

**ክፍለጊዜ አስራ ሁለት**

**ለ.** በዚህ ክፍለጊዜ ከምንባቡ የወጡ ስድስት አረፍተነገሮች ቀርበዋል። መምህር ተማሪዎችዎ እነዚህን አረፍተነገሮች ደብተራቸው ላይ በማስፈር የያዙት መልዕክት ምን እንደሆነ በራሳቸው አባባል እንዲጽፉ ያድርጉ። እንደአጨራረስ ቅደም ተከተላቸውም ደብተሮቻቸውን እየተቀበሉ እርማት ያድርጉበት፤ በዚህም ወቅት ቀደም ሲል ሲያከናውኑ የነበሯቸውን ተግባራት (ማስታወሻ መያዝና መልመጃዎችን መስራት) ከደብተራቸው ላይ እያዩ መሄድ ይችላሉ። ወቅታዊ ግብረመልስም ይስጧቸው።

**ክፍለጊዜ አስራ ሦስት**

# ትምህርት አራት፡ ቃላት

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-**

- ለቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍቺ ይሰጣሉ፤
- ለተለያዩ አላማዎች ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላትን ይጠቀማሉ።

## መልመጃ አራት (ሀ እና ለ)

በዚህ መልመጃ የቀረቡት ተግባራት ሁለት ሲሆኑ የመጀመሪያው ከምንባቡ በወጡ አረፍተነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍቺ መስጠት ነው። ሁለተኛው ደግሞ ለቃላት መዝገበቃላዊ ፍች መፈለግን የተመለከተ ነው። ስለሆነም እባክዎ መምህር የዕለቱ ትምህርት የቃላት አውዳዊና መዝገበቃላዊ ፍቺን የተመለከተ እንደሆነ በመግለጽ አረፍተነገሮቹንና ቃላቱን ደብተራቸው ላይ ጽፈው በትዕዛዛቱ መሰረት እንዲሰሯቸው ያበረታቷቸው፤ መልሶቻቸውንም ይቀበሏቸው። እንደክፍልም በጋራ ተነጋገሩባቸው።

**ክፍለጊዜ አስራ አራት**

## መልመጃ አምስት

በዚህ ክፍለ ግዜ የቀረበው መልመጃ በአረፍተነገር ውስጥ የተሰመረባቸው ቃላት በአረፍተነገሩ ውስጥ ያላቸውን አውዳዊ ፍቺ እንዲለዩ የሚጠይቅ ነው፡፡ ይህም በክፍለ

**ግዜ አስራ አራት የቀረበውን ትምህርት የሚያጠናክር ነው፡፡ ስለዚህ መልመጃውን በግል እንዲሰሩ ያድርጉና ደብተራቸውን በመሰብሰብ እርማት ይስጧቸው፡፡**

### ክፍለ ጊዜ አስራ አምስት

የዕለቱ ትምህርት በጽሁፍ ውስጥ ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላትን መጠቀም እንደሆነ በመግለጽ ቀጥሎ የቀረበውን ማስታወሻ መነሻ አድርገው ስለተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላት ምንነት ገለጻ ያድርጉላቸው ። ከዚያ በፊት ግን ቀደም ሲል በመልመጃ አራት ስር የቀረቡትን የሚመስሉ ሀረጎችና አረፍተነገሮች ውስጥ ተሰምሮባቸው የቀረቡ ቃላት አሉ። ስለሆነም እነሱን ደብተራቸው ላይ በመጻፍ ፍቺያቸውን እንዲያመላክቱ ይጠይቋቸው።

ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላትን የተመለከተው ማስታወሻ ከዚህ በታች ቀርቧል፡-

ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላት የምንላቸው በዕለት ተእለት ንግግራችንና በጽሁፍ ውስጥ ተግባር ላይ የማይውሉ ቃላት ናቸው። እነዚህ ቃላት ብዙውን ጊዜ በተወሰኑ ሰዎች ዘንድ ብቻ የሚታወቁና ከሙያ ጋር ተያያዥ የሆኑ ሀሳቦችን ለመግለጽ ሲባል ጥቅም ላይ የሚውሉ ናቸው።

ለምሳሌ፡- ተለመ፣ ተረተረ፣ ጎለጎለ፣ ጨፈለቀ

ዋርድ፣ ኦፒዲ፣ ሪከቨሪ፣ ዲስፔንሰሪ

መጀመሪያ ላይ ያሉት ቃላት በእርሻ አካባቢ ያሉ ሰዎች ብቻ የሚጠቀሟቸው ሲሆኑ ሁለተኛ ላይ ያሉት ቃላት ደግሞ በህክምና ሙያ አካባቢ ያሉ ሰዎች የሚገለገሉባቸው ቃላት ናቸው።

መምህር ተማሪዎችዎ እርስዎ የሚሰጡትን ገለጻና መማሪያ መጽሐፋቸው ላይ ያለውን ማስታወሻ እያነበቡ ማስታወሻ እንዲውስዱ ይንገሯቸው። በማስከተልም ከማስታወሻው ቀጥሎ የመጣውን መልመጃ (**ለ. ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላትን ተጠቅሞ አረፍነገር መመስረት**) እንዲሰሩ ያሳስቧቸው። በቀጣዩ ክፍለጊዜም በተለያዩ ሙያዎች (ግብርና፣ ምህንድስና፣ ብረታብረት ስራ፣ መካኒክነት፣ ንግድ ወዘተ) ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ ቃላትን ጠይቀው በማሰባሰብ እንዲመጡ ይንገሯቸው።

ክፍለጊዜ አስራ ስድስት

# ትምህርት አምስት፡ መጻፍ

## ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-

- በጻሁፍ ውስጥ መሸጋገሪያ ቃላትን ይጠቀማሉ።

የዕለቱ ትምህርት በጽሁፍ ውስጥ የመሸጋገሪያ ቃላትን መጠቀም እንደሆነ በመግለጽ ቀጥሎ የቀረበውን ማስታወሻ መነሻ አድርገው ስለመሸጋገሪያ ቃላት ማብራሪያ ይስጧቸው። ማስታወሻውም የሚከተለው ነው።

*መሸጋገሪያ ቃላት በጽሁፍ ውስጥ ሀሳቦች ተያያዥነትና ተከታታይነት እንዲኖራቸው፣ ሀሳቦች ተጨማሪና ተደጋጋፊ እንዲሆኑ፣ ቃላትን፣ ሀረጋትንና አረፍተነገሮችን የሚያያይዙ ናቸው። እንዲሁም የሚቃረኑ ሀሳቦችን ተቃርኖአቸውን ለማያያዝ ያገለግላሉ።*

*ለምሳሌ፡- ደበሌ እና ጫላ ከትምህርት ቤት መጡ።*

*አያኖ ከፍተኛ ውጤት አስመዝግቧል፤ ይሁን እንጂ የተሻለ ውጤት ያመጡም አሉ።*

*ሰዎቹ የተቸገሩ ወገኖችን ከመርዳታቸውም በላይ በአካባቢው ልማት ላይ በመሳተፍም ይታወቃሉ።*

*የተሰመረባቸው ቃላት የመሸጋገሪያ ቃላት ናቸው። እነዚህ የመሸጋገሪያ ቃላት ቃላትን፣ ሀረጋትንና አረፍተነገሮችን በማያያዝ አረፍተነገሮቹ ሙሉ እንዲሆኑ ያደርጋሉ።*

## መልመጃ ስድስት

ከዚያም የቀረበላቸውን ማብራሪያና ምሳሌ መሰረት አድርገው የቀረቡትን አያያዥ ቃላት ተጠቅመው ተጓድለው የተሰጧቸውን አረፍተነገሮች እንዲያሟሉና የመሸጋገሪያ ቃላቱ በየአረፍተነገሮቹ ውስጥ ለምን አላማ እንደገቡ እንዲናገሩ ይጋብዙ። በዚህ ክፍል በምላሾቹ ላይ ከተነጋገራችሁ በኋላ ምጋቤ ምላሽ በመስጠት ወደ ቀጣዩ ተግባር

ይሸጋገሩ። ቀጣዩ ተግባር ተማሪዎቹ ራሳቸው መሸጋገሪያ ቃላት (አያያዦች)ን እየተጠቀሙ የየራሳቸውን አረፍተነገሮች እንዲመሰርቱ የሚደረግበት ነው። በመሆኑም መምህር እባክዎ ተማሪዎችዎ ይህንኑ እንዲያደርጉ ይንገሯቸውና በክፍል ውስጥ እየተዘዋወሩ አፈጻጸማቸውን ይቃኙ፤ መልሶቻቸውንም እንዲያጋሩ ያድርጉ። የተሰጠው ጊዜ ምናልባት ከተጠናቀቀ መልሶቻቸውን በቀጣዩ ክፍለጊዜ እንዲያንጸባርቁ ያድርጉ።

### ክፍለጊዜ አስራ ሰባት

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-**

- ሀረጋትን በአረፍተነገሮች ውስጥ ይለያሉ።

## ሀረጎች

### መልመጃ ሰባት

በዚህ ክፍል ጊዜ የሚቀርብው ይዘት በሀረጎች አረፍተነገር መመስረትን የተመለከተ ነው። መምህር እባክዎ በመማሪያ መጻህፋቸው ላይ የሚገኘውን ማስታወሻ መነሻ አድርገው ስለሀረግ ማብራሪያ ያቅርቡላቸው። ለሀረግ አይነቶቹም በቂ ምሳሌ እየሰጡ ያስረዷቸው። በመቀጠል በተሰጧቸው ሀረጎች ተጠቅመው አረፍተነገር እንዲመሰርቱ ያድርጉ።

### ክፍለጊዜ አስራ ስምንት

መምህር በዚህ ክፍለጊዜ የሚነሳውም ሀረጎችንና አይነታቸውን በተመለከተ ሲሆን ተማሪዎች የቀረበላቸውን ምሳሌ መነሻ በማድረግ ለየሀረግ አይነቶቹ ምሳሌ የሚሆኑ ሁለት ሁለት ሀረጎችን ይመሰርታሉ። ስለሆነም እርስዎ የሀረግን ምንነትና አይነቶቹን በተመለከተ ክለሳ በማቅረብ በቀጥታ ወደ መልመጃው እንዲገቡ ያድርጉ። ሲጨርሱም ሀረጎቻቸውን እየተለዋወጡ ስለትክክለኛነታቸው ይነጋገሩ፤ ይህ ሲጠናቀቅም ማሳያ የሚሆኑ ሀረጎችን ከየአይነታቸው ከተማሪዎች በመቀበልና ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ማረጋገጫ (ምጋቤ ምላሽ) ይስጡ።

## 4. ግምገማ

- ባዳመጡት አጭር ልቦለድ ውስጥ የልቦለድ አላባውያንን መለየታቸውን ያረጋግጡ።
- ያዳመጡትን አጭር ልቦለድ ታሪክ በቃላቸው መተረካቸውን ይከታተሉ።
- በአጭር ልቦለድ ያሉትን የግጭት መንስኤዎች መለየታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- በአጭር ልቦለድ ውስጥ ያሉትን ዋናና ንኡሳን ገጸባህርያትን መለየታቸውን ይጠይቁ።
- በአጭር ልቦለድ ያለ ታሪክ መቼ እንደተፈጸመ መለየታቸውን ያረጋግጡ።
- አረፍተነገሮች ምን ማለት እንደሆኑ መተርጎማቸውን ይከታተሉ።
- ያነበቡትን መረዳታቸውን ይጠይቁ፡፡
- ለቃላት አውዳዊ ትርጉም መስጠታቸውን ያረጋግጡ።
- ለቃላት ተመሳሳይ ትርጉም መስጠታቸውን ይከታተሉ።
- በአረፍተነገር ውስጥ የመሸጋገሪያ ቃላትን አስገብተው መጠቀማቸውን ይለዩ።
- ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላትን ተጠቅመው አረፍተነገር መመስረታቸውን ያረጋግጡ።

## 5. የመልመጃዎችና ተግባራት መልስ

### ትምህርት አንድ፡ማዳመጥ

### ቅድመማዳመጥ

1. አንድ ነጠላ ታሪክ ላይ የሚያተኩር፣ አንድ አብይ ገጸባህሪ ያለው፣ በጥቂት ጊዜያት ተነቦ የሚያልቅ፣ ውስን ግጭቶች ያሉት ወዘተ
2. ተማሪዎች እንደየልምዳቸው የሚሰጧቸው የተለያዩ መልሶች

### የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. እሼት የሚሸጡት ሴት እና ገገሮው (ተራኪው)
2. ክረምት (ወርሃ ሰኔ)፣ የዝናብ ወቅት

### መልመጃ አንድ

ሀ. በቃል የሚመለሱ የተለያዩ ጥያቄዎች

1. መንገድ ዳር በቆሎ በሚጠበስበት አካባቢ (ዷንሾ)

2. ክረምት ዝናብ ሊዘንብ ባለበት ጊዜ/ሰኔ ወር/
3. ሸብረክ ብሎ የእኼት ዋጋ ጠየቀ፣ በአክብሮት ስም ስላልጠራቸው ይቅርታ ጠየቀ፣ ሦስቱ እኼት ስንት እንደሆነ ደግሞ ጠየቀ፣ ስድስት ራስ የበቆሎ እኼት ገዛ
4. አዛውንት
5. ወርሃ ሰኔ ሲል የሰኔ ወር ማለቱ ነው/ የክረምት ወቅት/
6. ሻጪ እያግባቡ ስለነገሩትና ተማጽኖ ስላቀረቡ፤ እንዲሁም በእድሜ መግፋታቸውን ከግምት በማስገባት
7. የማታ እንጀራ ይስጥህ፤ በእርጅና ዘመንህ ችግር አይግጠምህ ማለት ነው
8. ሳይገዛቸው እንዳይሄድ

## ተግባር አንድ

(በቡድን ተወያይተው የደረሱበት ማንኛውም ተቀባይነት ያለው መልስ)

## ተግባር ሁለት

(ቀደም ሲል ያዳመጡት ምንባብ ክንውኖች በቅደምተከተል)

# ትምህርት ሁለት፡መናገር

## ተግባር ሦስት

በገዢና ሻጭ መካከል ይደረጋል ተብለው የሚታሰቡ ምልልሶችን መሰረት ያደረገ የሚና ጨዋታ

## ተግባር አራት

አስቀድመው አንብበው እንዲመጡ የተነገራቸውን አጭር ልቦለድ ታሪክ አሳጥሮ መናገር፤ ገጸባህሪያቱን መግለጽ

## ተግባር አምስት

የቀረበውን ምንባብ በማንበብ ታሪኩን አሳጥሮ በራስ አገላለጽ ማቅረብ

## ተግባር ስድስት

ሀ. ለ በጎ የተሰኘውን ታሪክ መልሶ በቃል መንገር፤ እሱን የሚመስል ገጠመኝ ካለ በቃል ማቅረብ

ለ. 1. መ

2. ለ
3. ሀ
4. ሀ

## ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

### የቅድመማንበብ ጥያቄዎች

1. አንድ ነጠላ ታሪክ ያለው፣ ብዙገጸባህሪያት የማይሳተፉበት…ውበት ያለው የፈጠራ ስራ…
2. ታሪክ፣ ገጸባህሪያት፣ መቼት፣ ጭብጥ…

### የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. መምህሩ 2. መልካም ስም

### የአንብቦመረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

ሀ. 1. የመምህሩ መኖሪያ ቤት/ከተማ/

2 አባታችሁ የመልካም ስም ባለቤት በመሆኑ በወንጀል አትፈለጉም፤ ስለዚህ ፍርሃት አይግባችሁ ለማለት

3. በሞት አፋፍ ላይ ሆነው እያጣጣሩ

4. በጎ በመስራት፣ ባለመስረቅ…

5. ባለመልካም ስም እና በጣም ተወዳጅ ስለነበሩ…

6. ደስተኛ የሆኑ ሰዎች በሚሰሩት ስራም ውጤት ማምጣት፣ ስኬት ማስመዝገብ ይችላሉ ለማለት ነው

### ተግባር ሰባት

1. በህይወት ዘመናችሁ መልካም ሁኑ (አትስረቁ፣ ሰው አታስቀይሙ፣ ከክፋት ራቁ ወዘተ)
2. አስደሳችና ያማረ (በስኬት የታጀበ)…
3. ሀብትና ንብረት ባይኖረውም፣ ሀቀኛ በማህበረሰቡ ዘንድ ተወዳጅና በዚሁ ምክንያትም ቤተሰቡን (ልጆቹን) ያስከበረ፤ መልካም ስሙን ተክሎ ያለፈ

## መልመጃ ሦስት

ድርጊት አንድ፣ መምህሩ ለልጆቹ ተናዘዙ።
ድርጊት ሁለት፣ የለሊቱ አጋማሽ ስደርስ ለሞት እጅ ሰጡ
ድርጊት ሶስት፣ ወዳጆቻቸውና ጎረቤቶቻቸው እንባ አፈሰሱ
ድርጊት አራት፣ ቀብራቸው በቀጣዩ ቀን ተፈጸመ
ድርጊት አምስት፣ ልጆቻቸው በአባታቸው መልካም ስም የተነሳ የሚወደዱና የሚከበሩ ሆኑ
ድርጊት ስድስት፣ ልጆቹ ደስተኞች፣ መልካም ስብዕናን የገነቡና በራሳቸው የሚተማመኑ ሆኑ

**ለ.** ተቀባይነት ያላቸውና በተማሪዎቹ የሚሰጡ የተለያዩ መልሶች

# ትምህርት አራት፡ ቃላት

## መልመጃ አራት

**ሀ. የቃላት አውዳዊ ትርጉም**

1. አታንሳው /አትላጠው
2. ሊዘንብ /ሊጥለው/
3. ተንበርክኬ /ቁጢጥ/
4. ረጅም ዕድሜ /ያረጁ/
5. ልመና፤ አኩራምቶ/ጠርንፎ፣ጭምድድ አድርጎ/
6. ሞገስ ያለው ፤ የከመረው
7. ገምተዋል

**ለ.** 1. ስጦታ
2. ከተጽዕኖ መላቀቅ
3. ተሳካ/ፍሬ አፈራ
4. ጭምት/የተገደበ/
5. እርካታ
6. መልካም
7. ውለታ/ አደራ
8. በጎ/መልካም
9. አሳዛኝ
10. ምስጋና/ማበረታቻ

## መልመጃ አምስት

1. ጠንክሬ/ሳልበገር
2. በሚያጓጉ/በሚያሳሱ፤ተጠብቄ/ሁሉን ትቼ
3. ተቆጣጥሬ/አስቀርቼ
4. የየዕለት ተግባራቸው/ባህላቸው
5. ቻሉ/ደረሱ
6. ጫንቃ
7. አረፉ/ሞቱ

ለ. ቃላቱን በመጠቀም ተማሪዎች የሚመሰርቷቸውና ተቀባይነት ያላቸው ማናቸውም አረፍተነገሮች

## ትምህርት አምስት፡ መጻፍ

## መልመጃ ስድስት

ሀ. 1. ከዚያም
2. በአንጻሩ
3. በተያያዘ
4. በመሆኑም
5. እንዲሁም
6. ስለዚህ/በመሆኑም

ለ. መሸጋገሪያ ቃላትን የተጠቀሙና ተቀባይነት ያላቸው ማናቸውም አረፍተነገሮች መልስ ይሆናሉ

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

ሀ. የተሰጡትን ሀረጎች (ከ1-10) ከግምት ያስገቡና የቋንቋውን ሰዋስው (ስርዓት) የጠበቁ ተቀባይነት ያላቸው ማናቸውም አረፍተነገሮች በምላሽነት ሊቀርቡ ይችላሉ።

ለ. ለየሀረግ አይነቶቹ ምሳሌ የሚሆኑ ሁለት ሁለት ሀረጎች

# ምዕራፍ አምስት

# የህዝብ ብዛት

(የክፍለጊዜ ብዛት 18)

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- በንቃት አዳምጠው የቀረበውን ጽሁፍ ይገመግማሉ፤
- የህዝብ ብዛት የሚለውን ጽንሰሀሳብ ያብራራሉ፤
- ተራኪ ድርሰት ይጽፋሉ፤
- የህዝብ ቁጥር በምጣኔ ሀብት እድገት ላይ ያለውን እንድምታ ይመረምራሉ፤
- ፍላጎቶቻቸውን ለመግለጽ ፉካሬያዊ ቃላትን ይጠቀማሉ፤
- የገቢርና ተገብሮ ቃላትን በአረፍተ ነገር ውስጥ ይጠቀማሉ::

## 2. የትምህርት ይዘት

### 2.1 ማዳመጥ

- የሚነበበውን ጽሁፍ ማዳመጥ
- የወሳኝ ኩነት ምዝገባን ጠቀሜታ ማዳመጥ
- በወሳኝ ኩነት ምዝገባ ውስጥ የሚመዘገቡ ጉዳዮችን ለመለየት ማዳመጥ
- የምንባቡን ዋና መልዕክት ለመለየት ማዳመጥ

### 2.2 መናገር

- በወሳኝ ኩነት ምዝገባ ውስጥ የሚመዘገቡ ጉዳዮች ለምን ወሳኝ ኩነት እንደተባሉ መናገር
- የአንድን ህዝብ ብዛት የሚወስኑ ጉዳች ላይ ንግግር ማድረግ
- የህዝብ አስተዳደርን በስርዓት ለመምራት መነሻ መሰረቶች ላይ ንግግር ማድረግ
- ስለወሳኝ ኩነት ምዝገባ ጠይቀው ያገኙትን በቃል ማቅረብ
- ተወያይተው ያገኙትን መናገር
- በያዙት ማስታወሻ ላይ ንግግር ማድረግ

- ያዳመጡትን ምንባብ ፍሬሀሳቡን መናገር

## 2.3 ማንበብ

- "የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ምጣኔ ሀብታዊ አንድምታ" የሚለውን ምንባብ ማንበብ
- የየአንቀጾችን መልዕክት ለማግኘት ማንበብ
- የተለያዩ ጥያቄዎችን ለመመለስ ማንበብ
- የመንስኤና ውጤት ግንኙነት ያላቸውን ሀሳቦች ለመለየት ማንበብ
- የቃላትን አውዳዊ ፍች ለማግኘት ማንበብ
- ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ለመስጠት ማንበብ

## 2.4 ቃላት

- ለቃላት አውዳዊ ትርጉም መስጠት
- ለቃላት ተመሳሳይ ትርጉም መስጠት
- ለቃላት ፍካሬያዊና እማሬያዊ ፍቺ መስጠት

## 2.5 መጻፍ

- ተራኪ ድርሰት መጻፍ
- የአለም ህዝብ ቁጥር ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ያሣየውን ዕድገት መጻፍ
- እንደገና አስተካክሎ መጻፍ
- የራስን የህይወት ታሪክ መጻፍ

## 2.6 ሰዋስው

- ገቢርና ተገብሮ ግሶችን መለየት
- በገቢርና በተገብሮ ግሶች አረፍተነገር መጻፍ

# 3. የማስተማሪያ ዘዴ

- ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ወይም ከአጠቃላይ ወደዝርዝር የማስተማሪያ ስልቶችን ተጠቅሞ ማስተማር።
- ተማሪን ማዕከል ያደረጉ የማስተማር ዘዴዎችንና ብልሃቶችን መጠቀም።
- የቅድመ ማዳመጥ ተግባር በማቅረብ የቀደመ እውቀታቸውን በውይይት መቀስቀስ

- በማዳመጥ ጊዜ ተማሪዎች እያዳመጡ የጽሁፉን ፍሬ ሀሳብ በማስታወሻቸው እንዲይዙ ማድረግ
- ያዳመጡትን ምንባብ መሰረት ያደረገ ቀስቃሽ ጥያቄዎችን ማቅረብ
- ችግርን የማቃለል ተግባራትን ሰጥቶ ችግር ማቃለልን ማለማመድ
- ከክፍል ውጪ የሚሰሩ መስተጋብርን የሚፈጥሩ ተግባራትን እንዲሰሩ ማድረግ
- ቅድመ ንባብ ተግባራትን በማቅረብ ማወያየትና የቀደመ እውቀታቸውን መቀስቀስ
- አንብቦ የመረዳት ማስተማሪያ ስልቶችን ተግባራዊ ማድረግ
- ማብራሪያ የሚፈልጉ ጥያቄዎችን አቅርቦ እንዲያብራሩ ማድረግ
- ሂደታዊ ጽህፈት ማስተማሪያ ስልቶችን ተከትለው ድርሰት መጻፍ ማለማመድ
- ስለገቢርና ተገብሮ ግሶች የሚያውቁትን አስታውሰው እንዲናገሩ ማነሳሳት

ክፍለጊዜ አንድ

# ትምህርት አንድ ማዳመጥ

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-**

- በንቃት አዳምጠው ምንባብን ይገመግማሉ።

## ቅድመ ማዳመጥ

በትምህርት አንድ ስር በክፍለ ጊዜ አንድ የተማሪዎችን የማዳመጥ ፍላጎት የሚያነሳሱ ሁለት ጥያቄዎች ቀርበዋል። እባክዎ መምህር ሁለቱን የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች መልስ ተቀብለዋቸው ወደ ዋናው ትምህርት ይግቡ። በሚያዳምጡበት ጊዜም አጫጭር ማስታወሻ እንዲይዙ ያድርጉ። በመጀመሪያ ‹‹ወሳኝ ኩነት›› በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ የመጀመሪያዎቹን ሶስት አንቀጾች ያንብቡላቸው። ከዚያም ቆም ብለው በማዳመጥ ጊዜ የቀረቡ ጥያቄዎችን ያሰሯቸው። በመቀጠል ቀሪውን የምንባብ ክፍል ያንብቡላቸው። እንደሚታወቀው ምንባቡ ቢያንስ ሁለት ጊዜ የሚነበብ ሲሆን የማዳመጥጊዜ ተግባራቱ የሚከናወኑት በመጀመሪያው ምንባብ ይሆናል።

# የወሳኝ ኩነት ምዝገባ

ልደትና ሞት ጋብቻና ፍቺ የሰው ልጅ ሕይወት የሚጀመርባቸውና የሚጠናቀቅባቸው የሕይወት ኩነቶች ናቸው። እንግዲህ ወሣኝ ኩነት በመባል የሚታወቁት **የልደት፣ የጋብቻ፣ የፍቺ እና የሞት** ክስተቶች ናቸው። እነዚህ ክስተቶች ወሣኝ ኩነቶች የተባሉበት ዋናው ምክንያት ወሳኝ የሆኑ ሕጋዊ የግለሰብ ማንነት መረጃዎች ምንጭ በመሆናቸው ነው።

ኩነቶች በአንድ አገር ዜጎች የማኅበራዊ፣ የኢኮኖሚና የፖለቲካ መስተጋብሮች ላይ ቁልፍ ሚና ይኖራቸዋል። ከዚህ በመነሳት ከላይ የተጠቀሱት ኩነቶች ሲከሰቱ የሚመዘገቡበት፣ የሚደራጁበት እና ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውልበት የአመዘጋገብና የመረጃ አጠነቃቀር ሥርዓት **የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ** በመባል ይታወቃል። በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ ፍትሐብሔር ሕግ **"ሰው ከተወለደበት ቀን አንስቶ እስከ ሞተበት ቀን ድረስ የሕግ መብት አለው"** በማለት ደንግጓል። በሌላም በኩል ጋብቻና ፍቺ በሰው የአኗኗር ሥርዓት ውስጥ የሚከሰቱ ዋነኛ ማኅበረሰባዊና ሕጋዊ የለውጥ ጠቋሚ ወሳኝ ኩነቶች ናቸው። እነዚህ በግለሰቦች ላይ የሚከሰቱ ተፈጥሮአዊና ማኅበረሰባዊ ለውጦች የአንድን ሀገር የህዝብ አስተዳደር በሥርዓት ለመምራት መሰረቶች ናቸው።

## የማዳመጥ ጊዜ

እባክዎ መምህር እዚህ ጋ ምንባቡን ገታ አድርገው ተማሪዎች ቀደም ብለው ያዳመጡትን የምንባቡን ክፍል በማስታወስ ተማሪዎችዎ ባዶ ቦታዎቹን እንዲያሟሉ ያትጓቸው።

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ኩነቶች በአንድ አገር ዜጎች የ__________፣ የ__________ እና የ__________ መስተጋብሮች ላይ ቁልፍ ሚና ይኖራቸዋል።
2. __________ እና __________ በሰው የአኗኗር ሥርዓት ውስጥ የሚከሰቱ ዋነኛ ማኅበረሰባዊና ሕጋዊ የለውጥ ጠቋሚ ወሳኝ ኩነቶች ናቸው።

ልደትና ሞት የህዝብ ብዛትና እድገትን በቀጥታ ከሚያመለክቱ ክስተቶች ዋነኞቹ ናቸው። ይኸውም የህዝቡ ቁጥር መጨመር፣ መቀነስ ወይም ባለበት መቆየቱ

የሚታወቀው በአንድ ሀገር በሚከሰተው የልደትና ሞት ኩነት ብዛት ነው። በተመሣሣይ መልኩ ጋብቻና ፍቺም የአንድ ሀገር ህዝብ ብዛትና እድገት መጨመርን ወይም መቀነስን በተዘዋዋሪ ከሚወስኑ ሁኔታዎች ውስጥ የሚካተቱ ናቸው። የጋብቻ ኩነት ሲከሰት የአንድ ሀገር ህዝብ ቁጥር ይጨምራል። በአንፃሩ የፍቺ ኩነቶች በተከሰቱ ቁጥር የሚከሰቱ የልደት ኩነቶችም በዚያው መጠን ይቀንሳሉ። በተመሣሣይ መልኩ የልደት መጠን በጨመረ ቁጥርና የሞት ኩነቶች ክስተት በቀነሰ ቁጥር የህዝብ ቁጥር እድገትም በዚያው መጠን ይጨምራል፡፤

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

ሀ. መልመጃ አንድ ተማሪዎች ያዳመጡትን መሰረት አድርገው የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃል የሚመልሱበት ነው። እባክዎ መምህር ተማሪዎች ሦስቱንም ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በቂ ምላሽ እየሰጡ እንዲመልሱ ያበረታቱዋቸው። ለምላሾቻቸው ትክክለኛነትም ሌሎች ተማሪዎች ማረጋገጫ እንዲሰጡ በመጋበዝ ተጨማሪ የውይይት አማራጭ መፍጠር ይችላሉ።

ለ. በዚህ ክፍል ባዶ ቦታ ማሟላትን የሚጠይቅ መልመጃ ቀርቧል፤ እባክዎ መምህር ተማሪዎችዎ ጥያቄዎቹን በደብተራቸው ላይ ጽፈው ምላሽ እዲሰጡባቸው ያድርጉ። መልሶቻቸውንም ከጎናቸው ካለ ተማሪ ጋር እንዲያነጻጽሩና ለክፍሉ እንዲያንጸባርቁም ያበረታቷቸው።

**ክፍለጊዜ ሁለት**

## ተግባር አንድ

መምህር በዚህ ተግባር አንድ ስር ተማሪዎችዎ ቢቻል በአካል ሂደው ባይቻል ደግሞ ምናባዊ አውድ ፈጥረው ወሳኝ ኩነት ዝገባን የሚያካሂዱናወሳኝ ኩነት ምዝገባ የማያካሂዱ ሰዎች የሚገጥማቸውን እድልና ተግዳሮት በተመለከተ ውይይት እንዲያደርጉ ያበረታቷቸው። ከዚህም ሌላ ወሳኝ ኩነት ማስመዝገብ ላይ ቸልተኝነት የሚታይባቸው ሰዎች ቢያጋጥሟቸው ምን አይነት ምክር ለምን እንደሚሰጡም ጭምር ይናገሩ። በመጨረሻም ከውይይቱ ያገኟቸውን ግብአቶችና ሌሎችን በመጠቀም አጠቃላይ ሀሳቡን በአንቀጽ መልክ አደራጅተው እንዲያቀርቡ ያትጓቸው። መምህር በራስዎም ተነሳሽነት ሞዴል አንቀጽ አስቀድመው በማዘጋጀት በማሳየት

ቢያቀርቡላቸው ትምህርቱን ይበልጥ ተጨባጭ ያደርጉላቸዋል ተብሎ ይታሰባል። በመጨረሻም ተግባር ሁለትን በቤታቸው ሰርተው እንዲመጡ ይዘዟቸው።

**ክፍለጊዜ ሶስት**

## ተግባር ሁለት

**ለ.** መምህር ዛሬም ተማሪዎችዎ ወሳኝ ኩነትን በተመለከተ እየተነጋገሩና እየጻፉ የቋንቋ ክህሂሎቻቸውን እንዲያጎለብቱ እድል የሚፈጥርላቸው ተግባራት ቀርበዋል። በዚሁ መሰረት በአካባቢያቸው የወሳኝ ኩነት አሰጣጥ ሂደትን በአካል ሄደው በመጎብኘትና ሰዎችን በመጠየቅ መረጃ እንዲያሰባስቡና ያሰባሰቡትንም መረጃ አጠናቅረው ለክፍል እንዲያቀርቡ በማበረታታት ያሳትፏቸው። ምዘናውንም በአቅርቦት ወቅት በሚኖር ጽብረቃና ተሳትፎ በመመስረት ያከናውኑ።

**ክፍለጊዜ አራት**

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

### ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡

- መረጃን መሰረት አድርገው ይናገራሉ።

## ተግባር ሶስት

ወሳኝ ኩነት ምዝገባ በሚል ርዕስ የቀረበው ምንባብ ሲነበብላቸው ያዳመጡትን መሰረት በማድረግ በቀረቡላቸው ጥያቄዎች ላይ በቡድን ከተወያዩ በኋላ የደረሱበትን ድምዳሜ ለክፍል ጓደኞቻቸው በቃል እንዲያቀርቡ ያድርጉ።

**ክፍለጊዜ አምስት**

## ተግባር አራት

በዚህ ምዕራፍ በክፍለጊዜ አንድ ምንባብ ሲነበብላቸው የያዙትን ማስታወሻ መናገር የሚል ነው። የያዙትን ማስታወሻ ለጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያድርጉ። ጓደኞቻቸው ሲነግሯቸው እንዲያዳምጡም ይንገሯቸው። የሚለያዩባቸውን ሀሳቦችም ለይተው እንዲናገሩ ያድርጉ። በዚህ ጊዜም እየተዘዋወሩ ያበረታቷቸው። በመጨረሻም ተግባር አምስትን በቤታቸው ሰርተው እንዲመጡ በየቤትስራ መልክ ይስጧቸው።

ክፍለጊዜ ስድስት

## ተግባር አምስት

በዚህ ክፍለጊዜ የሚቀርበው የትምህርት ይዘት ጠይቀው ያገኙትን መረጃ ማቅረብ የሚል ነው። በአካባቢያችሁ የሚገኙ ነዋሪዎችን ስለወሳኝ ኩነት ምዝገባ ያላቸውን ግንዛቤ ጠይቀው መምጣታቸውን ካረጋገጡ በኋላ ባገኙት መረጃ ላይ በቡድን እንዲወያዩ ያድርጉ። ተወያይተው የደረሱበትን በተወካያቸው አማካኝነት ለክፍል ጓደኞቻቸው በቃል እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው።

ክፍለጊዜ ሰባት

# ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

### ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-

- በጥልቀት በማንበብ የመንስኤና ውጤት ግንኙነት ያላቸውን ሀሳቦች ከምንባብ ይለያሉ።

## ቅድመ ንባብ

እባክዎ መምህር ተማሪዎች በቀጥታ ወደ ንባብ ከመግባታቸው በፊት ለማንበብ ተነሳሽነት ያድርባቸው ዘንድ በሚከተሉት ነጥቦች ዙሪያ ምላሽ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው።

- ርዕሱን ተመልክተው ምንባቡ ስለምን እንደሚያወሳ እንዲናገሩ
- የህዝብ ብዛት ዕድገት ከምጣኔያዊ እድገት አንድምታ ጋር ምን አይነት ግንኙነት እንዳለው
- የሀገራችን የህዝብ ብዛት እድገት አሳሳቢ የሚሆነው ለምን እንደሆነ

ከዚያም "የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ምጣኔ ሀብታዊ አንድምታ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በትኩረት እንዲያነቡ ይዘዟቸው። ሲያነቡም በአንኳር አንኳር ጉዳዮች ዙሪያ አጫጭር ማስታወሻዎች እንዲይዙ ያድርጓቸው።

## የንባብ ጊዜ

ተማሪዎች የምንባቡን ሶስት አንቀጾች አንብበው ካጠናቀቁ በኋላ የህዝብ ቁጥር ዕድገት የሚያስከትላቸው ተጽዕኖዎች ምን ምን እንደሆኑ፣ የሕዝብ ቁጥር ማደግ የምጣኔ ሀብትን እንዴት ይደግፋል ብለው እንደሚያስቡ? ይጠይቋቸው፤ መልሶቻቸውን በመቀበል ያበረታቷቸው። አጫጭር ማስታወሻ መያዛቸውን እንዲቀጥሉ ያሳስቡ፤

ክፍለጊዜ ስምንት

## ድህረ ንባብ

### መልመጃ ሁለት

ሀ. በመልመጃ ሁለት ስር ምንባቡን መሰረት አድርገው የወጡ ጥያቄዎች አሉ። እባክዎ መምህር ያለፈውን ትምህርት ይዘት ከከለሱና የእለቱን ትምህርት ካስተዋወቁ በኋላ ሁሉንም ጥያቄዎች (ከ1-8) ተማሪዎች ምንባቡን ከግምት እያስገቡ እንዲሰሯቸው ማበረታቻ ይስጧቸው፤ እየተዘዋወሩም ይመልከቷቸው።

ክፍለጊዜ ዘጠኝ

ለ. የህዝብ ቁጥርና ምጣኔሀብትን የተመለከተው ምንባብ በክፍለጊዜ ዘጠኝ ስር በማጣቀሻነት ጥቅም ላይ ይውላል። በመሆኑም ተማሪዎች እንዲመልሷቸው የሚጠበቁ የምርጫ ጥያቄዎች ስለቀረቡ ምንባቡን መሰረት አድርገው እንዲመልሷቸው ያበረታቷቸው። ጥያቄዎቹ መጀመሪያ በግል ከተሰሩ በኋላ ቀጥሎ ደግሞ ጥንድ ጥንድ እየሆኑ የሚሰሯቸው ናቸው። በመጨረሻም እንደክፍል በጋራ ለጽብረቃ ይቀርባሉ። እባክዎ መምህር ይህንኑ ቅደም ተከተል በመከተል ተማሪዎችዎን ተሳታፊ ያድርጓቸው።

ክፍለጊዜ፡ አስር

### መልመጃ ሦስት

በዚህ ክፍለ ጊዜ የቀረበው የትምህርት ይዘት የምክንያትና ውጤት ትስስር ያላቸውን ሀሰቦች መለየት በሚል የቀረበ ነው። በመሆኑም መምህር የምክንያትና ውጤት ትስስር ያላቸውን አረፍተነገሮች አቅርበው ምክንያትና ውጤት የተገለጹትን ሀሳቦች በማሳየት ይለዩላቸው። ምሳሌውን መሰረት አድርገውም በመማሪያ መጽሃፋቸው ላይ የቀረቡትን ጥያቄዎች እንዲሰሩ ያመላክቷቸው። ማጠናቀቃቸውን በማረጋገጥም ከተማሪዎቹ ጋር በጋራ በመሆን የሁሉንም ጥያቄዎች መልሶች ሰሌዳ ላይ ይጻፏቸው።

በመልመጃ አራት ስር የቢጋር ሰንጠረዥ ቀርቧል። ተማሪዎችዎ ይህንን የቢጋር ሰንጠረዥ ወደ ደብተራቸው ከገለበጡ በኋላ የተጓደሉትን ሀሳቦች እንዲያሟሉ ያበረታቷቸው። ሀሳቦቹ የህዝብ ቁጥር መጨመር ያለውን አዎንታዊና አሉታዊ ጎኖች

የተመለከቱ ናቸው። በመጨረሻም ያሟሉትን ቢ.ጋር መነሻ አድርገው አንቀጽ ጽፌው እንዲያቀርቡ ያድርጉ። የተያዘው ጊዜ አንቀጹን ጽፎ ለመጨረስ የማይበቃ ከሆነ በየቤት ስራ መልክ በቤታቸው አጠናቅቀው እንዲመጡ ያሳስቧቸው።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ**

# ትምህርት አራት፡ ቃላት

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-**

- ፍላጎቶቻቸውን ለመግለጽ ፍካሬያዊ ቃላትን ይጠቀማሉ፤
- ለቃላት አውዳዊ ፍቺ ይሰጣሉ፤
- ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ይሰጣሉ።

## መልመጃ አምስት

በዚህ መልመጃ የቀረቡት ጥያቄዎች ከምንባቡ ለወጡ ቃላት አውዳዊ ፍቺ መስጠትን የተመለከቱና ለቃላት ተመሳሳይ ፍች መፈለግን የሚጠይቁ ናቸው። በመሆኑም ተማሪዎች ይህንን መሰረት አድርገው በ ሀ እና ለ ትዕዛዛት ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች ይመልሱ። ሲያጠናቅቁም ከብጤዎቻቸው ጋር መልሶቹን እያነጻጸሩ ይተራረሙ። በመጨረሻም እንደክፍል በጋራ ምላሾቹን የማረጋገጥ ውይይት ይሰናዳ። መምህር እርስዎም በክፍል ምልከታ የተገኘን መረጃና በጽብረቃ ወቅት ያለ ተሳትፎን ከግምት በማስገባት ምዘና ያካሂዱ፤ ምዘናውም ከቋንቋ አጠቃቀምና የቋንቋ ክሂሎች የመዳበር ደረጃን ከግምት ያስገባ ይሁን። በአማራጭነት የመልመጃ ጥያቄዎቹን በተመለከተ የተማሪዎቹን ደብተሮች በመሰብሰብና በማረም ምጋቤ ምላሽ መስጠት ይቻላል።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት**

## መልመጃ ስድስት

በዚህ ክፍለ ጊዜ የቀረበው የትምህርት ይዘት የፍካሬያዊ ቃላት ፍቺን የተመለከተ ነው። በተማሪው መማሪያ መጽሀፍ ላይ የቀረበውን ማስታወሻና ምሳሌ መነሻ አድርገው ስለፍካሬያዊ ቃላት ምንነት በምሳሌ በማስደገፍ ማብራሪያ ያቅርቡላቸው። ከዚያም በመልመጃ ስድስት ሀ ስር በአረፍተነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት ፍካሬያዊ ፍቺ እንዲሰጡ ያበረታቱ። በስተመጨረሻም በትዕዛዝ ለ ስር በተጠየቀው መሰረት

የየራሳቸውን ቃላት በመምረጥ እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ከሰጧቸው በኋላ በቃላቱ መልሰው ይህንኑ ፍቻቸውን በሚያሳይ መልኩ አረፍተነገሮች እንዲመሰርቱባቸው ያድርጉ።

ክፍለጊዜ አስራ ሦስት

**መልመጃ ሰባት**

የዕለቱ ትምህርት በመልመጃ ሰባት ሐ ስር ለቀረቡት ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ መስጠትን የሚመለከት እና በዚሁ መልመጃ መ ስር ተማሪዎቹ የየራሳቸውን አምስት አምስት ቃላት መርጠው እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቻቸውን በሚያሳይ መልኩ አረፍተነገሮች እንዲመሰርቱ የሚጠይቀው ነው። ስለሆነም መምህር ተማሪዎችዎ ለቃላት ያላቸው ግንዛቤ እንዲጎለብትና የቃላት ክምችታቸውንም እንዲያሳድጉ ስለሚረዳቸው ተግባሩን ሳይሰላቹ በትኩረት እንዲሰሩ ያሳስቧቸው፤ አፈጻጸማቸውን በመገምም ምጋቤ ምላሽ ይስጧቸው።

ክፍለጊዜ አስራ አራት

## ትምህርት አምስት፡ መጻፍ

### ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-

- ተራኪ ድርሰትን ይጽፋሉ፤
- ተራኪ ድርሰትን በማንበብ ሁነቶችን በቅደምተከተል ያሰፍራሉ።

መምህር እባክዎን ለተማሪዎችዎ የዕለቱ ትምህርት ተራኪ ድርሰት መጻፍ እንደሆነ በመግለጽ በተማሪ መጽሀፍ ላይ የቀረበውን ማስታወሻ መነሻ አድርገው ስለተራኪ ድርሰት ማብራሪያ ይስጧቸው። ማስታወሻውም

**ተራኪ ድርሰት፡** የተራኪ ድርሰት ዋና አላማ የድርጊት ቅደምተከተል ያላቸውን ታሪኮች ከግለሰባዊ እይታ አንጻር መተረክ ነው። ዋና ተግባሩ መንገር ስለሚፈለገው ጉዳይ መጠቀስ የሚገባቸውን አንድ በአንድና በቅደምተከተል በማንሳት አንድ ወጥ የታሪክ ቅንጫቢ ለታዳሚው ለማቅረብ ነው። በማራኪ ዝርዝር ሁኔታዎች እና በሳቢ ሁነቶች ከተዋቀረ ተራኪ ጽሁፍ ለጸሃፊውም ሆነ ለአንባቢው አስዳሳችና ማራኪ ይሂናል።

***ምሳሌ***

ከዕለታት አንድ ቀን የራበው መንገደኛ የአተር እሸት ያለበት ማሳ አገኘ። ቁጭ አለና አተሩን ከነልባሱ ሲበላ ቆየ። ጠገብ ሲል ልባሱን እያነሳ መብላት ጀመረ። በጣም ሲጠግብ ደግሞ ከውስጥ የዘሩን ፍሬ እያወጣ መብላት ያዘ። የማሳው ባለቤት ከዛፍ ስር ሆና ስታየው ኖራ መንገደኛ እንደመጀመሪያውም እንደመጨረሻውም አትብላ፣ እንደመካከለኛው ብላ አለችው።

መምህር ተማሪዎችዎ ማስታወሻው ላይ ከተወያዩና ምሳሌውን ካዩ በኋላ ተግባር ሰባትን በተሰጠው መመሪያ መሰረት እንዲሰሩት ያሳስቧቸው። ለተግባር ስምንት ግብዓት የሚሆን መረጃም በቀጣዩ ክፍለጊዜያቸው ይዘው እንዲመጡ ያሳስቧቸው፤ ለዚህም ተግባሩን አስመልክቶ በመጽሐፋቸው የተሰጠውን ትዕዛዝ ማንበብ ይጠበቅባቸዋል።

### ክፍለጊዜ አስራ አምስት

## ተግባር ስምንት

ቀደም ሲል በተጠቆሙት መሰረት ቤተመጽሐፍ በመሄድ ያነበቡትን ተራኪ ጽሑፍ በተመለከተ ዋና ዋና ክንውኖችን በቅደም ተከተል በማስፈር ለክፍል ጓደኞቻቸው በማንበብ ያቀርባሉ። መምህር እርስዎም ሁሉም ተማሪዎች የሚጠበቅባቸውን በማድረግ እየተሳተፉ መሆኑን ክፍል ውስጥ ዘወር ዘወር እያሉ ይመልከቱ፤ በዚህም ለአጠቃላይ ምዘናው (የጽሑፍ ክሂል) የሚሆን ግብዓት ያገኙበታል ተብሎ ይጠበቃል።

### ክፍለጊዜ አስራ ስድስት

## ተግባር ዘጠኝ

መምህር ተማሪዎችዎ ዛሬም ሌላ መጻፍን የመለማመጃ እድል ከሚያገኙበት ተግባር ጋር ይተዋወቃሉ። በዚህ ተግባር የተራኪ ድርሰት አወቃቀርን (የጊዜና የክስተት ቅደምተከተል) በመከተል የየራሳቸውን የህይወት ታሪክ መጻፍን ይለማመዳሉ። ስለሆነም መምህር ተማሪዎችዎ ይህንን እድል በአግባቡ እንዲጠቀሙ በማበረታታት እና ድጋፍና ክትትል በመስጠት እንዲተጉ ማድረግ ይጠበቅብዎታል።

ክፍለጊዜ አስራ ሰባት

## ተግባር አስር

መምህር እባክዎ ተማሪዎችዎ የቀረበውን ምንባብ አንብበው የአለም ህዝብ ቁጥር ዕድገት በምጣኔ ሀብት ላይ የሚኖረውን አዎንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖ በዝርዝር ይመለከቱ ዘንድ የትምህርቱን አላማና አቀራረብ በማስተዋወቅ ቅድመዝግጅት እንዲያደርጉ ያበረታቷቸው። በመቀጠልም ወደ ጽሑፍ ተግባሩ እንዲሸጋገሩና ሲጽፉም በማንበብ ያገኙትን መረጃ እንዲጠቀሙ ለተማሪዎቹ ማሳሰቢያ ይሰጣቸው። ሲጨርሱም ደብተሮቻቸውን በመሰብሰብ እዚያው ክፍል ውስጥ እርማትና ምግቤ ምላሽ ይሰጣቸው።

ክፍለጊዜ አስራ ስምንት

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

### ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-

- የገቢርና የተገብሮ ግሶችን በአረፍተነገሮች ውስጥ ይጠቀማሉ።

## በገቢርና በተገብሮ ግሶች አረፍተነገር መመስረት

### መልመጃ ስምንት

የዕለቱ ትምህርት በገቢርና በተገብሮ ግሶች አረፍተነገር መመስረትን የተመለከተ ነው። እባክዎ መምህር በተማሪ መጽሀፍ ላይ የቀረበውን ማስታወሻ መነሻ አድርገው ስለገቢርና ተገብሮ ግሶች ገለጻ ያድርጉላቸው። በመቀጠልም በፊደል ተራ ሀ እና ለ ስር የቀረቡትን መለማመጃዎች ደብተራቸው ላይ በመጻፍ በትዕዛዛቱ መሰረት እንዲሰሯቸው ያድርጉ። በገቢር እና ተገብሮ ግሶች ልየታ ላይ ተማሪዎችዎ የሚቸገሩ ከሆነ ከሚያገኟቸው የአማርኛ ሰዋስው መጽሐፍት ወይም ሌሎች አጋዥ መጽሐፍት መረጃ በማጠናቀር ተጨማሪ ማብራሪያና መልመጃዎችን አዘጋጅተው ሊሰጧቸው ይችላሉ።

## 4. ግምገማ

- በትኩረት አዳምጠው አጫጭር ማስታወሻ መያዛቸውን ያረጋግጡ።
- ያዳመጡትን ምንባብ ጭብጡን መለየታቸውን ያረጋግጡ፡፤
- በአረፍተነገሮች ውስጥ የተጓደሉትን ሀሳቦች ማሟላታቸውን ይመልከቱ፡፤

- ጠይቀው ያገኙትን ለክፍል ጓደኞቻቸው ማቅረባቸውን ይከታተሉ
- ያነበቡትን የምንባብ ጭብጥ መረዳታቸውን ይለዩ።
- የመንስኤና ውጤት ግንኙነት ያላቸውን ሀሳቦች መለየታቸውን ያረጋግጡ።
- ለቃላት አውዳዊ ትርጉም መስጠታቸውን ያረጋግጡ።
- ለቃላት ተመሳሳይ ትርጉም መስጠታቸውን ይከታተሉ።
- ለቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ መስጠታቸውን ያረጋግጡ።
- በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ተራኪ ድርሰት መጻፍቸውን ይከታተሉ።
- በተራኪ ድርሰት አወቃቀር ተገማግመው ተራኪ ድርሰት መጻፋቸውን ይከታተሉ።
- ገቢርና ተገብሮ ግሶችን መለየታቸውን ያረጋግጡ
- በገቢርና ተገብሮ ግሶች አረፍተ ነገር መመስረታቸውን ይመልከቱ፡፤

# 5. የመልጀዎችና ተግባራት የሚጠበቁ መልሶች

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

### ቅድመ ማዳመጥ

1. ልደት፣ ጋብቻና ሞት ወዘተ የሚመዘገብበት
2. በርካታ ጥቅሞች አሉት (ተማሪዎቹ የሚያቀርቡት ማንኛውም ተቀባይነት ያለው ምላሽ)

### የማዳመጥ ጊዜ

1. ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ
2. ጋብቻና ፍቺ

### አዳምጠ መረዳት

#### መልመጃ አንድ

**ሀ. በቃል የሚመለሱ የተለያዩ ጥያቄዎች**

1. ልደት፣ ጋብቻና ሞት
2. ልደት፣ ጋብቻና ሞት ናቸው።

3. ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ወሳኝ የሚባሉና ለማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ውሳኔዎች ጠቀሜታ ያላቸው መረጃዎች የሚደራጁበት መሆኑን (እነዚህም ልደት፣ ጋብቻና ሞት ናቸው)

**ለ. የተጓደሉትን ማሟላት**

1. የልደት፣ የጋብቻና

**ለ. የተጓደሉትን ሀሳቦች ማሟላት**

1. ሞት፣ ውልደት፣ ጋብቻና ፍቺ
2. የወሳኝ ኩነት ምዝገባ
3. ልደትና ሞት

## ተግባር አንድ

የተለያዩ ተቀባይነት ያላቸው መልሶች

## ተግባር ሁለት

የተሰበሰበ መረጃን መሰረት አድርገው የሚቀርቡ የተለያዩ መልሶች

## ተግባር ሦስት

1. ለማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ውሳኔዎች በግብአትነት ስለሚውሉ …
2. ልደትና ሞት
3. የህዝብ ብዛት ቁጥር፣ የሚያስፈልግ በጀት፣ የህዝብ ምጣኔ መቆጣጠሪያበተግባራት ሁሉ በዚህ ስለሚመራ
4. ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ውሳኔዎች የሚሰጡት ወሳኝ ኩነት መረጃ የሚቀብለውን መረጃ መሰረት አድርጎ በመሆኑ ወዘተ

## ተግባር አራት

ተቀባይነት ያላቸው የተለያዩ መልሶች

## ተግባር አምስት

የዳሰሳ ጥናት አይነት ስለሆነ መረጃው በአግባቡ ተሰብስቦ መቅረብ አለበት

# ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

## ቅድመማንበብ ጥያቄዎች

ተማሪዎቹ የሚሰጧቸውና ከጥያቄዎቹ በተያያዘ የሚሰጡ ማናቸውም መልሶች

## የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. በምጣኔ ሀብት ዕድገት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አለው፤ በታዳጊ አገሮች ማኅበራዊ፣ ምጣኔሀብታዊና ፖለቲካዊ ችግሮችን ያስከትላል፤ በምግብ አቅርቦትና በተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ተጽዕኖ ያሳርፋል
2. ምርታማ የሆነ የሰው ሀይል በብዛት ያለበት ከሆነ የህዝብ ቁጥር መጨመሩ ምጣኔ ሀብቱን ሊያሳድገው ይችላል

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

**ሀ.** 1. ምርት እንዳይቀንስና ድህነት እንዳይስፋፋ

2. ተቃራኒ ወይም ተነጻጻሪ ሀሳብ
3. የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ለምጣኔ ሀብታዊ ዕድገት ጠቃሚ ነው
4. <u>ጠቀሜታ</u>፡ ከተሜነትን ያስፋፋል፣ መሰረታዊ ልማትን (መንገድ፣ መብራት. ት/ት ቤት) በተናበበ መልኩ ለማቅረብ ያስችላል፣ ፈጠራን ያበረታታል (ተፎካካሪ ስለሚበዛ)፤ <u>ጉዳቶች</u>፡ አካባቢያዊ ብክለት ሊከሰት ይችላል፣ ለወረርሺኝ ያጋልጣል፣ ጠንክሮ የማይሰራ ማህበረሰብ ከበዛበት ለምጣኔ ሀብት ውድቀት ትልቅ ሚና አለው
4. የአገርን ዕድገት ለማፋጠን የተመጣጠነ የሕዝብ ቁጥር ዕድገትን በማምጣት ዜጎችን የልማት ተጠቃሚ ማድረግ ይቻላል
5. (ምክንያታዊ የሆኑ የተለያዩ መልሶች)
6. (ምክንያታዊ የሆኑ የተለያዩ መልሶች)
7. በአሁኑ አያያዝ የህዝብ ቁጥር መጨመሩ ከምጣኔ ሀብት እድገቱ ጋር እየሄደ ስላልሆነ አሳሳቢ ነው

**ለ. የምርጫ ጥያቄዎች**

1. ሀ
2. ለ
3. ሀ
4. መ
5. ለ

6. ሀ
7. ሐ


## መልመጃ ሶስት

### ሐ. የምክንያትና ውጤት ግንኙነት ያላቸውን ሀሳቦች መለየት

1. ምክንያት:-የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በአገር ሀብት ላይ ጫና መፍጠር
   ውጤት፡ አሉታዊ ተጽዕኖ ማምጣት
2. ምክንያት:-የሕዝብ ቁጥር ማደግ የዕውቀት አማራጮች እንዲሰፉ ያደርጋል
   ውጤት፡ አሁን የሰው ልጆች የደረሱበትን የዕድገት ደረጃ ማመልከት
3. ምክንያት:-በማኅበረሰቡ ውስጥ የሰለጠኑ ሰዎች ቁጥር በርካታ መሆን
   ውጤት:-የምጣኔ ሀብታዊ ዕድገት ይፋጠናል
4. ምክንያት፡ የስራ ፈጠራ ዕድል አለማደግ
   ውጤት፡ ለፀጥታ ችግር፣ ለወንጀልና ለስደት መዳረግ
5. ምክንያት:- የህዝብ ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ መጨመር
   ውጤት:- መሰረታዊ ፍላጎት ማሟላት አዳጋች መሆን

## መልመጃ አራት

ሀ.



ለ. (የተለያዩ መልሶች)

# ትምህርት አራት፡ቃላት

## መልመጃ አምስት

**ሀ. አውዳዊ ፍቺ መስጠት**

1. ተግባቦት
2. ተጽእኖ
3. መደሰት
4. ጀማሪ
5. አስፈላጊው/ዋናው
6. ብቃት/ችሎታ
7. መስማማት
8. ባዶ መሆን/ መንጠፍ
9. ተግባራዊ
10. ማኅልበት

**ለ. ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ መስጠት**

1. ለውጥ
2. ትንቢያ
3. የራስ
4. ቅርርብ
5. ጠቋሚ
6. መሆን
7. አሳሳቢ
8. መደዳ
9. ፍልሰት
10 አስቸጋሪ

(ቃላቱን በመጠቀም የሚመሰረቱ የተለያዩ አረፍተነገሮች)

## መልመጃ ስድስት

**ሀ. ለቃላት ፍካሬያዊ ፍቺ መስጠት**

1. ስልጣን 3. ብልጥ/ንቁ 5. በጣም ተናድዳ
2. ትዳር 4. ኅበዝ

**ለ.** (ተማሪዎች የሚሰሯቸው የተለያዩ መልሶች)

## መልመጃ ሰባት

| | **እማሬያዊ ፍቺ** | **ፍካሬያዊ ፍቺ** |
|---|---|---|
| **ሐ.** | 1. የዱር አውሬ፣ ስጋ በል | ብዙ የሚበላ፣አግበስባሽ |
| | 2. የቤት እንስሳት፣ ሳር በል | ሰነፍ፣ ስራ የማይወድ |
| | 3. በራሪ አእዋፍ | የዋህ |
| | 4. ስራ ፈታ | ሞተ |
| | 5. በደረቱ የሚሳብ ተናዳፊ አውሬ | ተንኮለኛ |
| | 6. ሄደ | ከዚህ አለም በሞት ተለየ |
| | 7. ጉልበት አጣ/ዛለ/ | ህይወቱ አለፈ |
| | 8. ከማዕድን የሚሰራ ጠንካራ ቁስ | ጠንካራ ሰው |
| | 9. የቤት እንስሳት፣ሳር በል | የዋህ፣ ምንም ተንኮል የሌለበት |
| | 10. ለጦር የሚሆን አውሮፕላን | ፈጣን፣ ቶሎ የሚደርስ |

**መ. (የተለያዩ አረፍተነገሮች)**

# ትምህርት አምስት: መጻፍ

## ተግባር ሰባት

(ተማሪዎች የሚጽፉት ስለትህርት ቤት አመሰራረት የሚገልጽ ተራኪ ድርሰት)

## ተግባር ስምንት

(ቤተመጽሐፍ በመጎብኘት ተራኪ ጽሑፍ አንብበው የሚያቀርቡት ዘገባ)

## ተግባር ዘጠኝ

(ተማሪዎች የየራሳቸውን ህይወት ታሪክ ጽፈው ያቀርባሉ)

## ተግባር አስር

(የህዝብ ቁጥር በምጣኔ ሀብት ላይ ያለውን ተጽዕኖ በተመለከተ የሚጻፍ አንቀጽ)

## ትምህርት ስድስት፡ሰወስው

### መልመጃ ስምንት ሀ.

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| አልተጨመረም (ተገብሮ) | ደገመ (ገቢ.ር) | ፈቀደ (ገቢ.ር) | ተሞገተ (ተገብሮ) | አመለጠ (ገቢ.ር) |
| ተነገረ (ተገብሮ) | ተፈታ (ተገብሮ) | ታረሰ (ተገብሮ) | ታወቀ (ተገብሮ) | በላ (ገቢ.ር) |
| ተፈረመ (ተገብሮ) | ታረመ (ተገብሮ) | መሰለ (ገቢ.ር) | ተመከረ (ተገብሮ) | ተጠጣ (ተገብሮ) |
| ተከበረ (ተገብሮ) | አከለ (ገቢ.ር) | ተቀመረ (ተገብሮ) | ሰማ (ገቢ.ር) | ሰበሰበ (ገቢ.ር) |

**ለ.** (የተለያዩ መልሶች)

# ምዕራፍ ስድስት

# በረሃማነት

(የክፍለጊዜ ብዛት 9)

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- እያነበቡ ትንታኔ በመስጠት ጽሁፍን ይገመግማሉ::
- የበረሃማነት ጽንሰሀሳብን ያብራራሉ::
- ምንባቡን አቀላጥፈው በማንበብ ማጠቃለያ ይሰጣሉ::
- በረሃማነት በአየር ንብረት ለውጥ ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት ይተነትናሉ::
- የገላጭ ድርሰትን መዋቅር ይለያሉ::
- ስሜቶቻቸውን ለመግለጽ ፍካሬያዊ ቃላትን ይጠቀማሉ::
- አገልግሎታዊ አ/ነገሮችን ይጽፋሉ::

## 2. የትምህርት ይዘት

### 2.1 ማዳመጥ

- የሚነበበውን ጽሁፍ ማዳመጥ
- የተለያዩ ተግባራትን ለማከናወን ምንባቡን ማዳመጥ
- የምንባቡን ዋና መልዕክት ለመለየት ማዳመጥ

### 2.2 መናገር

- ጤናማ አፈር እንዴት መፍጠር እንደሚቻል ማስረዳት
- የተፈጥሮና የኬሚካል ማዳበሪያ ልዩነታቸውን መተንተን
- የተፈጥሮ ማዳበሪያ ጥቅሙን መዘርዘር
- ያዳመጡትን ምንባብ ፍሬሀሳቡን መናገር

### 2.3 ማንበብ

- በረሃማነትና ድርቅ የሚለውን ምንባብ ማንበብ
- የየአንቀጾችን መልዕክት ለማግኘት ማንበብ

- የተለያዩ ጥያቄዎችን ለመመለስ ማንበብ
- የመንስኤና ውጤት ግንኙነት ያላቸውን ሀሳቦች ለመለየት ማንበብ

## 2.4 ቃላት

- የቃላት ፍካሬያዊ ፍቺ
- የቃላት እማሬያዊ ፍቺ

## 2.5 መጻፍ

- ገላጭ ድርሰት መጻፍ
- እንደገና አስተካክሎ መጻፍ

## 2.6 ሰዋስው

- አገልግሎታዊ አረፍተነገሮች

# 3. የማስተማሪያ ዘዴ

- የአዳምጦ መረዳት ማስተማሪያ ስልቶችን መጠቀም
- ያዳመጡትን መሰረት አድርገው የተወያዩበትን እንዲናገሩ ማበረታታት
- መፍትሄ እንዲያመነጩ የሚያስችሉ ተግባራትን ሰጥቶ ማለማመድ
- መስተጋብርን እንዲፈጥሩ የሚያስቻሏቸውን ተግባራትማቅረብ
- የአንብቦ መረዳት ስልቶችን ተግባራዊ አድርገው ‹‹የገዳ ስርዓት ባህላዊ ቅርስ›› የሚለውን ምንባብ እንዲያነቡ ማድረግ
- እንዲወያዩ የሚጋብዙና ማብራሪያ የሚፈልጉ ጥያቄዎችን ማቅረብ
- በአረፍተነገር ውስጥ ያሉ ቃላትን አውዳዊ ትርጉም እንዲሰጡ አቅጣጫ ማሳየት
- በቀረበላቸው ርእስ መነሻነት ሶስት አንቀጽ ያለው አመዛዛኝ ድርሰት ምሳሌ አቅርቦ እንዲጽፉ ማገዝ
- ስዕል ተመልክተው የስዕሉን ማጠቃለያ እንዲጽፉ ማድረግ
- ስለአገልግሎታዊ ዓረፍተነገሮች የሚያውቁትን እንዲናገሩ መቀስቀስ

ክፍለጊዜ አንድ

# ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

### ተማሪዎችይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-

- በንቃት አዳምጠው ምንባብን ይገመግማሉ፡፡
- ያዳመጡትን ፍሬ ሀሳብ ይለያሉ፡፡

## ቅድመ ማዳመጥ

በትምህርት አንድ ስር በክፍለ ጊዜ አንድ የተማሪዎችን የማዳመጥ ፍላጎት የሚያነሳሱ ሶስት ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ በሶስቱ ጥያቄዎች ላይ ከተማሪዎች ጋር ከተነጋገሩ በኋላ ወደ ዋናው ትምህርት ይግቡ፡፡ በመጀመሪያ ‹‹ጤናማ አፈር ለጤናማ ህይወት›› በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ የመጀመሪዎቹን ሶስት አንቀጾች ያንብቡላቸው፡፡ ከዚያም ቆም ብለው በማዳመጥ ጊዜ የቀረቡ ጥያቄዎችን ያሰሯቸው፡፡ በመቀጠል የተቀረውን የምንባብ ክፍል ያንብቡላቸው፡፡ከዚያም ያዳምጠ መረዳት ጥያቄዎችን ባዳመጡት መሰረት በቃላቸው እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡በመጨረሻም በክፍለጊዜ ሁለት ተግባር አንድን በቤታቸው ሰርተው እንዲመጡ ይዘዟቸው፡፡

## ጤናማ አፈር ለጤናማ ህይወት

ጤናማ አፈር እንዲኖር አፈሩ ውሀ የማስረግና እርጥበት የመያዝ አቅሙን ማሻሻል ተገቢ ነው። ይህ የተመረጠው በሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች ነው።አንደኛው ፍግና ብስባሽ የአፈርን ለምነት በዘላቂነት የማሻሻልና የሰብል ምርትን ለመጨመር የሚያስችል መሆኑ ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ አርሶ አደሩ የኢኮኖሚ አቅሙን የሚፈታተነውን ሰው ሰራሽ የኬሚካል ማዳበሪያ መጠቀሙን እንዲቀንስ ማስቻሉ ነው፡፡ በፋብሪካ የሚመረተው የኬሚካል ማዳበሪያዎች ምርትን የመጨመር አቅም ቢኖራቸውም ዘላቂ አይደሉም። ይልቁንም በተደጋጋሚ ጥቅም ላይ ከዋሉ በአፈሩ ውስጥ የሚገኙ ለአፈር ለምነት አስፈላጊ የሆኑ ደቂቅ ህዋሳትን ያጠፋሉ።

በተፈጥሮ ማዳበሪያ (ኮምፖስት) የዳበረ አፈር ሰው ሰራሽ ማዳበሪያ ካልተጨመረበት ውሀን በሁለት ሳምንታት የማቆየት አቅም አለው። ይህም ዝናብ አጠር በሆኑ አካባቢዎች ሰብል በእርጥበት እጥረት እንዳይጎዳ ያስችለዋል። ሌላው በተፈጥሮ

ማዳበሪያ የበለጸገ አፈር በከፍተኛ ደረጃ የአፈር መሸርሸርን መቋቋም ይችላል። ይህም የሚሆንበት ምክንያት ብስባሽ ያለበት አፈርየአፈሩን አካላት ርስ በርስ እንዲያያዙ ስለሚያደርግ አፈሩ አይሸረሽርም።ይህም ውሃው ቆይቶ በምንጭ መልክ እንዲወጣ ያስችላል።

## የማዳመጥ ጊዜ

**እዚህጋ ማንበብዎን በመግታት እስካሁን ያዳመጡትን መሰረት አድርገው ለአርሶ አደሩ ምርት ማነስ ዋነኛ ምክንያት ምን እንደሆነና የኬሚካል ማዳበሪያዎች በግብርናው ምርት ላይ ያላቸውን ተጽዕኖ ይጠይቋቸው፡፡ እንዲሁም የተቀረው የምንባብ ክፍል በተፈጥሮ የዳበረ አፈር ምን አይነት ጥቅም ያለው መሆኑን እንዲገምቱ ያድርጉ፡፡**

በነዚህ አካባቢዎች ደርቀውና ጠፍተው የነበሩ ምንጮችና ወንዞች በሁለትና ሶስት አመታት ውስጥ እንደገና መፍሰስ ጀምረዋል። ሌላው የተፈጥሮ ማዳበሪያ ጥቅም አረምን ለመከላከል የሚያስችል መሆኑ ነው። አብዛኞቹ አረሞች በተፈጥሮ ደካማ የሆነ ሰብልን የሚያጠቁ ናቸው። አፈሩ ለምነት የሌለው ከሆነ በላዩ ላይ የሚበቅለው ሰብል ጥንካሬ ስለማይኖረው በቀላሉ በአረም የሚጠቃ ይሆናል።

https://agriprofocus.com/upload/wegelisue ተሻሽሎ የተወሰደ

ክፍለጊዜ ሁለት

# ትምህርት ሁለት መናገር

### ተማሪዎችይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-

- በተሰጠው ርዕሰ ጉዳይ ላይ በራስ የመተማመን ስሜትን በተላበሰ መልኩ ንግግር ያደርጋሉ፡፡

## መልመጃ ሁለት

‹‹ጤናማ አፈር ለጤናማ ህይወት›› በሚል ርዕስ የቀረበው ምንባብ ተማሪዎች ሲነበብላቸው ያዳመጡትን መሰረት አድርገው የቀረቡትን ጥያቄዎች ላይ ከተወያዩ በኋላ በቃል ማቅረብ የዚህ ክፍለ ጊዜ ትምህርት ነው፡፡ መምህር እባክዎ ምንባቡን አንድ ጊዜ ያንብቡላቸውና በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ በቡድን እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ ከዚያም የተወያዩትን በቡድን ተወካያቸው አማካኝነት በቃላቸው እንዲመልሱ ያድርጉ፤

ያበረታቷቸው፡፡በመጨረሻም በክፍለጊዜ አንድ በቤታቸው ሰርተው የመጡትን እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

ክፍለጊዜ ሦስት

# ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

**ተማሪዎችይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-**

- የቀረበውን ምንባብ አቀላጥፌው በማንበብ ማጠቃለያ ይሰጣሉ፡፡

## ቅድመ ንባብ

የዕለቱ ትምህርት ‹‹በረሃማነትና ድርቅ›› በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ማንበብ ነው፡፡ ተማሪዎች ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት ስዕሉን ተመልክተው የስዕሉን መልዕክት እንዲናገሩ፣ በረሃማነት በሰው ልጆች ላይ የሚያስከትለውን ተጽዕኖ እንዲዘረዝሩ፣ የምንባቡን ርዕስ ተመልክተው በምንባቡ ውስጥ ምን ምን ሀሳቦች ሊነሱ እንደሚችሉ እንዲገምቱ ያድርጉ፡፡ ከዚያም ምንባቡን እንዲያነቡ ይዘዟቸው፡፡ ከዚያም ቆም ብለው ከላይ ያነበቡትን መሰረት አድርገው የቀረቡትን የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎችን ያሰሯቸው፡፡ በመቀጠልም የተቀረውን የምንባብ ክፍል እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡

ክፍለጊዜ አራት

## ድህረ ንባብ

### መልመጃ ሶስት

በመልመጃ ሁለት ስር ምንባቡን መሰረት አድርገው የወጡ ጥያቄዎች አሉ፡፡ የመጀመሪያው ለቀረቡት ጥያቄዎች በጽሁፍ መመለስ ነው፡፡ ሁለተኛው የምርጫ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ሁሉንም ጥያቄዎች በትዕዛዙ መሰረት ከነበቂ ምክንያት ጋር እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡ግብረ መልስም ይሥጧቸው፡፡ቀጥሎም ተግባር ሁለትን በትዕዛዛቸው መሰረት እንዲያከናውኑ ያድርጉ፡፡ ይከታተሏቸው፡፡ተቀብለውም አስተያየት ይስጧቸው፡፡

ክፍለጊዜ አምስት

# ትምህርት አራት፡ ቃላት

### ተማሪዎችይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-

- ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ይሰጣሉ፡፡
- ስሜቶቻቸውን ለመግለጽ እማሬያዊና ፍካሬያዊ ቃላትን ይጠቀማሉ፡፡

## መልመጃ አራት

በዚህ ክፍለ ጊዜ የቀረበው ይዘት የመጀመሪያው ከምንባቡ ለወጡ ቃላት አውዳዊ ትርጉም መስጠት ነው፡፡ ሁለተኛው የቃላት እማሬዊና ፍካሬዊ ፍች ነው፡፡ የዕለቱ ትምህርት ለቃላት አውዳዊና ተመሳሳይ ትርጉም መስጠት እንደሆነ በመግለጽ ከምንባቡ ለወጡ ቃላት አውዳዊ ትርጉም እንዲፈልጉ ይዘዙ ግብረ መልስም ይስጧቸው፣ ቀጥሎ የሚቀርበው ይዘትም እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች ነው፡፡ ስለእማሬያዊና ፍካሬያዊ ቃላት የሚያውቁትን ጠይቀው ምላሻቸውን ከተቀበሉ በኋላ ቀጥሎ የቀረበውን ማስታወሻ መነሻ አድርገው ማብራሪያ ያድርጉላቸው፡፡ ማስታወሻውም፡

## የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ

እማሬያዊ ፍቺ ቃሉ ሲባል ወይም ሲጠራ ወደ አእምሯችን የሚመጣው የቃሉ ትርጉም ነው፡፡ ፍካሬያዊ ፍች ደግሞ የአንድ ቃል ተጨማሪ/ተደራቢ ትርጉም ነው፡፡ ይህም ግለሰቡ ቃሉ ለወከለው ነገር የሚኖረው አተያይ/አመለካከት፣ ዝንባሌና እምነት ላይ ይመሰረታል፡፡

ለምሳሌ፡ ሰውዬው <u>ቁልፍ</u> ጣለ፡፡

ሰውዬው በመስሪያ ቤቱ ውስጥ <u>ቁልፍ</u> ሰው ነው፡፡

ከላይ ‹‹ቁልፍ›› የሚለው ቃል በሁለቱ አረፍተነገሮች ውስጥ የተለያየ ትርጉም አለው፡፡ በመጀመሪያው አረፍተነገር የቤት መክፈቻ የሚል ትርጉም ሲኖረው ይህም ቀጥተኛ/እማሬዊ/ ፍቺው ነው፡፡ በሁለተኛው አረፍተነገር እጅግ የሚፈለግ/ዋነኛ/ ሰው የሚል ሲሆን ይህም ተጨማሪ ወይም ፍካሬያዊው ፍቺ ነው፡፡

ከዚያም ለቀረቡ ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ሰጥተው እንዲመጡ የቤት ስራ ይስጧቸው፡፡

ክፍለጊዜ ስድስት

# ለቃላት አማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ መስጠት

## መልመጃ አምስት

በዚህ ክፍለ ጊዜ የቀረበው የትምህርት ይዘት የእማሬያዊና ፍካሬያዊ ቃላት ፍቺ የሚል ነው፡፡ በባለፈው ክፍለ ጊዜ የተሰጣቸውን ማብራሪያ በመከለስ በቤታቸው ሰርተው እንዲመጡ የታዘዙትን ከተማሪው ጋር በመሆን ይስሩ፡፡

ክፍለጊዜ ሰባት

## ትምህርት አምስት፡መጻፍ

**ተማሪዎችይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-**

- ገላጭ ድርሰት ይጽፋሉ፡፡
- የገላጭ ድርሰትን መዋቅር ይገመግማሉ፡፡

### ተግባር ሶስት

የዕለቱ ትምህርት ገላጭ ድርሰት መጻፍ እንደሆነ በመግለጽ ቀጥሎ የቀረበውን ማስታወሻ መነሻ አድርገው ስለገላጭ ድርሰት ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡

**ማስታወሻውም**

### ገላጭ ድርሰት

የገላጭ አጻጻፍ ስልት እይታን፣ ድምጽን፣ መንካትን፣ ሽታን ቅምሻን ይጠራል፡፡ ገለጻው በአምስቱ የስሜት ህዋሳት ላይ ይመሰረታል፡፡ ዋነኛ አላማው መልእክትን ማስተላለፍ ስለሆነ ለቃላት ምርጫ ልዩ ትኩረት ይሰጣል፡፡ ሀሳቦቹንም በምክንያትና ውጤት፣ በማወዳደርና ማነጻጸር፣ትረካን፣ ብያኔን፣ ሂደታዊ ትንተናን ይጠቀማል፡፡ እንዳንዳቸውን በተናጠል ስንመለከት፡

ምክንያትንና ውጤት፡ ክስተቶች ተከታትለው በሚመጡበት ጊዜ የመጀመሪያው ለሁለተኛው ክስተት መምጣት ምክንያት በመሆን ሀሳቦች ሲደራጁ ነው፡፡

ማወዳደርና ማነጻጸር፡ በተለያዩ ነገሮች መካከል ተመሳስሎና በተመሳሳይ ነገሮች መካከል ልዩነትን የማሳያ የአጻጻፍ ስልት ነው፡፡

**ተራኪ/ሁተታዊ፡ አንድ ነገር ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ያለውን ሂደት እየተነተነ ይተርካል፡፡ ትንተናውም በጊዜና በቦታ ወይም በአፈጻጸም ቅደምተከተል ላይ የተመሰረተ ነው፡፡**

**ብያኔ፡ የአንድን ነገር ምንነት ወይም ምን ማለትነት፣ በሌላ አማራጭ የአንድን ነገር ምን አለመሆን ላይ ያተኩራል፡፡**

***ምሳሌ***

**በምክንያትና ውጤት ስልት የተጻፈ**

ከስር መሬቱ እንደረመጥ ያቃጥላል፡፡ ከላይ የአየሩ ወበቅ እንደእሳት ላንቃ ይጋረፋል፡፡ ሳር ቅጠሉ ደርቋል፡፡ ዛፎቹ ከሰል መስለዋል፡፡ ወፎቹ ተሰደዋል፡፡ ጎድናቸው አንድ ሁለት ተብሎ የሚቆጠር በሞትና በህይወት መካከል የሚንገዳገዱ ጣዕረ ሞት የሚመስሉ የቤት እንስሳት መጠለያ አጥተው በየሜዳው በቁም ያንቀላፋሉ፡፡...

በተማሪው መማሪያ መጽሀፍ ላይ ካለው ምሳሌ በተጨማሪ ተጨማሪ ምሳሌ ያቅርቡላቸው፡፡ ከዚያም በቀረቡላቸው ርዕሶች መነሻ አንድ ገላጭ ድርሰት ጽፈው እንዲመጡ ይዘዟቸው፡፡ ከዚያም ተቀያይረው የድርሰታቸውን አወቃቀር እንዲገማገሙ ያድርጉ፡፡እርስዎም አስተያየት ይሥጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ስምንት**

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

**ተማሪዎችይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-**

- አገልግሎታዊ አረፍተነገሮችን ይጽፋሉ፡፡
- ገቢርና ተገብሮ ግሶችን ይለያሉ፡፡

**አገልግሎታዊ አረፍተነገሮች**

**መልመጃ ስድስት**

የዕለቱ ትምህርት አገልግሎታዊ አረፍተነገሮች የሚል ነው፡፡ በተማሪው የመማሪያ መጽሀፍ ላይ የቀረበውን ማስታወሻ መነሻ አድርገው ስለአገልግሎታዊ አረፍተነገሮች ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡

**ማስታወሻውም**

## አገልግሎታዊ አረፍተነገሮች

አገልግሎታዊ አረፍተ ነገሮች፡ በአራት ተከፍለው ሊታዩ ይችላሉ። እነሱም የሚከተሉት ናቸው።

1. ሀተታዊ አረፍተ ነገር፡ ቀጥተኛ ሀሳብ የሚገለጽበት ነው።
   ምሳሌ፡ *ቶሌራ ጎበዝ ሾፌር ነው።*
2. ጥያቄያዊ አረፍተ ነገር፡ ምላሽ የሚሻ ሀሳብ የሚገለጽበት ነው።
   ለምሳሌ፡ *ለምን የቤት ስራ አልሰራህም?*
3. ትእዛዛዊ አረፍተ ነገር፡ አንድ ሰው አንድን ስራ በትብብር ወይም አስገዳጅ በሆነ ሁኔታ እንዲሰራ ለማድረግ መልእክት የሚተላለፍበት አረፍተ ነገር ነው።
   ምሳሌ፡ *ያዋስኩሽን መጽሀፍ አምጭልኝ!*
4. አጋናኝ አረፍተነገር፡ *መደነቅን፣ መገረምን፣ መደንገጥንና የመሳሰሉትን ስሜቶች ለመግለጽ እንጠቀምበታለን።*
   ምሳሌ፡ *እንዴት ያለ ጭንቅላት ሰጥቷታል!*

ከዚያም አምስት አምስት አገልግሎታዊ አረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ ያድርጉና ተቀብለው ይመልከቱ፡፡

**ክፍለጊዜ ዘጠኝ**

**መልመጃ ሰባት**

የዕለቱ ትምህርት አገልግሎታዊ ዓረፍተነገሮችን መጻፍ የሚል ነው፡፡ በባለፈው ክፍለጊዜ ስለአገልግሎታዊ ዓረፍተነገሮች የተማሩትን በማስታወስ ለእያንዳንዳቸው አገልግሎታዊ ዓረፍተነገሮች ምሳሌ የሚሆኑ ሶስት ሶስት ጽፈው ለእርስዎ እንዲያሳዩ ያድርጉ ፡፡ እርስዎም ተቀብለው በጽሁፍ አስተያየት ይስጡ፡፤

## 4. ግምገማ

- በትኩረት አዳምጠው አጫጭር ማስታወሻ መያዛቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ያዳመጡትን ምንባብ ጭብጡን መለየታቸውን ያረጋግጡ፡፤
- ጠይቀው ያገኙትን ለክፍል ጓደኞቻቸው ማቅረባቸውን ይከታተሉ፡፡
- ያነበቡትን የምንባብ ጭብጥ መረዳታቸውን ይለዩ፡፡

- ለቃላት አውዳዊ ትርጉም መስጠታቸውን መልከቱ፡፡
- ለቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ መስጠታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ገላጭ ድርሰት መጻፍቸውን ይከታተሉ፡፡
- በገላጭ ድርሰት አወቃቀር ተገማግመው ገላጭ ድርሰት መጻፋቸውን ይከታተሉ፡
- አገልግሎታዊ አረፍተነገሮችን መመስረታቸውን ይመልከቱ፡፡
- ገቢርና ተገብሮ ግሶችን መለየታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- በገቢርና ተገብሮ ግሶች አረፍተ ነገር መመስረታቸውን ይመልከቱ፡፡

# 5. የተመረጡ መልመጃዎች መልስ

## ትምህርት አንድ

### መልመጃ አንድ

**ሀ. የተለያዩ ጥያቄዎችን በቃል መመለስ**

1. የተለያዩ መልሶች
2. በአፈር ውስጥ ብስባሽ መጨመር
3. የሚፈረፈር ነው
4. የተፈጥሮ ማዳበሪያ ስለተጨመረበት
5. እንክርዳድ፣ አቀንጭራ እና ፓርቲኒየም
6. የተለያዩ መልሶች

**ለ. የምርጫ ጥያቄዎች**

1. ለ
2. ሀ
3. መ
4. መ
5. መ

## ትምህርት ሶስት

### መልመጃ ሶስት

**ሀ. በጽሁፍ የሚመለሱ የተለያዩ ጥያቄዎች**

1. በረሃማነትንና ድርቅን መከላከል፣ ዛፎችን መትከል
2. ዛፎችን መትከል፣ ዘላቂነት ያለው የመሬት አጠቃቀምን ተግባራዊ ማድረግ

ሌሎችን በዚሁ መሰረት ያሰሯቸው፡፡

**ለ. የምርጫ ጥያቄዎች**

1. መ
2. መ
3. ሀ
4. ለ
5. መ

# ትምህርት አራት

## መልመጃ አራት

**ሀ. የቃላት ተመሳሳይ ፍቺ**

| | |
|---|---|
| 1. ረ | 5. ሀ |
| 2. ሐ | 6. ሰ |
| 3. ሸ | 7. ለ |
| 4. መ | 8. ሠ |

| ቃላት እማሬዊና ፍካሬዊፍቺ | እማሬያዊ ፍቺፍ ካሬያዊ ፍቺ |
|---|---|
| 1. ማር የምትሰጥ ነፍሳት | ፈጣን፣ ጎበዝ |
| 2. መጠለያ/መኖሪያ ቤት/ | ትዳር/ኑሮ |
| 3. ቤት አልተገኘም | ሞተ |
| 4. የሚጠጣ፣ፈሳሽ | ደከመ፣዗ለ |
| 5. ተክል | ረኀም |

# ትምህርት ስድስት

## መልመጃ ስድስት

ሀተታዊ፡-2፣5

ጥያቄዊ፣ 3፣8

ትዕዛዛዊና፡-1፣6

አጋናኝ፡-4፣7

# ምዕራፍ ሰባት

# የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ

(የክፍለጊዜ ብዛት 9)

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- መረጃ ሰጪ ጽሁፍን በጥልቀት በማዳመጥ ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡
- የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ ጽንሰሃሳብንና የሚያስከትለውን ተጽእኖ ያብራራሉ፡፡
- በአንድ ጉዳይ ላይ ይደራደራሉ፡፡
- አገልግሎታዊ አረፍተ ነገሮችን ያወዳድራሉ፡፡
- ቃላትን ከተቃራኒ ፍቻቸው ጋር ያዛምዳሉ፡፡

## 2. የትምህርት ይዘት

### 2.1 ማዳመጥ

- የሚነበበውን ጽሁፍ ማዳመጥ
- የምንባቡን ዋና መልዕክት ለመለየት ማዳመጥ

### 2.2 መናገር

- የህጻናት መብቶች የሚባሉትን በቃል ማቅረብ
- ክርክር ማድረግ

### 2.3 ማንበብ

- ስዕል ተመልክቶ ማንበብ
- የህጻናት መብትና የጉልበት ብዝበዛ የሚለውን ምንባብ ማንበብ
- የየአንቀጾችን መልዕክት ለማግኘት ማንበብ

### 2.4 ቃላት

- የቃላት ተቃራኒፍቺ

## 2.5 መጻፍ

- የህጻናት መብቶችን መጻፍ
- የአንቀጾችን ፍሬሀሳብ መጻፍ
- የምንባቡን ፍሬ ሀሳብ በአንቀጽ መጻፍ

## 2.6. ሰዋስው

- አገልግሎታዊ አረፍተነገሮች
- ገቢርና የተገብሮ ግሶችን መለየት

# 3. የማስተማሪያ ዘዴ

- መረጃ ሰጪ ጽሁፍን በጥልቀት የማዳመጥ ስልትን ተግባራዊ እንዲያደርጉ አቅጣጫ ማሳየት፡፡
- የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ ጽንሰሃሳብንና የሚያስከትለውን ተጽእኖ እንዲናገሩ ማነሳሳት፡፡
- የሚያዳምጡትን ጽሁፍ አውዳዊ አድርጎ ማቅረብ
- የማንበብና የመጻፍ መልመጃዎችን መስጠት
- ክርክር እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት
- የቀረበ ቃል ፍቺን የቀደመ እውቀታቸውን ተጠቅመው እንዲናገሩ ማትጋት
- የምንባቡን ርዕስ ተመልክተው ምንባቡ ስለምን እንደሚያወሳ እንዲገምቱ ማነሳሳት
- ስዕልን ተመልክተው ስለስዕሉ እንዲናገሩ መጠየቅ
- ያነበቡትን የምንባብ አንቀጽ መነሻ አድርገው የተቀረው የምንባብ ክፍል ስለምን እንደሚያወሳ እንዲናገሩ ማበረታታት
- ቀስቃሽ ጥያቄዎችን በማቅረብ ተማሪዎች እንዲወያዩ ማድርግ
- ከክፍል ውጪ የሚሰሯቸውን ተግባራት መስጠት
- ለቃላት ተመሳሳይ ትርጉም እንዲሰጡ ምሳሌ መስጠት
- ለቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ እንዲሰጡ ፍንጭ መስጠት
- በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ገላጭ ድርሰት እንዲጽፉ አቅጣጫ ማመልከት
- አገልግሎታዊ አረፍተ ነገሮችን እንዲለዩ ማበረታታት

ክፍለጊዜ አንድ

# ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

### ተማሪዎችይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-

- መረጃ ሰጭ ጽሁፍን በማዳመጥ ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡

## ቅድመ ማዳመጥ

በትምህርት አንድ ስር በክፍለ ጊዜ አንድ የተማሪዎችን የማዳመጥ ፍላጎት የሚያነሳሱ ሁለት ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ በሶስቱ ጥያቄዎች ላይ ከተማሪዎች ጋር ከተነጋገሩ በኋላ ወደ ዋናው ትምህርት ይግቡ፡፡ በመጀመሪያ "የህጻናት መብቶች" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ የመጀመሪያዎቹን ሶስት አንቀጾች ያንብቡላቸው፡፡ ከዚያም ቆም ብለው በማዳመጥ ጊዜ የቀረቡ ጥያቄዎችን ያሰሯቸው፡፡ በመቀጠል የተቀረውን የምንባብ ክፍል ያንብቡላቸው፡፡

# የህጻናት መብቶች

ህጻናት በእድሜያቸው ለጋነትና የዳበረ ማህበራዊ ህይወት ስለሌላቸው ህይወታቸውን ለሚፈታተኑ በርካታ አደጋዎች የተጋለጡ ናቸው፡፡ በቀላሉ በበሽታዎች ይጠቃሉ፤ ምግብ፣ መጠለያ ወዘተ.በራሳቸው ሊያሟሉ አይችሉም፡፡ ሊቆጣጠሯቸው ለማይችሉ በርካታ ሰው ሰራሽ አደጋዎች የተጋለጡ ናቸው፡፡ እነዚህን ሁሉ ችግሮች ተቋቁመውና አልፈው በህይወት መቆየት ይችሉ ዘንድ ወላጆች፣ ቤተሰቦች፣ ማህበረሰብ ልዩ ልዩ ድርጅቶችና መንግስት ሊያውቁላቸውና ሊያሟሉላቸው የሚገቡ መብቶች አሏቸው፡፡

## የማዳመጥ ጊዜ

ማንበብዎን ቆም አድርገው ቀደም ብለው ከዳመጡት የተረዱት የህጻናት መብቶች የሚባሉት ምን ምን እንደሆኑ ይጠይቁ፤ ቀጥለው በሚያዳምጡት ምንባብ ውስጥ የትኞቹ የህጻናት መብቶች እንደሚነሱ እንዲገምቱ ያድርጉ፡፡

ህጻናት በአካላቸው ማደግ ብቻ ሳይሆን አእምሯቸውም መጎልበት ይኖርበታል፡፡ ሞራላዊና መንፈሳዊ ብቃት እንዲኖራቸው በእሴቶችና በባህል መበልጸግ ይኖርባቸዋል፡ ፡ህጻናት መልካም ዜጎች እንዲሆኑ ግንዛቤያቸው፣ በተፈጥሮ ያገኟቸው ጸጋዎችና

ችሎታዎች በበቂ ሁኔታ መበልጸግ ይኖርባቸዋል፡፡እነዚህም እውን እንዲሆኑ ትምህርት፣ ጨዋታ፣ መዝናኛ ባህላዊ ድርጊቶች፣ ልዩ ልዩ ነጻነቶች፣ ስልጠናዎች፣ መረጃዎች፣ አመራርና ቁጥጥር ያስፈልጋቸዋል፡፡

ህጻናት ከማንኛውም አይነት ጥቃት የሚታደጉበት በጥቅሉ ጥበቃ የማግኘት ተብለው የሚታወቁ በርካታ መብቶች አሏቸው፡፡ ህጻናትን ከበደሎችና ጥቃቶች መጠበቅና መከላከል ካልተቻለ በህይወት መቆየታቸውም ሆነ እድገታቸው አደጋ ላይ ያደርሳሉ፡፡ እነዚህ በደሎችና ጥቃቶች አካላቸውን የሚያጎድሉ፣ ስሜታቸውን የሚጎዱ፣ ሞራላቸውንና መንፈሳቸውን የሚያላሽቁ ባጠቃላይ ኑሮአቸውንና ህይወታቸውን የሚያጨልሙ አደጋዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ ህጻናት በእድሜያቸው ለጋነት፣ የደረጀ ማህበራዊ ህይወት ስለሌላቸውና ራሳቸውን ችለው መኖር ስለሚሳናቸው ለበርካታ በደሎችና ጥቃቶች የተጋለጡ መሆኑን በማጤን ቤተሰብና መንግስት ልዩ ትኩረት በመስጠት ጥበቃ የማግኘት መብቶቻቸውን ሊያረጋግጡላቸው ይገባል፡፡

*የሰብአዊ መብት ትምህርት ማስፋፊያ ካዘጋጀው የህጻናት መብቶችና ሃላፊነቶች ትምህርት ማጣቀሻ መጽሀፍ እንዲስማማ ተደርጎ የተወሰደ*

### ክፍለጊዜ ሁለት

### ድህረ ማዳመጥ

### መልመጃ አንድ

በዚህ ክፍለጊዜ የትምህርት ይዘት ተማሪዎች ‹‹የህጻናት መብቶች›› በሚል ርዕስ የቀረበው ምንባብ ሲያነቡላቸው ያዳመጡትን መሰረት አድርገው የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃል መመለስ ነው፡፡መምህር እባክዎ ሁሉንም ጥያቄዎች ተማሪዎች ትክክለኛ መልስ ከነበቂ ምክንያታቸው ጋር እንዲመልሱ ያበረታቱዋቸው፡፡ተቀብለውም ይመልከቱላቸው፡፡ከዚያም በተግባር አንድ ስር በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ በጥንድ እየተወያዩ ማስታወሻ እንዲይዙ ያድርጉ፡፡የያዙትን ማስታወሻም በአስተዋጽኦ መልክ አደራጅተው አንቀጽ በመጻፍ እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡ሰርተው ባቀረቡት ተግባር ላይም አስተያየት ይሥጡ፡፡

ክፍለጊዜ ሦስት

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

**ተማሪዎችይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-**

- የህጻናት መብቶችን ይናገራሉ፡፡
- በአንድ ጉዳይ ላይ ይከራከራሉ፡፡

## ተግባር አንድ

በዚህ ክፍለ ጊዜ በይዘትነት የሚቀርበው ትምህርት የህጻናት መብቶች በቃል ማቅረብ የሚል ነው፡፡ ‹‹የህጻናት መብቶች›› በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ መሰረት በማድረግ የተዘረዘሩትን የህጻናት መብቶች በቃላቸው ዘርዝረው እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡ በመቀጠልም "ህጻናት ሲያጠፉ መቀጣት አለባቸው? ወይስ የለባቸውም?" የሚሉትን ሀሳቦች አንደኛውን ደግፈው ሌላይኛውን ተቃውመው ቡድን መስርተው እንዲከራከሩ ያድርጉ፡፡ በዚህ ጊዜ የክርክር አደራረግ መመሪያዎችን እንዲከተሉ ያድርጉ፡፡ክርክሩ ውስጥ ያልተሳተፉ ተከራካሪዎች ያቀረቡት ሀሳብ ምክንያታዊ መሆናቸውና አለመሆናቸው ላይ ሀሳብ በመስጠት እንዲሳተፉ ያበረታቱ፡፡

ክፍለጊዜ አራት

# ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

**ተማሪዎችይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-**

- ስዕልን አንብበው መልዕክቱን ይረዳሉ፡፡
- የቀረበላቸውን ምንባብ በጥልቀት ያነባሉ፡፡

## ቅድመ ንባብ

ተማሪዎች በቀጥታ ወደ ንባብ ከመግባታቸው በፊት ለማንበብ እንዲነሳሱ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡

- የቀረበውን ስዕል ተመልክተውስዕሉ ምን መልዕክት እንደሚያስተላልፍ
- በአካባቢቸው ሕጻናት ያለአቅማቸው ምን ምን ስራዎችን እንደሚሰሩ
- ርዕሱን በመመልከት በምንባቡ ውስጥ ምን ምን ሀሳቦች ይነሳል ብለው እንዲገምቱ

ከዚያም ‹‹የህጻናት መብቶች›› በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በትኩረት እንዲያነቡ ይዘዟቸው፡፡ ከዚያምተማሪዎች የምንባቡን ሁለት አንቀጾች አንብበው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ባነበቡት የምንባብ ክፍል ስለህጻናት ጉልበት ብዝበዛ ምን እንደተረዱ ይጠይቋቸው፤
- በተቀረው የምንባቡ ክፍል ስለህጻናት ጉልበት ብዝበዛ ምን ምን ነጥቦች ሊነሱ እንደሚችሉ እንዲገምቱ ያድርጓቸው፡፡ ከዚያም ንባባቸውን እንዲቀጥሉ ይዘዟቸው፡፡

### ክፍለጊዜ አምስት

## ድህረ ንባብ

### መልመጃ ሁለት

የዕለቱ ትምህርት በመልመጃ ሁለት ስር ምንባቡን መሰረት አድርገው የወጡ ጥያቄዎችን መስራት ነው፡፡ የመጀመሪያው ለቀረቡት ጥያቄዎች በጽሁፍ መመለስ የሚል ነው፡፡ ሁለተኛው የምንባቡ አንቀጾች የሚያስተላልፉትን መልዕክት መለየት የሚል ነው፡፡ ሁሉንም ጥያቄዎች ተማሪዎች ከበቂ ምክንያት ጋር እንዲመልሱ እያደረጉ ያሰሯቸው፡፡

### ክፍለጊዜ ስድስት

### መልመጃ ሶስት

በዚህ ክፍል ጊዜ የሚቀርበው ትምህርት በመልመጃ ሶስት ስር ምንባቡን መሰረት አድርገው የተዘጋጁየምርጫ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ የሁሉንም ጥያቄዎች መልሶች ተማሪዎች በትክክልና በተገቢው ሁኔታ መስራታቸውን እየጠየቁ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡በመቀጠልም በየአካባቢያቸው የህጻናት መብቶች አጠባበቅ ምን እንደሚመስል በቡድናቸው ከተወያዩ በኋላ የደረሱበትን በአንቀፅ አደራጅተው እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡ባቀረቡት አንቀጽ ላይም ገንቢ አስተያየት ይስጡ፡፡

### ክፍለጊዜ ሰባት

# ትምህርትአራት፡ ቃላት

**ተማሪዎችይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-**

- ለቃላት አውዳዊ ትርጉም ይሰጣሉ፡፡
- ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ ይሰጣሉ፡፡

## መልመጃ አራት

በዚህ ክፍለ ጊዜ የቀረቡት ይዘቶች የመጀመሪያው ከምንባቡ ለወጡ ቃላት አውዳዊ ትርጉም መስጠት ነው፡፡ ሁለተኛው ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ መስጠት የሚል ነው፡፡ ከምንባቡ ለወጡ ቃላት አውዳዊ ትርጉም እንዲፈልጉ፣ከዚያም ለቀረቡ ቃላት ተቃራኒ ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡ከተማሪው ጋር በመሆን ለጥያቄዎቹ ግብረ መልስ ይሥጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ስምንት**

# ትምህርት አምስት፡ መጻፍ

**ተማሪዎችይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-**

- በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ ክብደት መጠናቸው እያደጉ የሚሄዱ ጽሁፎችን ይፈጥራሉ፡፡
- ፈሊጣዊ አነጋገሮችን በጽሁፍ ውስጥ ይጠቀማሉ፡፡

## ተግባር አንድ

የዕለቱ ትምህርት በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ ጽሁፍ መጻፍ የሚል ነው፡፡ የመጀመሪያው በአካባቢያቸው የሚተገበሩ የህጻናት መብቶችን መጻፍ ነው፡፡ ሁለተኛ የምንባቡን አንቀጾች ዝርዝር ሀሳቦች በቅደምተከተል መጻፍ ነው፡፡ ከዚያም የጻፉትን የአንቀጾችን ዝርዝር ሀሳቦች ተጠቅመው አንድ አንቀጽ እንዲጽፉ ያድርጓቸው፡፡ከዚያም የጻፉትን ተቀብለው ይመልከቱ፡፡ያበረታቷቸውም በመጨረሻም ስለፈሊጣዊ አነጋገሮች አጠር ያለ ማብራሪያ ያድርጉና ተማሪዎች የሚያውቋትን ፈሊጣዊ ንግግሮች ከዘረዘሩ በኋላ ፍቺያቸውን እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡

ክፍለጊዜ ዘጠኝ

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

ተማሪዎችይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-

- አገልግሎታዊ አረፍተነገሮችን ያወዳድራሉ፡፡
- አገልግሎታዊ አረፍተነገሮችን ያወዳድራሉ ያነጻጽራሉ፡፡

## መልመጃ አምስት

የዕለቱ ትምህርት አገልግሎታዊ አረፍተነገሮችን ማወዳደርና ማነጻጸር ነው፡፡ በተማሪው የመማሪያ መጽሀፍ ላይ የቀረበውን ማስታወሻ መነሻ አድርገው ስለአገልግሎታዊ አረፍተነገሮች ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡ ከዚያም አገልግሎታዊ ዓረፍተነገሮችን በማወዳደርና በማነጻጸር ጽፈው እንዲያሳይዎ ያድርጉ፡፡ ተቀብለውም አስተያየት ይስጧቸው፡፡

## 4. ግምገማ

- ምንባቡን አዳምጠው ጭብጡን መለየታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ጠይቀው ያገኙትን ለክፍል ጓደኞቻቸው ማቅረባቸውን ይከታተሉ፡፡
- ለቃላት አውዳዊ ትርጉም መስጠታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ መስጠታቸውን ይመልከቱ፡፡
- በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ጽሁፍ መጻፍቸውን ይከታተሉ፡፡
- የምንባቡን መልዕክት በአንቀጽ መጻፋቸውን ይከታተሉ፡፡
- የፈሊጣዊ አነጋገሮችን ፍቺ መጻፍቸውን ይመልከቱ፡፤
- አገልግሎታዊ አረፍተነገሮችን ማወዳደራቸውንና ማነጻጸራቸውን ይመልከቱ፡

## 5.የተመረጡ መልመጃዎች መልስ

## ትምህርት አንድ

### መልመጃ አንድ

ሀ. በቃል የሚመለሱ የተለያዩ ጥያቄዎች

1. ጥበቃና እንክብካቤ የማይደረግላቸው ከሆነ፣ መብቶቻቸው የማይጠበቅ ከሆነ
2. ለጉልበት ብዝበዛ፣ ህይወታቸውን ማጣት ሌሎቹን በዚሁ መሰረት ያሰሯቸው፡፡

ለ. የምርጫ ጥያቄዎች

1. መ
2. ለ
3. ሀ
4. ሐ
5. መ

ሐ. የተጓደሉትን ቃላት ማሟላት

1. ይጠቃሉ
2. መበልጸግ
3. ዕውቀት
4. የመጠበቅ
5. የሚጎዱ

# ትምህርት ሦስት

## መልመጃ ሁለት

ሀ. የተለያዩ መልሶች

1. ተጨማሪ
2. ከመራብ

ሌሎቹን በዚሁ መሰረት ያሰሯቸው፡፡

ለ. አዛምድ

1. ለ
2. ሀ
3. ሀ
4. መ
5. ሠ

ሐ. የምርጫ ጥያቄዎች

1. ሀ
2. መ
3. ለ

4. መ
5. ለ

# ትምህርት አራት

ሀ. ለቃላት አውዳዊ ትርጉም መስጠት

1. ማለፍ
2. የመተዳደር
3. የሚቃወም
4. ለማስተካከል
5. ከጉስቅልና
6. ሚና

## መልመጃ አራት

ተቃራኒ ፍቺ መስጠት

1. መ
2. ሠ
3. ረ
4. በ
5. ሰ
6. ሸ
7. ቀ
8. ሀ
9. ለ
10. ሐ

# ምዕራፍ ስምንት

# ሰላም

(የክፍለጊዜ ብዛት 9)

## 1. የሚጠበቀው ውጤት

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ጽሁፍን አዳምጠውይተነትናሉ፡፡
- የሰላምን አስፈላጊነት ያብራራሉ፡፡
- የጽሁፉን ፍሬ ሀሳብ አንብበው ማጠቃለያ ይሰጣሉ፡፡
- በጽሁፍ ውስጥ ተገቢ ስርዓተ ነጥቦችን ይጠቀማሉ፡፡
- በጽሁፍ ውስጥ ተዘውታሪ ቃላትን ይጠቀማሉ፡፡
- ውስብስብ አረፍተነገሮችን ይጠቀማሉ፡፡

## 2. የትምህርት ይዘት

### 2.1 ማዳመጥ

- ሰላም በቤተሰብ ውስጥ እንዴት እንደሚፈጠር ማዳመጥ
- አጫጭር ማስታወሻ ለመያዝ ማዳመጥ
- ሰላም በቤተሰብ ውስጥ ያለውን ጥቅም ማዳመጥ
- ለቃላት አውዳዊ ትርጉም ለመስጠት ማዳመጥ

### 2.2 መናገር

- በቡድን የተወያዩትን በቃል ማቅረብ
- ‹‹ሰላም በቤተሰብ መካከል›› የሚለውን ምንባብ አዳምጦ ጭብጡን መናገር
- ጠይቀው ያገኙትን በቃል ማቅረብ

### 2.3 ማንበብ

- የስዕልንመልዕክት ለማግኘትማንበብ
- ‹‹የሰላም ዋጋ ስንት ነው?›› የሚለውን ምንባብ ማንበብ

- የየአንቀጾችን መልዕክት ለማግኘት ማንበብ

## 2.4 ቃላት

- የተዘውታሪ ቃላት አውዳዊ ትርጉም

## 2.5 መጻፍ

- ስለሰላም ማጠቃለያ መጻፍ
- ‹‹የሰላምን ዋጋ እንዴት ማወቅ ይቻላል›› በሚለው ርዕስ ላይ አንቀጽ መጻፍ
- ሰላምን እንዴት በቤተሰብ መካከል መፍጠር ይቻላል›› በሚለው ርዕስ ላይ ድርሰት መጻፍ
- ስርዓተ ነጥቦችን በጽሁፍ ውስጥ መጠቀም

## 2.6 ሰዋስው

- ውስብስብ አረፍተነገሮችን መመስረት
- ውስብስብ አረፍተነገሮችን መለየት

# 3. የማስተማሪያ ዘዴ

- የቀደመ ዕውቀታቸውን ተተቅመው ሰላም በቤተሰብ መካከል እንዴት እንደሚፈጠር እንዲናገሩ ማነሳሳት
- የምንባቡን ርዕስ ተመልክተው ምንባቡ ምን እንደሚያወሳ እንዲናገሩ ማበረታታት
- በመጀመሪያ ማዳመጥ ግምት እንዲሰጡ በሁለተኛው ማዳመጥ የሰጡትን ግምት እንዲያነጻጽሩ ማበረታታት
- ባዳመጡት መሰረት እንዲወያዩ ቀስቃሽ ጥያቄዎችን ማቅረብ
- የመጻፍና የማንበብ መልመጃዎችን መስጠት
- ችግርን የማቃለል ተግባር እንዲሰሩ ማድረግ
- ስዕልን ተመልክተው መልዕክቱን እንዲናገሩ ማበረታታት
- የምንባቡን ርዕስ ተመልክተው ምንባቡ ስለምን እንደሚያወሳ እንዲገምቱ ማነሳሳት

- ያነበቡትን የምንባብ አንቀጽ መነሻ አድርገው የተቀረው የምንባብ ክፍል ስለምን እንደሚያወሳ እንዲናገሩ ማበረታታት
- ለቃላት አውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ ማበረታታት
- የቀደመ እውቀታቸውን ተጠቅመው ስለሰላም ማጠቃለያ እንዲጽፉማበረታታት
- ሂደታዊ የጽህፈት ስልቶችን ተከትለው በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ አንቀጽና ድርሰት እንዲጽፉ ማበረታታት
- ውስብስብ አረፍተ ነገሮችን እንዲመሰርቱ ማበረታታት

ክፍለጊዜ አንድ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

### ተማሪዎችይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-

- አዳምጠው ምንባብን ይተነትናሉ፡፡

### ቅድመ ማዳመጥ

በትምህርት አንድ ስር በክፍለጊዜ አንድ የተማሪዎችን የማዳመጥ ፍላጎት የሚያነሳሱ ሶስት ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ በሶስቱ ጥያቄዎች ላይ ከተማሪዎች ጋር ከተነጋገሩ በኋላ ወደ ዋናው ትምህርት ይግቡ፡፡ በመጀመሪያ ‹‹ሰላም በቤተሰብ መካከል›› በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ የመጀመሪያዎቹን ሶስት አንቀጾች ያንብቡላቸው፡፡ ከዚያም ቆም ብለው በማዳመጥ ጊዜ የቀረቡ ጥያቄዎችን ያሰሯቸው፡፡ በመቀጠል የተቀረውን የምንባብ ክፍል ያንብቡላቸው፡፡

## ሰላም በቤተሰብ መካከል

ሰላም ፍጥረታት የሚሹት የሕይወት ዋስትና ነው። በቤተሰብ መካከል ሰላም ከጠፋ አብሮ መኖር አይቻልም። በጎረቤት መካከል ሰላም ከጠፋ፣ በሕዝቦች መካከል ሰላም ከጠፋ ማሕበራዊ ኑሮ አደጋ ውስጥ ይወድቃል። በሰላም ወጥቶ በሰላም መግባት አይቻልም። ርስ በእርስ ሰላማዊ ንግግር ወይም ሰላማዊ ውይይትን ማድረግ አይቻልም።

ሰላምን የተወሰነ ግለሰብ፣ የቤተሰብ ወይም የማሕበረሰብ ክፍል ብቻውን ሊያመጣ አይችልም። ሰላም በገንዘብ የሚገዛ፣ በሃብት የሚለወጥ አይደለም። ሰላም የሚገኘው

እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል እና የማሕበረሰብ ክፍል በአስተሳሰቡ፣ በንግግሩ እና በሥራው ትክክለኛነቱ የተረጋገጠለትን ተግባር ሲያከናውን ነው። ጥላቻን የሚቀሰቅስ ንግግር፣ በቀልን የሚመኝ ልብ፣ በሌሎች ላይ ጉዳትን የሚያስከትሉ ተግባራት ቅራኔን፣ አመጽን፣ ጦርነትን እና ጥፋትን እንጂ ሰላምን አያስከትሉም። በሰዎች መካከል ሰላምን ለማንገስ ከተፈለገ ከሁሉ አስቀድሞ ስብዕናቸው መከበር አለበት።

## የማዳመጥ ጊዜ

*መምህር ማንበብዎን ቆም አድርገው ተማሪዎች ቀደም ብለው ካዳመጡት ስለሰላም ምን እንደተረዱና የሰላም እጦት በፍጥረታት ላይ ምን አይነት ጉዳት እንዳለው ይጠይቁ፡፡ በመቀጠልም የተቀረውን የምንባብ ክፍል ያንብቡላቸው፤ ሲያነቡላቸውም አጫጭር ማስታወሻ እንዲይዙ ይዘዙ፡፡*

በቤተሰብ፣ በማሕበረሰብ፣ በአገር መካከል ሰላም በሚጠፋበት ጊዜ መንስኤውን መለየት ይገባል፡፡ ይህም ተወያይቶ ለተፈጠሩት ችግሮች መፍትሄን ለማፈላለግ መልካም መንገድን ይፈጥራል። ወላጆች የልጆቻቸውን መልካም ስነምግባር በማነጽ የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ ነው። ልጆቻቸውን መምከርና መገሰጽ ብቻ ሳይሆን መልካም ስነ ምግባርንም ማሳየት ይኖርባቸዋል።

የቤተሰብን፣ የአካባቢን እና የአገርን ሰላም የሚያውኩ በርካታ የሰላም እንቅፋቶች አሉ። በምንገኝበት የስልጣኔ ዘመን የብዙሃን መገናኛዎች መረጃን እና እውቀትን በማስተላለፍ በባሕል እድገት እና በትምህርት አገልግሎት ትልቅ አስተዋጽዖን በማበርከት ላይ ይገኛሉ። የመገናኛ ቴክኖሎጂ በዳበረ ቁጥር የአገልግሎት ቁጥርም ይጨምራል። የብዙሃን መገናኛዎች ሰላምን በማሳደግ ሰፊ እገዛ አላቸው።

## ድህረ ማዳመጥ

## መልመጃ አንድ

*‹‹ሰላም በቤተሰብ መካከል›› በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ሲያነቡላቸው ተማሪዎች ያዳመጡትን መሰረት አድርገው በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ በጥንድ ከተወያዩ በኋላ በጽሁፍ መልሱ የሚል ነው፡፡ መምህር እባክዎ ሁሉንም ጥያቄዎች ተማሪዎች ትክክለኛ መልስ ከበቂ ምክንያት ጋር እንዲመልሱ ያበረታቷቸው፡፡ በመቀጠልም ያዳመጡትን*

መሰረት አድርገው ለቀረቡት ቃላት አውዳዊ ትርጉም እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡በዚህ ጊዜም ለቃላቱ ትክክለኛ አውዳዊ ትርጉም እንዲሰጡ ቃላቱ የሚገኙበትን አረፍተነገር ከምንባቡ እየወሰዱ ያንብቡላቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ሁለት**

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

**ተማሪዎችይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-**

- የተደመጠውን ምንባብ መልእክት ይተነትናሉ፡፡
- የሰላምን አስፈላጊነት ያብራራሉ፡፡

## ተግባር አንድ

በዚህ ክፍለ ጊዜ በይዘትነት የሚቀርበው ትምህርት‹‹ሰላም በቤተሰብ መካከል›› በሚል ርዕስ የቀረበው ምንባብ ሲያነቡላቸው ተማሪዎች ያዳመጡትን መሰረት አድርገው በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ከተወያዩ በኋላ በቃል ማቅረብ የሚል ነው፡፡መምህር ተማሪዎቹ በቀረቡላቸው ጥያቄዎች ላይ በዛ ያሉ ደቂቃዎችን መድበው እንዲወያዩ ያመቻቹ፤ይከታተሏቸው፡፡ ከዚያም ውይይታቸውን ማጠናቀቃቸውን ካረጋገጡ በኋላ ሁሉንም ጥያቄዎች ተራ በተራ እየጠየቁ በቃላቸው እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡ በመቀጠልም በተግባር ሁለት ስር በቀረቡ ጥያቄዎች ላይ በቡድን እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ ከዚያም ተወያይተው ያገኙትን በቡድን ተወካያቸው አማከይነት እንዲያቀርቡ ያድርጉ፤ ሲያቀርቡም ያበረታቷቸው፡፡ ቀጥሎም በአካባቢያቸው ያሉ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቶችን ጠይቀው ያገኙትን ለክፍል ጓደኞቻቸው በቀጣይ ክፍለጊዜ እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

**ክፍለጊዜ ሶስት**

## ተግባር ሁለት

የዕለቱ ትምህርት በባለፈው ክፍለ ጊዜ የተሰጣቸውን ተግባር በቃል ማቅረብ ነው፡፡ ተግባሩም ሰላምን እንዴት ማምጣት እንደሚቻል የስነዜጋ መምህራቸውን ጠይቀው ወይም መጻህፍት አንብበው ያገኙት መረጃ ላይ በቡድን ከተወያዩ በኋላ የደረሱበትን ለክፍሉ ተማሪዎች ማቅረብ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ተማሪዎች ሰርተው የመጡ መሆናቸውን ካረጋገጡ በኋላ ሁሉም ቡድን በቡድን ተወካዩ አማካይነት ተራ በተራ በቃል እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው፡፡

ክፍለጊዜ አራት

# ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

ተማሪዎችይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-

- የጽሁፍን ዋና ሀሳብ አንብበው ያጠቃልላሉ፡፡

## ቅድመ ንባብ

በዚህ ክፍለጊዜ የቀረበው የትምህርት ይዘት ‹‹የሰላም ዋጋው ስንት ነው›› የሚለውን ምንባብ ማንበብ የሚል ነው፡፡ መምህር! እባክዎን ተማሪዎች በቀጥታ ወደ ንባብ ከመግባታቸው በፊት፡

- የቀረበውን ስዕል ተመልክተው ስዕሉ ምንመልዕክት እንደሚያስተላልፍ አብራሩ
- ርዕሱን ተመልክተው በምንባቡ ውስጥ ምን ምን ሀሳቦች ሊነሱ እንደሚችሉ ተናገሩ
- የሰላም ዋጋው ምን ያህል እንደሆነ ገምቱ

የሚሉትን የቅድመ ንባብ ተግባራትን ያሰሯቸው፡፡ከዚያም‹‹የሰላም ዋጋው ስንት ነው›› በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በትኩረት እንዲያነቡ ይዘዟቸው፡፡

## የንባብ ጊዜ

ተማሪዎች የምንባቡን የመጀመሪያ አንቀጽ አንብበው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ባነበቡት የምንባብ ክፍል ሰላም ለማህበረሰቡ ምንአይነት ጥቅም እንዳለው ተናገሩ
- በተቀረው የምንባቡ ክፍል ስለሰላም ምን ምን ሀሳቦች ሊነሱ እንደሚችሉ ገምቱ

የሚሉትን የንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን ያሰሯቸው፡፡ከዚያም የተቀረውን የምንባቡን አንቀጾች በትኩረት እንዲያነቡ ይዘዟቸው፡፡

ክፍለጊዜ አምስት

## ድህረ ንባብ

### መልመጃ ሁለት

የዕለቱ ትምህርት የመጀመሪያው ምንባቡን መሰረት አድርገው ለቀረቡት ጥያቄዎች በጽሁፍ መመለስ የሚል ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የምንባቡ አንቀጾች የሚያስተላልፉትን መልዕክት መለየት የሚል ነው፡፡ ሶስተኛው ምንባቡን መሰረት አድርገው የወጡ የምርጫ ጥያቄዎች የሚል ነው፡፡ ሁሉንም የመልመጃ ሁለት ጥያቄዎች ተማሪዎችን አንድ በአንድ እየጠየቁ እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡ግብረ መልስም ይስጧቸው፡፡ ቀጥሎም በተግባር ሶስት ስር በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ማስታወሻ እየያዙ በጥንድ እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ከዚያም የያዙትን ማስታወሻ ለክፍል ጓደኞቻቸው በንባብ እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

ክፍለጊዜ ስድስት

## ትምህርት አራት፡ ቃላት

ተማሪዎችይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-

- ለተዘውታሪ ቃላት አውዳዊ ፍቺ ይሰጣሉ፡፡
- ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ይሰጣሉ፡፡

### መልመጃ ሶስት

በዚህ ክፍለጊዜ የቀረበው ይዘት ለተዘውታሪ ቃላት አገባባዊ ፍቺ መስጠት የሚልነው፡፡ የዕለቱ ትምህርት ለቃላት አውዳዊና ተመሳሳይ ትርጉም መስጠት እንደሆነ በመግለጽ ከምንባቡ ለወጡ ተዘውታሪ ቃላት አውዳዊ ትርጉም እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡ከዚያም በሰንጠረዡ ውስጥ ከቀረቡት ቃላት ሰላምን የሚገልጹትን ለይተው እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡

ክፍለጊዜ ሰባት

## ትምህርት አምስት፡ መጻፍ

ተማሪዎችይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-

- የአንድን ጽሁፍ መልዕክት ማጠቃለያ ይጽፋሉ፡፡
- በጽሁፍ ውስጥ ተገቢ ስርዓተ ነጥቦችን ይጠቀማሉ፡፡

# ስለሰላም ማጠቃለያ መጻፍ

## ተግባርአራት

የዕለቱ ትምህርት ስለሰላም ማጠቃለያ መጻፍ የሚልነው፡፡ ‹‹ሰላም በቤተሰብ መካከል›› የሚለው ምንባብ ሲነበብላቸው የተረዱትንና ‹‹የሰላም ዋጋው ስንት ነው››የሚለውን ምንባብ ሲያነቡ ያገኙትን ሀሳቦች መነሻ አድርገው በመማሪያ መጻፋቸው ላይ የቀረቡትን ሶስት የመነሻ ሀሳቦች ተጠቅመው ድርሰት እንዲጽፉ ያመቻቹ፡፡

**ክፍለጊዜ ስምንት**

# ስርዓተ ነጥቦችን በጽሁፍ ውስጥ መጠቀም

## መልመጃ አራት

የዕለቱ ትምህርት ስለ ስርዓተ ነጥቦች እንደሆነ ገልጸው ቀጥሎ የቀረበውን ማስታወሻ መነሻ አድርገው ማብራሪያ ያድርጉላቸው፡፡ ማስታወሻውም፡

ስርዓተ ነጥቦች አረፍተ ነገሮች የተሟላ መልዕክት እንዲኖራቸው ያደርጋሉ፡፡ ስርዓተ ነጥቦች አረፍተነገርን በትክክል ለመጻፍ፣ ሀሳቦችን በቀረቡት ቃና፣ ክረት፣ ድምጸት ወዘተ ለመግለጽ ያገለግላሉ፡፡ በአማርኛ ቋንቋ በርካታ ስርዓተ ነጥቦች አሉ፡፡ ከነዚህም ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

**አራት ነጥብ** /፡፡/ በአረፍተ ነገር መጨረሻ ላይ የሚገባ ነው፡፡ይህም አረፍተነገርን ለመቋጨት ያገለግላል፡፡

ለምሳሌ፡ ዋቅቶላ ቤተሰቦቹጋ ሄደ፡፡

ጫልቱ ትላንትና ከፊንፊኔ መጣች፡፡

**ነጠላ ሰረዝ** /፣/ በአረፍተነገር ውስጥ በተከታታይ ለተመሳሳይ ተግባር የገቡትን ቃላት ለመለየት ያገለግላል፡፡

ለምሳሌ፡ እናቴ ሽንኩርት፣ ባቄላ፣ ቃሪያ፣ቲማቲምና በቆሎ እሸት ገዝታ መጣች፡፡

ጠዋት ፊቴን ታጥቤ፣ ቁርሴን በልቼ፣ ቦርሳዬን ይዜ ወደ ትምህርት ቤት እሄዳለሁ፡፡

ጥያቄ ምልክት/?/ ምላሽ የሚሻ ሀሳብ ያለው አረፍተነገር መጨረሻ ላይ የሚገባ ምልክት ነው፡፡

ለምሳሌ፡ አንተ መቼ ትመጣለህ?

አንቺ ጎበዝ ተማሪ ነሽ?

**ድርብ ሰረዝ** /፤/ ሙሉ መልዕክት ያላቸው አረፍተነገሮች ወይም በራሳቸው ባለቤትና ማሰሪያ አንቀጽ ያላቸው አረፍተነገሮች በአንድ አረፍተነገር ውስጥ ሲገኙ አረፍተነገሮቹ በድርብ ሰረዝ ይለያሉ፡፡

ለምሳሌ፡ ሜቲ ትመጣለች፤ ነገር ግን ልትቆይ ትችላለች፡፡

ሰዎች በሰርግ ዕለት ምግብ ይመገባሉ፤ዘፈን ይዘፍናሉ፤ እስክስታ ይወርዳሉ፡፡

**ቃለአጋኖ** /!/ አንድ ሀሳብ በመገረም፤ በመደነቅ፤ በመቆጣትና በመሳሰሉት ድምጸቶች ሲቀርብ እነዚህን ድምጸቶች ለማመልከት ቃለአጋኖን እንጠቀማለን፡፡

ለምሳሌ፡ ቤቱ በጣም ያምራል!

አንተ ለምን አልመጣህም!

ከዚያም በመልመጃ አምስት ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች እንዲሰሩ ይዘዟቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ዘጠኝ**

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

### ተማሪዎችይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡

- ውስብስብ አረፍተነገሮችንይመሰርታሉ፡፡

## መልመጃ አምስት

የዕለቱ ትምህርት ውስብስብ አረፍተ ነገሮችን መመስረት የሚል ነው፡፡ቀጥሎ የቀረበውን ማስታወሻ መነሻ አድርገው ስለውስብስብ አረፍተነገሮች ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡ **ማስታወሻውም፡**

ውስብስብ አረፍተነገር፡ በውስጡ ከአንድ መልዕክት በላይ ያለው አረፍተነገር ነው፡፡ ይህም ማለት ውስብስብ አረፍተነገር ከአንድ በላይ ግስ ወይም ማሰሪያ አንቀጽ ያለው አረፍተነገር ያለው ማለት ነው፡፡

ምሳሌ፡

ጋሩማ ትምህርት ቤት ሄዶ መጣ፡፡ ይህ አረፍተነገር ሁለት መልዕክት አለው፡፡አንደኛው ‹‹ጋሩማ ወደ ትምህርት ቤት ሄደ›› የሚል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ‹‹ጋሩማ ከትምህርት

ቤት መምጣቱን›› የሚገልጽ ነው፡፡ በተጨማሪም ይህ አረፍተነገር ‹‹ሄደ››ና ‹‹መጣ›› የሚሉ ሁለት ግሶች /ማሰሪያ አንቀጾች/ አሉት ማለት ነው፡፡

# 4. ግምገማ

- ምንባቡን አዳምጠው መተንተናቸውን ይከታተሉ፡፡
- በምንባቡ መሰረት ለተለያዩ ጥያቄዎች መልስ መስጠታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ጠይቀው/አንብበው ያገኙትን ለክፍልጓደኞቻቸው ማቅረባቸውንይከታተሉ፡፡
- ስዕሎችን ተመልክተው መልዕክታቸውን መለየታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- የተወያዩትን በቃል ማቅረባቸውን ይመልከቱ፡፡
- ለተዘውታሪ ቃላት ፍቺ መስጠታቸውንይመልከቱ፡፡
- በሰላም ላይ ጽሁፍ መጻፋቸውን ይከታተሉ፡፡
- አረፍተነገሮችን በስርዓት ነጥብ ማሟላታቸውን ይመልከቱ፡፧
- ውስብስብ አረፍተነገሮችንመመስረታቸውንይመልከቱ፡

# 5 የተመረጡ መልመጃዎች መልስ

## ምህርት አንድ

### መልመጃ አንድ

ሀ. የተለያዩ መልሶች

ለ. የቃላት አውዳዊ ትርጉም

1. የሚፈልጉት
2. ትግል
3. ተግባቢ
4. የሚያስቸግር
5. ከፍ ለማድረግ
6. ክብር
7. በመገንባት
8. የዋህነት
9. ርዳታ
10. ፍትሃዊ

## ትምህርት ሦስት

### መልመጃ ሁለት

ሀ. በጽሁፍ የሚመለሱ የተለያዩ ጥያቄዎች

1. ሰላም ፍቅር ነው፤ ሰላም መግባባት ነው...
2. ሰላም፣ ከሚረብሹ የተለያዩ ነገሮች መጠበቅ ሌሎችን በዚሁ መሰረት ያሰሯቸው፡፡

ለ. አዛምድ

1. ሐ
2. ሠ
3. መ
4. ለ
5. ሀ

ሐ. የምርጫ ጥያቄዎች

1. መ
2. ለ
3. መ
4. ሐ

## ትምህርት አራት

### መልመጃ ሶስት

**ሀ. ለተዘውታሪ ቃላት አውዳዊ ትርጉም መስጠት**

1. በጋራ
2. የሚሰሩ
3. መበላሸት
4. ተስፋፍተው

## ትምህርት አምስት

### መልመጃ አራት

ሀ. ስርአተ ነጥቦችን ማሟላት

1. መስከረም ወንዞች የሚቀንሱበት፣ አበቦች የሚፈኩበት፣ መስኩ የሚለመልምበትና ትምህርት ቤቶች የሚከፈቱበት ወር ነው
2. ሞቱማ እግር ኳስ መጫወት፣ መጽሀፍ ማንበብ፣ በእግር መንዝና መዝናናት ይወዳል፡፡
3. ወደ ፊንፊኔ የሄዱት መቼ ነው?
4. ለምን ትቀመጣለህ? ለምን አትሰራም? አትነሳም፡፡

5. ሂድና ዳቦ፣ ሽንኩርት፣ ቃሪያና ጎመን ገዝተህ ና፡፡

ለ. እናቴ ታታሪ ነጋዴ ነች፡፡ ሁልጊዜ በአካባቢችን የሚገኙ የከተማ ወረዳ ገበያዎች ላይ እየተዘዋወረች ትነግዳለች፡፡ ከዚያ ስትመለስ ደግሞ እኛን ትጎበኘንና ወደ ሱቋ ትመለሳለች፡፡ ከምትነግዳቸው የዕቃ አይነቶች መካከል ጥቂቶቹ ጨርቃጨርቅ፣ የተዘጋጁ ልዩ ልዩ አልባሳት፣ ጫማዎችና የጸጉር ቅባቶች ዋነኞቹ ናቸው፡፡

## ትምህርት ስድስት

### መልመጃ አምስት

ሀ.1፣ 2፣ 5፣ 7፣ 8፣

# ምዕራፍ ዘጠኝ

# የአየር ንብረት

(የክፍለጊዜ ብዛት 9)

## 1. የሚጠበቀው ውጤት

**ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-**

- የጽሁፍን ሀሳብ በማዳመጥ ዋጋ ይሰጣሉ፡፡
- የአየር ንብረት ጽንሰሀሳብን ያብራራሉ፡፡
- የአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖን ይተነትናሉ፡፡
- ለተለያዩ አላማዎች ምንባብ ያነባሉ፡፡
- የምስሎችን ዝርዝር ማብራሪያዎች ይጽፋሉ፡፡
- ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላትን አገባባዊ ፍቺ ይጠቀማሉ፡፡
- ድርብ ድብልቅ አረፍተነገሮችን ይመሰርታሉ፡፤

## 2. የትምህርት ይዘት

### 2.1 ማዳመጥ

- የአየር ንብረት ለውጥምን ማለት እንደሆነ ማዳመጥ
- ምንባቡ ሲነበብ አጫጭር ማስታወሻ ለመያዝ ማዳመጥ
- የአየር ንብረት ለውጥ እንዴት መቀነስ እንደሚቻል ማዳመጥ
- የአየር ንብረት ለውጥ በሰው ልጆች ላይ የሚመጣውን ተጽዕኖ ማዳመጥ

### 2.2 መናገር

- በቡድን የተወያዩትን በቃል ማቅረብ
- ጠይቀው ያገኙትን በቃል ማቅረብ
- ምንባቡን ፍሬ ነገር በቃል ማቅረብ

### 2.3 ማንበብ

- የስዕልን መልዕክት ለማግኘት ማንበብ

- የአየር ንብረት ለውጥ የሚለውን ምንባብ ማንበብ
- የየአንቀጾችን መልዕክት ለማግኘት ማንበብ
- የቃላትን አውዳዊ ፍች ለማግኘት ማንበብ

## 2.4 ቃላት

- የቃላትን አውዳዊ ፍች መስጠት
- ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላት አገባባዊ ፍቺ መስጠት

## 2.5 መጻፍ

- ስዕል ተመልክቶ የስዕሉን መልዕክት በአንቀጽ መጻፍ
- ስለአየር ንብረት የሚያውቁትን፣ ከምንባቡ ያገኙትን አዳዲስ ሀሳቦች ተጠቅመው ማጠቃለያ መጻፍ

## 2.6 ሰዋስው

- ድርብ ድብልቅ አረፍተነገር መመስረት

# 3. የማስተማሪያ ዘዴ

- የአዳምጦ መረዳት ማስተማሪያ ስልቶችን ተግባራዊ ማድረግ
- ያዳመጡትን መሰረት አድርገው የተወያዩበትን እንዲናገሩ ማበረታታት
- መፍትሄ እንዲያመነጩ የሚያስችሉ ተግባራትን ሰጥቶ ማለማመድ
- ከክፍል ውጪ የሚሰሯቸውን የተለያዩ ተግባራት መስጠት
- የአንብቦ መረዳት ስልቶችን ተግባራዊ አድርገው ‹‹የአየር ብክለት›› የሚለውን ምንባብ እንዲያነቡ ማድረግ
- ማብራሪያ የሚፈልጉ ጥያቄዎችን አቅርቦ በማብራራት ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ማትጋት
- በአረፍተነገር ውስጥ ያሉ ቃላትን አውዳዊ ትርጉም እንዲሰጡ አቅጣጫ ማሳየት
- በቀረበላቸው ርእስ መነሻነት ሶስት አንቀጽ ያለው አመዛዛኝ ድርሰት ምሳሌ አቅርቦ እንዲጽፉ ማገዝ
- ስዕል ተመልክተው የስዕሉን ማጠቃለያ እንዲጽፉ ማድረግ
- ስለአገልግሎታዊ ዓረፍተነገሮች የሚያውቁትን እንዲናገሩ መቀስቀስ

ክፍለጊዜ አንድ

# ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

ተማሪዎችይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-

- የጽሁፍን ሀሳብ በማዳመጥ ዋጋ ይሰጣሉ፡፡
- በሚሰጣቸው ርዕሰጉዳይ ላይ ንግግር ያደርጋሉ፡፡

## ቅድመ ማዳመጥ

በትምህርት አንድ ስር በክፍለ ጊዜ አንድ የተማሪዎችን የማዳመጥ ፍላጎት የሚያነሳሱ ሁለት ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ሁለቱንም ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡ ከዚያም‹‹የአየር ንብረት ለውጥን መቀነስ›› በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ የመጀመሪያዎቹን ሶስት አንቀጾች ያንብቡላቸው፡፡ ከዚያም ቆም ብለው በማዳመጥ ጊዜ የቀረቡ ጥያቄዎችን ያሰሯቸው፡፡ በመቀጠል የተቀረውን የምንባብ ክፍል ያንብቡላቸው፡፡ ከዚያም የድህረ ንባብ ጥያቄዎችን ባዳመጡት መሰረት በቃላቸው እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡ በተጨማሪም በተግባር አንድ ስር የቀረቡትን በቡድን እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ በመጨረሻም የተወያዩትን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ያድርጉ፤ ሲያቀርቡም ያበረታቷቸው፡፡

# የአየር ንብረት ለውጥን መቀነስ

የአየር ንብረት ለውጥ፣ ምድራችንን እየተፈታተናት የመጣ የተፈጥሮ አደጋ ነው። ለውጡ የተፈጥሮ ሚዛንን በማዛባት፣ የምድራችንን የውኃ ትነት መጠን በከፍተኛ ደረጃ እንዲባባስ አድርጓል። በአየር ንብረት ለውጥ የአብዛኛዎቹ የውኃ አካላት መጠን ቀንሷል፤ አንዳንዶቹ የውኃ አካላትም ጠፍተዋል። ይህም በሰው ልጆች የዕለትተዕለት ግንኙነት ላይተፅዕኖ የሚፈጥር ጤናማ ያልሆነ የሙቀት መጨመር እንዲከሰት አድርጓል።

የአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭነትን ለመቀነስ በሚያስችሉ ተግባራት ላይ መሰማራት ተገቢ ይሆናል። ከተግባራቱም መካከል የደን ጭፍጨፋን መቀነስና የደን ሽፋንን መጨመር ዋነኞቹ ናቸው። የደን ጭፍጨፋን መቀነስ የአየር ንብረት ለውጥን

ለመከላከል ከፍተኛ ሚና አለው። ደኖች የካርቦን ጋዝን በግንዳቸውና በሥራቸው ይዘው በማስቀረት ልቀትን ይቆጣጠራሉ፤ አካባቢን ከብክለት ይታደጋሉ።

## የማዳመጥ ጊዜ

መምህር ማንበብዎን ቆም አድርገው ተማሪዎች ቀደም ብለው ካዳመጡት የአየር ንብረት ለውጥን እንዴት መቀነስ እንደሚቻል፣ የአየር ንብረት ለውጥ ተጸእኖው ምን እንደሆነ ይጠይቁ፡፡ በመቀጠልም የተቀረውን የምንባብ ክፍል ያንብቡላቸው፤ ሲያነቡላቸውም አጫጭር ማስታወሻ እንዲይዙ ያድርጉ፡፡

የደን ጭፍጨፋ፣ በዛፍ ግንዶችና ሥሮች ተይዞ የነበረውን ካርበን፣ ወደከባቢ አየር እንዲለቀቅ በማድረግ ከፍተኛ የካርበንዳይኦክሳይድ ክምችት ይፈጥራል። ጭፍጨፋው የደኖች መመናመንን ስለሚፈጥር አካባቢ ይራቆታል፤ ጎርፍ ይከሰታል፤ የላይኛው የአፈር ክፍል በጎርፍና በነፋስ እየተጠረገ ስለሚሄድ ምርት ይቀንሳል፤ ድርቅም ይከሰታል። ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ደኖችን ባለመጨፍጨፍ በየዓመቱ 4.8 ቢሊዮን ቶን የሚደርስ ካርበንዳይኦክሳይድ ይዘው እንዲያስቀሩ ማድረግ ይቻላል። ይህም በየዓመቱ ከሚቀጣጠለው ነዳጅ ጋር በተያያዘ ከሚኖር የካርበን ልቀት 18 በመቶ ያህል ይሆናል።

(የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር በአማራ ብ/ክ/መ/ ትምህርት ቢሮ ከተዘጋጀ አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ ከተማሪ መጽሐፍ 8ኛ ክፍል የተወሰደ)

## ድህረ ማዳመጥ

### መልመጃ አንድ

‹‹የአየር ንብረት ለውጥን መቀነስ›› በሚል ርዕስ የቀረበው ምንባብ ሲያነቡላቸው ተማሪዎች ያዳመጡትን መሰረት አድርገው የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ የሚል ነው፡፡ መምህር እባክዎ ሁሉንም ጥያቄዎች ተማሪዎች ትክክለኛ መልስ ከበቂ ምክንያት ጋር እንዲመልሱ ያበረታቱዋቸው፡፡ ግብረ መልስም ይስጧቸው፡፡ በመጨረሻም በትምህርት ሁለት በተግባር አንድ በ "ለ" ስር የቀረበውን ተግባር በክፍል ውስጥ እንዲሰሩ ይዘዟቸው፡፡ በመጨረሻም በተወካያቸው አማካኝነት እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

**ክፍለጊዜ ሁለት**

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

**ተማሪዎችይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-**

- በሚሰጣቸው ርዕሰጉዳይ ላይ ንግግር ያደርጋሉ፡፡
- የአየር ንብረት ጽንሰ ሀሳብን ያብራራሉ፡፡

## ተግባር ሁለት

በዚህ ክፍለ ጊዜ በይዘትነት የሚቀርበው ትምህርት አንደኛው ‹‹የአየር ንብረት ለውጥን መቀነስ›› በሚል ርዕስ ምንባብ ሲያነቡላቸው ተማሪዎች ያዳመጡትን መሰረት አድርገው በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ተወያይተው ለክፍል ተማሪዎች በቃል ማቅረብ ነው፡፡ መምህር ተማሪዎቹ በቀረቡላቸው ጥያቄዎች ላይ እንዲወያዩ ያመቻቹ፤ ይከታተሏቸው፡፡ ከዚያም ተወያይተው ያገኙትን ሀሳብ በቃላቸው እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡ ቀጥሎም "የአየር ንብረት ለውጥ በሀገራት ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያስከትላል" ለዚህ መንስኤው ማነው? የበለጸጉ ሀገራት ወይስ ታዳጊ ሀገራት? አንደኛውን ደግፈው ሌላውን በመቃወም ቡድን መስርተው እንዲከራከሩ ሁኔታዎችን ያመቻቹ፡፡ ክርክሩ ውስጥ ያልተሳተፉ ተማሪዎች ተከራካሪዎች ያቀረቡት ሀሳብ ምን ያህል ምክንያታዊ መሆን አለመሆኑን አስተያየት በመስጠት እንዲሳተፉ ያበረታቱ፡፡ በክርክሩ ወቅትም በምዕራፍ ሰባት ክፍል ጊዜ ሶስት ስር የተቀመጡትን የክርክር ማድረጊያ ነጥቦችን እንዲከተሉ ያድርጉ፡፡ ተግተው እንዲከራከሩም ያበረታቷቸው፡፡ ተግባር ሶስትንም እንዲከውኑ ያግዟቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ሦስት**

# ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

**ተማሪዎችይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-**

- ለተለያዩ አላማዎች ምንባብ ያነባሉ፡፡

## ቅድመ ንባብ

በዚህ ክፍለጊዜ የቀረበው የትምህርት ይዘት ‹‹የአየር ብክለት›› የሚለውን ምንባብ ማንበብ የሚል ነው፡፡ መምህር! እባክዎን ተማሪዎች በቀጥታ ወደ ንባብ ከመግባታቸው በፊት፡-

- የቀረበውን ስዕል ተመልክተው ስዕሉ ምን መልዕክት እንደሚያስተላልፍ አብራሩ
- ስለአየር ብክለት ምን ሰምታችሁ እንደምታውቁ ተናገሩ
- ርዕሱን ተመልክታችሁ በምንባቡ ውስጥ ምን ምን ሀሳቦች ሊነሱ እንደሚችሉ ተናገሩ፡፡

የሚሉትን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን ያሰሯቸው፡፡ ከዚያም ‹‹የአየር ብክለት›› በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በትኩረት እንዲያነቡ ይዘዟቸው፡

## የንባብ ጊዜ

ተማሪዎች የምንባቡን ሁለትአንቀጾች አንብበው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ከላይ የተመለከቱት ስዕል ምን መልዕክት እንዳለው ተናገሩ፤
- ባነበቡት ሁለት አንቀጾች ውስጥ ስለአየር ብክለት ምን እንደተረዳችሁ ግለጹ
- በተቀረው የምንባቡ ክፍል ስለአየር ብክለት ምን ምን ሀሳቦች ሊነሱ እንደሚችሉ ገምቱ
- ከታች የቀረበው ስዕል ምን መልዕክት እንዳለው ተናገሩ

የሚሉትን የንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን ያሰሯቸው፡፡ ከዚያም የተቀሩትየምንባቡ አንቀጾች በትኩረት እንዲያነቡ ይዘዟቸው፡፡

**ክፍለጊዜ አራት**

## ድህረ ንባብ

### መልመጃ ሁለት

የዕለቱ ትምህርት የመጀመሪያው ምንባቡን መሰረት አድርገው ለቀረቡት ጥያቄዎች በጽሁፍ መመለስ ነው፡፡ ሁለተኛው ምንባቡን መሰረት አድርገው የወጡ የምርጫ ጥያቄዎች መመለስ ነው፡፡ ሁሉንም የመልመጃ ሁለት ጥያቄዎች ተማሪዎችን አንድ በአንድ እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡ ከዚያም በተግባር አንድ ስር በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ በጥንድ እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ ማስታወሻም በአስተዋጽኦ መልክ እንዲይዙ ይንገሯቸው፡፡ ቀጥሎም የያዙትን ማስታወሻ በቃል እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

ክፍለጊዜ አምስት

# ትምህርት አራት፡ ቃላት

**ተማሪዎችይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-**

- ለቃላት አውዳዊ ፍቺ ይሰጣሉ፡፡
- ለቃላት ተመሳሳይ ትርጉም መስጠት
- ለተዘውታሪ ቃላትአገባባዊ ፍቺ ይሰጣሉ፡፡

## ለተዘውታሪ ቃላት አገባባዊ ፍቺ መስጠት

**መልመጃ ሰስት**

በዚህ ክፍለ ጊዜ የቀረበው ይዘት ለቃላት አውዳዊ ትርጉም መስጠት የሚል ነው፡፡ በመጀመሪያ የመጀመሪያውን ጥያቄ ይስሩላቸው፡፡ ከዚያም የተቀሩትን ጥያቄዎች ተማሪዎች በግላቸው ምንባቡን እያነበቡ እንዲሰሩ በቂ ጊዜ ይሰጧቸው፡፡ ከዚያም ጥያቄዎቹን ከተማሪዎች መልስ እየተቀበሉ ግብረ መልስ ይስጡ፡፡ቀጥሎም ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡ ግብረ መልስም ይስጧቸው፡፡

ክፍለጊዜ ስድስት

## ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላት አገባባዊ ፍቺ

የዕለቱ ትምህርት ተዘውታሪ ላልሆኑ ቃላት አገባባዊ ፍቺ መስጠት የሚል እንደሆነ ለተማሪዎች ከገለጹላቸው በኋላ ቀጥሎ የቀረበውን ማስታወሻ መነሻ አድርገው ማብራሪያ ያድርጉላቸው፡፡

**ማስታወሻ**

ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላት በንግግርም ሆነ በጽሁፍ ውስጥ አዘውትረን የማንጠቀማቸው ቃላት ናቸው፡፡ የነዚህን ቃላት ትርጉም ለመረዳትም ቃላቱ የሚገኙበትን አረፍተነገሮችና የተነገሩበትን አውድ መመልከትና መረዳት ይገባል፡፡

*ምሳሌ፡ የአየር ብክለትን ለመከላከል ታዳሽ የሀይል አማራጭን መጠቀም ግዴታ ነው፡፡*
*ጽዱ የኃይል ምንጮችን መጠቀም ያስፈልጋል፡፡*

ከላይ የተሰመረባቸው ቃላት ብዙ ጊዜ የማንጠቀማቸው ቃላት ናቸው፡፡ ስለዚህ እንዲህ አይነት ቃላት ትርጉማቸውን ለመለየት አገባባቸውን መመልከት አለብን፡፡በመቀጠል

በመልመጃ ሶስት ስር የቀረቡትን የመለማመጃ ጥያቄዎች እንዲሰሩ ይዘዟቸው፡፡ ከዚያም መልሶቻቸውን እየተቀበሉ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ሰባት**

## ትምህርት አምስት፡ መጻፍ

**ተማሪዎችይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-**

- የምስሎችን ዝርዝር ማብራሪያዎች ይጽፋሉ፡፡

## ስለአየር ብክለት ማጠቃለያ መጻፍ

### ተግባር አንድ

የዕለቱ ትምህርት ስዕልን ተመልክቶ የስዕሉን መልዕክት በአንቀጽ መጻፍና ስለአየር ብክለት ማጠቃለያ መጻፍ የሚል ነው፡፡ መምህር እባክዎ ተማሪዎች የቀረቡላቸውን ስዕሎች ተመልክተው የስዕሉን መልዕክት በራሳቸው አገላለጽ እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፡፡ ቀጥሎም በአየር ብክለት ላይ ማጠቃለያ እንዲጽፉ ያመቻቹ፡፡ አስፈላጊ እገዛም ያድርጉላቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ስምንት**

## ማጠቃለያ አንቀጽ መጻፍ

መምህር የዕለቱ ትምህርት ስለ አየር ንብረት የሚያውቁትንና ያነበቡትን መነሻ አድርገው ማጠቃለያ አንቀጽ መጻፍ እንደሆነ ይግለጹላቸው፡፡ከዚያም ስለአየር ንብረት የሚያውቁትንና ያነበቡትን በአጭር በአጭር በደብተራቸው ላይ እንዲያሰፍሩ ያድርጉ፡፡ ከዚያም ያሰፈሯቸውን ሀሳቦች መነሻ አድርገው አንቀጽ አስፋፍተው እንዲያረቁ ያድርጉ፤በዚህ ጊዜም ይከታተሏቸው፤ዕገዛም ያቅርቡላቸው፡፡

**ክፍለጊዜ ዘጠኝ**

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-**

- ድርብ ድብልቅ አረፍተነገሮችን ይመሰርታሉ፡፡

## ድርብ ድብልቅ አረፍተነገሮችን መመስረት

### መልመጃ አራት

የዕለቱ ትምህርት ድርብ ድብልቅ አረፍተነገሮችን መመስረት የሚል ነው፡፡ ቀጥሎ የቀረበውን ማስታወሻ መነሻ አድርገው ስለድርብ ድብልቅ አረፍተነገሮች ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡

**ማስታወሻ**

ሁለት አረፍተነገሮችንና ከአንድ ወይም ከአንድ በላይ ጥገኛ ሀረጎችን በውስጡ ይዞ ይመሰረታል፡፡ አረፍተነገሮቹ የየራሳቸው ባለቤትና ማሰሪያ አንቀጽ አላቸው፡፡

ምሳሌ፡ ጃለኔ ምሳዋን በላች፡፡ ቡና አፈላች እና ከእናቷ ጋር ጠጥታ ተኛች፡፡

ይህ አረፍተነገር በውስጡ ሁለት ራሳቸውን የቻሉ ማለትም ባለቤትና ማሰሪያ አንቀጽ ካላቸው አረፍተነገሮች የተመሰረተ ነው፡፡

ከዚያም የቀረቡላቸውን የመልመጃ ጥያቄዎችን በደብተራቸው ላይ እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡ ከዚያም ከተማሪዎች ላይ መልስ እየተቀበሉ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡ያበረታቷቸው፡፡

## 4. ግምገማ

- ምንባቡን አዳምጠው መተንተናቸውን ይከታተሉ፡፡
- በምንባቡ መሰረት ለተለያዩ ጥያቄዎች መልስ መስጠታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ጠይቀው/አንብበው ያገኙትን ለክፍል ጓደኞቻቸው ማቅረባቸውን ይከታተሉ፡፡
- ስዕሎችን ተመልክተው መልዕክታቸውን መለየታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- የተወያዩትን በቃል ማቅረባቸውን ይመልከቱ፡፡
- ለተዘውታሪ ቃላት ፍቺ መስጠታቸውን ይመልከቱ፡፡
- በአየር ብክለት ላይ ጽሁፍ መጻፋቸውን ይከታተሉ፡፡
- ድርብ ድብልቅ አረፍተነገሮችን መመስረታቸውን ይመልከቱ፡

# 5.የተመረጡ መልመጃዎች መልስ

## ትምህርት አንድ

### መልመጃ አንድ

ሀ. በቃል የሚመለሱ የተለያዩ ጥያቄዎች

1. የግብርና ምርት መቀነስ፣ የጤና መታወክና የመሳሰሉት
2. ዛፎችን መትከል፣ የተቃጠለ አየር ወደ ከባቢ አየር ከመልቀቅ መታቀብ

   ሌሎችንም በዚሁ መሰረት ያሰሯቸው፡፡

## ትምህርት ሦስት

### መልመጃ ሁለት

ሀ. በጽሁፍ የሚመለሱ የተለያዩ ጥያቄዎች

1. ዛፎች መጨፍጨፍ፣ የኢንዱስትሪዎች ጭስና የመሳሰሉት
2. በታዳጊ ሀገር ውስጥ የሚገኙ ሴቶችን ህጻናት

   ሌሎችንም በዚሁ መሰረት ያሰሯቸው፡፡

ለ. የምርጫ ጥቄዎች

1. ሐ
2. ለ
3. ሐ
4. መ
5. መ

## ትምህርት አራት

### መልመጃ ሶስት

ሀ. ለቃላት አውዳዊ ትርጉም መስጠት

1. ከባድ ችግር
2. አስቸጋሪ
3. ትቶ
4. ለማስወገድ
5. ችግር
6. እንዲይዙ

7. ስራው

**ለ.ተመሳሳይ ትርጉም**

1. ሌላ
2. መከለል
3. አንከን
4. መፋለስ
5. መመረዝ
6. ምሳሌ
7. መያዝ
8. ቁልቁለት
9. ችግር
10. ከፍታ

**ሐ.ተዘውታሪ ላልሆኑ ቃላት ትርጉም መስጠት**

1. ሮጦ ሄደ
2. ቀንሰው
3. ነጠላ/ጋቢ
4. ባህሪው የሚመች
5. ይለምናል

# ምዕራፍ አስር

# ተውኔት

(የክፍለጊዜ ብዛት 12)

## 1. የሚጠበቀው ውጤት

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- የሚደመጠውን ምንባብ አዳምጠው ትንታኔ ይሰጣሉ፡፡
- የተውኔትን ጽንሰሀሳብ በተመለከተ ያብራራሉ፡፡
- የተውኔት አላባውያንን ይገልጻሉ፡፡
- በጽሁፍ ውስጥ የተለያዩ አያያዥ ቃላትንይጠቀማሉ፡፡
- ተመሳሳይ ቃለ ተውኔትን ይፈጥራሉ፡፡
- ሀሳባቸውን ለመግለጽ ዘይቤአዊ አገላለጾችን ይጠቀማሉ፡፡

## 2. የትምህርት ይዘት

### 2.1 ማዳመጥ

- ቃለ ተውኔቱን መሰረት አድርገው የወጡ ጥያቄዎችን ለመመለስ ማዳመጥ
- የቃለ ተውኔቱ ክፍል እንዴት እንደሚጠናቀቅ ማዳመጥ
- በቃለተውኔቱ ወስጥ ያሉትን ገጸ-ባህርያት ለመለየት ማዳመጥ
- የቃለ ተውኔቱን ታሪክ ለመለየት ማዳመጥ
- የቃላትን ትርጉም ለመለየት ማዳመጥ

### 2.2 መናገር

- ያዳመጡትን ተውኔት ታሪክ መተረክ
- ያነበቡትን ተውኔት ታሪክ በቃል ማቅረብ
- ያነበቡትን ቃለ ተውኔት ፍሬነገሩን መናገር
- የተውኔቱ ታሪክ መቼቱን መናገር
- የተውኔቱን ግጭት መንስኤውን መናገር

## 2.3 ማንበብ

- የስዕልን መልዕክት ለማግኘት ማንበብ
- ‹‹ተውኔት›› የሚለውን ምንባብ ማንበብ
- የቃላትን አውዳዊ ፍች ለማግኘት ማንበብ

## 2.4 ቃላት

- የቃላትን አውዳዊ ፍች
- የተውኔት ቃላት ፍቺ
- ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላት አገባባዊ ፍቺ
- የቃላት ተመሳሳይ ትርጉም
- ዘይቤአዊ አገላለጾች

## 2.5 መጻፍ

- ያዳመጡትን ቃለተውኔት ፍሬነገሩን መጻፍ
- አጭር ቃለ ተውኔት መጻፍ
- ተውኔት በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ጭብጡን መጻፍ
- የተውኔት አይነቶችን ምንነት መጻፍ

## 2.6 ሰዋስው

- አረፍተነገሮችን በተገቢ አያያዥ ቃላት ማያያዝ

# 3. የማስተማሪያ ዘዴ

- ቃለተውኔትን እንዲያዳምጡ ማድረግ
- የቃለተውኔትን ታሪክ እንዲተርኩ ማነሳሳት
- ያዳመጡትን ቃለተውኔት ፍሬነገር እንዲናገሩ ፍንጭ መስጠት
- ተመልክተው የሚያውቁትን ቃለተውኔትታሪክ እንዲናገሩ መቀስቀስ
- ያነበቡትን ቃለተውኔት ፍሬነገሩን እንዲናገሩ መጠየቅ
- ተማሪዎች ሚና ወክለው ቃለተውኔትን በጓደኞቻቸው ፊት እንዲያቀርቡ ማመቻቸት
- ምንባቡን እንዲያነቡ መቀስቀስ

- ስዕልን ተመልክተው መልዕክቱን እንዲናገሩ አቅጣጫ ማሳየት
- ያነበቡትን የምንባብ አንቀጽ መነሻ አድርገው የተቀረው የምንባብ ክፍል ስለምን እንደሚያወሳ እንዲገምቱ ዕድል መስጠት
- ለቃላት አውዳዊ ፍቺ  እንዲሰጡ መጠየቅ
- ለቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ማሠጠት
- ዘይቤአዊ አገላለጾችን ተጠቅመው አረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ ማድረግ
- አያያዥ ቃላትን ተጠቅመው አረፍተነገሮችን እንዲያያይዙ ማበረታታት

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

### ተማሪዎችይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-

- ምንባብን አዳምጠው ይተነትናሉ፡፡

ክፍለጊዜ አንድ

### ቅድመ ማዳመጥ

በትምህርት አንድ ስር በክፍለ ጊዜ አንድ የተማሪዎችን የማዳመጥ ፍላጎት የሚያነሳሱ ሁለት ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ተማሪዎች ስለጭውውት ምን እንደሚያውቁ ይጠይቋቸው፡፡ ቀረበውን ጭውውትየተወሰነውን ክፍል ያንብቡላቸው፡፡ሲያነቡላቸውም በትኩረት እንዲያዳምጡም ይንገሯቸው፡፡

## ጭውውት

(እናት ወ/ሮ ታሪኳ እርጅና የተጫጫናቸው ከመሆኑም በላይ አብዛኞቹ ጥርሶቻቸው ወልቀው ከቀሩት ጥቂት ጥርሶች መካካል የመንጋጋ ጥርሳቸውን አሟቸዋል፡፡ዛሬ የሆስፒታል ቀጠሮ አላቸው፡፡ ልጃቸው አስማማው ባለቤቱን ዓለምነሽን ወደ እናቱ ቤት ልኮ እሱ ሀኪም ቤት የሚወስዳቸውን መኪና ለማፈላለግ ወደኋላ ቀርቷል፡፡ ዓለምነሽ አማቷ ቤት በደረሰች ጊዜ ወ/ሮታሪኳፊት ለፊት ተቀምጠው ከጎረቤታቸውከአቶ ቀጄላ ጋር እየተጫወቱ ነበር፡፡

ዓለምነሽ- "ሰላም ለዚህ ቤት! እንደምን አደራችሁ?

አቶ ቀጄላ፡ "እግዚአብሔር ይመስገን እንዴት ሰነበትህ?"

ዓለምነሽ- "እማማ እንዴት ነዎት ዛሬ?" አለች ከአቶ ከጄላ ጋር የእጅ ሰላምታ ከተለዋወጠች በኋላ ወደ አማቷ ጠጋ ብለው፡፡

ወ/ሮ ታሪኳ-"በጎ ነኝ ልጄ! መቼም ከትናንትናው ዛሬ መለስ ብሎልኛል" ካሉ በኋላ ወዲያውኑ "አስማምዬን የት ጥለሽ መጣሽ?"ብለው ጠየቋት፡፡

ዓለምነሽ-"ከቤት አብረን ወጣንና 'አንቺ ቀድመሽ እማማን አዘጋጃት እኔ መኪና አፈላልጌ ልምጣ' ብሎኝ ነው የተለያየነው፤ አሁን ይመጣል፡፡"ካለች በኋላ፣ ፊታቸውን የተሸፋፈኑበትን ነጠላ ገልጣ ለማየት እመከረች፣"ኧረ ተመስገን ነው ዛሬማ እብጠቱንም ቀንሷል'ኮ" አለች፡፡

ወ/ሮ ታሪኳ-"እኔማ መቼም ሲይዘኝ "ኑሮ ኑሮከመሬት፣ ዞሮ ዞሮ ከቤት' ነውና መሞቴ ካልቀረ ለምን እድሜ ሰጥተህ ታሰቃየኛለህ? እያልኩ፣ ፈጣሪዬን አማረርኩት፡፡ የሱ ቸርነት አያልቅም፤አሁን ደግሞ ተንፈስ አደረገኝ፡፡"

## የማዳመጥ ሂደት

መምህር እባክዎ ተማሪዎች ማዳመጣቸውን ገታ አድርገው ቀደም ብለው ያዳመጡትን ቃለ ተውኔት መሰረት በማድረግ የተውኔቱ ተዋንያን እነማን እንደሆኑ፣የተቀረው የታሪኩ ክፍል እንዴት ሊጠናቀቅ እንደሚችል ይጠይቋቸው፡፡በመቀጠልም የተቀረውን የምንባብ ክፍል ያንብቡላቸው፤ ሲያነቡላቸውም ትኩረት እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡

አቶ ቀጄላ፡ "አይ እሜቴ! ለምን ሆደ ባሻ ይሆናሉ? በትንሽ በትልቁ ፈጣሪን ማማረር የለብዎትም 'እግዜር በትር ሲቆርጥ ቆላ አይወርድም' ሲባል አልሰሙም?

ወ/ሮ ቷሪኳ፡ "አይ ቀጄልዬ! በጊዜ በሰበሰበኝ ምንኛ ደግ ነበር? አየህ! የሰጠኝን በሽታ ሁሉ ሆዴን አስፍቼ ችዬው ነበር፡፡ አሁን ግን የማልችለውን እየሰጠኝ ነው፡፡ 'ልጅ ከጠረው ጥርስ የጠረው' ይባላልእኮ! እንዳሉ አስማማው ወደቤት ይገባል፡፡

አቶ አስማማው፡ "እንዴት አደራችሁ? ምነው ዓለሜ፣ እማማን አላዘጋጀሻትም እንዴ!?" ካለ በኋላ፣ መለስ ብሎ እማማ! ተሸሎሽ አደረ? አላቸው፡፡

ወ/ሮ ታሪኳ፡ "በጎ ነኝ ልጄ! ምንም አልል ፡፡ና እንግዲህ መኪናውን ካመጣህ ደገፍ አድርገኝና እንሂድ፡፡"

አቶ አስማማው፡"እሺ አይዞሽ እማማ ትድኛለሽ" እያለ ደግፎ ያነሳቸዋል፡፡"አይዝዎት! አይዝዎት! ይድናሉ" እያሉ አቶ ቀጄላና ኣለምነሽም እየደገፏቸው ይወጣሉ፡፡

ምንጭ፡ ከአማርኛ የተማሪ መጽሀፍ 9ኛ ክፍል 2004 ዓ.ም 1ኛ ዕትም ተሻሽሎና እንዲስማማ ተደርጎ የተወሰደ፡፡

## ድህረ ማዳመጥ

### መልመጃ አንድ

መልመጃ አንድ ‹‹ጭውውት›› በሚል ርዕስ የቀረበው ምንባብ ሲያነቡላችሁ ተማሪዎች ያዳመጡትን መሰረት አድርገው የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃላቸው መመለስና ከጭውውቱ ለወጡ ዐረፍተነገሮች አውዳዊ ፍቺ መስጠት የሚል ተግባር ነው፡፡ መምህር መልመጃ አንድን እባክዎ ምሳሌ ይስሩላቸውና የተቀሩትን ተማሪዎች ትክክለኛ መልስ ከነበቂ ምክንያታቸው ጋር እንዲመልሱ ያበረታቱዋቸው፡፡ተግባር አንድ ስር ለቀረቡት ዓረፍተነገሮች በቡድን በመሆን በዓረፍተነገሮቹ ፍቺ ላይ እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ ተወያይተው ያገኙትን ለክፍል ጓደኞቻቸው በቃል እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

**ክፍለጊዜ ሁለት**

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

**ተማሪዎችይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-**

- ቃለተውኔትን ይተርካሉ፡፡
- ቃለተውኔትን በማንበብ በሚና ጨዋታ ይሳተፋሉ፡፡
- የራሳቸውን ቃለተውኔት አዘጋጅተው ይተውናሉ፡፡

### ተግባር ሁለት

በዚህ ክፍል ጊዜ በይዘትነት የሚቀርበው ትምህርት ‹‹አልወዳትም እንጂ አልጠላትም›› በሚል ርዕስ የቀረበውን ቃለውኔት መምህራቸው ሲያነቡላቸው ተማሪዎች ያዳመጡትን የቃለተውኔት ታሪክ ለክፍል ጓደኞቻቸው መተረክ የሚል ነው፡፡መምህር ቅድሚያ የተወሰነውን የቃለተውኔቱን ታሪክ ይተርኩላቸውና የተቀረውን ተማሪዎቹ ተራ በተራ እየተነሱ የቃለተውኔቱን ታሪክ እንዲተርኩ ያድርጉ፤ ያበረታቷቸው፡፡ ቀጥሎ ከጭውውቱ በተወሰዱ ምሳሌያዊና ፈሊጣዊ ንግግሮቹም ፍቺ ላይ በቡድን እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ተወያይተው ያገኙትን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ ከዚያም የቀረቡትን ምሳሌያዊና ፈሊጣዊ አነጋገሮችን አጠቃቀም የሚያሳዩ አውዶችን በጥንድ ሆነው በመፍጠር ለክፍል ተማሪዎች በቃል እንዲያሰሙ ያድርጉ፡፡

ክፍለጊዜ ሶስት

## ተግባር ሶስት

ያዳመጡትን ጭውውት መሰረት አድርገው ወ/ሮ ታሪኳ ምን ይሆኑ ይሆን? የተቀረው የጭውውት ክፍል እንዴት የሚጠናቀቅ እንደሚመስላቸው? በቡድን ከተነጋገሩ በኋላ የደረሱበትን ለክፍል ተማሪዎች እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ ቀጥሎ በመማሪ መጻፋቸው ላይ በቀረቡት ርዕሶች መነሻ ከ3-5 ደቂቃ የሚረዝም አንድ ጭውውት እንዲጽፉ ያድርጋቸው፡፡ አስፈላጊውን ዕገዛም ያድርጉላቸው፡፡/በጭውውቱ ውስጥ ምሳሌዊና ፈሊጣዊ አነጋገሮችን መጠቀማቸውን እንዲያስተውሉ ይንገሯቸው/፡፡ የጻፉትን ጭውውት ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋርምእንዲለማመዱ ያበረታቷቸው፡፡ የተለማመዱትንምበክፍላቸው ተማሪዎች ፊት እንዲተውኑ ያድርጉ፡፡

ክፍለጊዜ አራት

## መልመጃ ሁለት

የዕለቱ ትምህርት በቤታቸው ወይም በቤተመጻህፍት አንብበው የመጡትን ቃለተውኔት መሰረት አድርገው የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃላቸው መመለስ የሚል ነው፡፡ በቅድሚያ ተማሪዎች ቃለ ተውኔት አንብበው መምጣታቸውን ይጠይቁና ያነበቡትን የቃለ ተውኔት ርዕስ ምን እንደሆነ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ከዚያም ስላነበቡት ቃለተውኔት በመማሪያ መጽሀፋቸው ላይ የቀረቡትን ጥያቄዎች መነሻ አድርገው ለጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያደርጉ፡፡ እነሱም ጓደኞቻቸው ሲነግሯቸው አዳምጠው የእነሱ ከጓደኞቻቸው የሚለይበትን እንዲነግሯቸው ያድርጉ፡፡በዚሁ መልክ ሁሉም ተማሪዎች እንዲሳተፉ በማድረግ ትምህርቱን ያስቀጥሉ፡፡

ክፍለጊዜ አምስት

# ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

### ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-

- የተውኔትን ጽንሰ ሀሳብ ያነባሉ፡፡

## ቅድመ ንባብ

በዚህ ክፍለጊዜ የቀረበው የትምህርት ይዘት ‹‹ተውኔት›› በሚል ርዕስ ምንባብ ማንበብ ሚል ነው፡፡ መምህር! እባክዎን ተማሪዎች በቀጥታ ወደ ንባብ ከመግባታቸው በፊት፡-

- ተውኔት ምን እንደሆነ
- ስዕሉንተመልክተው ስለተውኔት ምን ማለት እንደሚችሉ ይጠይቁ

ከዚያም ‹‹የተውኔት አላባውያን›› በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በትኩረት እንዲያነቡ ይዘዟቸው፡፡ ሲመልሱም ተውኔት በድርጊት የታጀበ፣ በመድረክ ላይ የሚቀርብ እያዝናና የሚስተምር፣ ተዋንያን ቃለተውኔትን በመድረክ ላይ የሚያቀርቡ ነው ብለው መመለሳቸውን ያረጋግጡ፡፡ ግብረ መልስም ይስጧቸው፡፡ተማሪዎች የቃለተውኔቱን የመጀመሪያውን ክፍል አንብበው ካጠናቀቁ በኋላ የንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን ያስሯቸው፡፡ በመጨረሻም ምንባቡን መሰረት አድርገው ለቀረቡት ጥያቄዎች አንድ በአንድ እየጠየቁ እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡በመቀጠልም በክፍለጊዜ ስድስት ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች በቤታቸው ሰርተው እንዲመጡ ይዘዟቸው፡፡

ክፍለጊዜ ስድስት

## መልመጃ ሶስት

የዕለቱ ትምህርት በባለፈው ክፍለጊዜ በቤታቸው የሰሯቸው ጥያቄዎች ነው፡፡ተማሪዎች በቤታቸው የሰሯቸውን ጥያቄዎች መልሶቻቸውን ይመልከቱ፡፡አስተያየትም ይስጧቸው፡ ፡በመጨረሻም ከተማሪው ጋር በመሆን ግብረ መልስ ይስጡ፡፡ከዚያም በተግባር አንድ ስር በቀረቡት ጥያቄዎች መነሻነት በቡድን እንዲወያዩ ያድርጉና የደረሱበትን ለክፍል ጓደኞቻቸው በቃል እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

ክፍለጊዜ ሰባት

# ትምህርት አራት፡ ቃላት

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-**

- ዘይቤያዊ አነጋገሮችን ይጠቀማሉ፡፡

## መልመጃ አራት

በዚህ ክፍል ጊዜ የሚቀርበውይዘትዘይቤያዊ አገላለጽ የሚልነው፡፡ስለዘይሜ የሚውቁትን እዲናገሩ ያበረታቱ፡፡ ምላሻቸውን ተቀብለው ከርእሱ ጋር በተገቢው መንገድ እንዲተዋወቁከዚህ ቀጥሎ የቀረበውን ማስታወሻ መነሻ አድርገው ሰፋ አድርገው በደረጃቸው ማብራሪያ ያድርጉላቸው፡፡

**ማስታወሻ**

ዘይቤያዊ አገላለጽ አንድን በንግግር ወይም በጽሁፍ የሚቀርብን ሀሳብ አድምቆና አግዝፎ ለማቅረብ ሲባል ቃላት ከተለምዷዊው ወይም ዘወትራዊው ከሆነው አጠቃቀማቸው ለየት ያለ አጠቃቀምን ስንከተል ነው፡፡ ይህም አንድ ሀሳብ ጉልቶና ደምቆ ሲቀርብ ተመልካቹም ሆነ ሰሚው በቀላሉ መረዳት እንዲችል ያግዘዋል፡፡

ምሳሌ- ደራርቱ ከተቀመጠችበት ኳስ ይመስል ነጥራ ተነሳች፡፡

ደሚቱ እንደ ህጻን አለቀሰች፡፡

ሰውዬው አሳማ ነው፡፡

የመጀመሪያው አረፍተ ነገር የደራርቱን አነሳስ ከኳስ አነጣጠር ጋር በማወዳደር ደራርቱ የተነሳችበትን ሁኔታ አጉልቶ ያሣያል፡፡ በሁለተኛው አረፍተነገር ነገር ደግሞ አለሚቱ ህጻን የሚያለቅሰውን ያህል አምርራ ማልቀሷን ያመለክታል፡፡ በሶስተኛው አረፍተነገር ደግሞ ሰውዬው ብዙ እንደሚበላ አድምቆ ያሳያል፡፡

ከዚያም የቀረበላቸውን ገለጻና ምሳሌ መሰረት አድርገው አምስት ዘይቤያዊ አገላለጾች እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡ ተቀብለውም አስተያት ይስጧቸው፡፡

ክፍለጊዜ ስምንት

**መልመጃ አምስት**

የዕለቱ ትምህርት የቀረቡትን ዘይቤዎች አይነታቸውን ለይቶ መጻፍና በለዩአቸው ዓረፍተነገር እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡ተቀብለውም አስተያየት ይስጡ፡፡

ክፍለጊዜ ዘጠኝ

## ትምህርት አምስት፡ መጻፍ

### ተማሪዎችይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-

- ያዳመጡትን ቃለተውኔት በራሳቸው አገላለጽ ይጽፋሉ፡፡
- የራሳቸውን ቃለተውኔት ይጽፋሉ፡፡
- ያነበቡትን ፍሬሀሳብ ይጽፋሉ፡፡

## ያዳመጡትን ጭውውት መልዕክት በራሳቸው አገላለጽ መጻፍ

### ተግበር አራት

የዕለቱ ትምህርት ያዳመጡትን ጭውውት ታሪክ በራሳቸው አገላለጽ በቅደም ተከተል መጻፍ የሚል ነው፡፡ ቅድሚያ በማዳመጥ ትምህርት ወቅት የቀረበላቸውን ጭውውት አንድ ጊዜ ያንብቡላቸው፡፡ ከዚያም ተማሪዎች በቡድን እንዲደራጁ ያድርጉ፡፡ ከዚያም ባዳመጡት የቃለተውኔቱ ታሪክ ላይ እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ከዚያም የተወያዩትን ሀሳብ መሰረት አድርገው በራሳቸው አገላለጽ አንቀጽ እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፡፡ የጻፉትን ይመልከቱላቸው፡፡ በመጨረሻም የራሳቸውን አንድ አጭር ቃለተውኔት በቤታቸው ጽፈው እንዲመጡ ይዘዟቸው፡፡

**ክፍለጊዜ አስር**

## አጭር ቃለ ተውኔት ጽፎ በመድረክ ላይ መከወን

### ተግባር አምስት

የዕለቱ ትምህርት ቤታቸው ጽፈው የመጡትን አጭር ታሪክ ከጓደኞቻቸው ጋር ተለማምደው በመድረክ ላይ ማቅረብ የሚል ነው፡፡ ስለዚህ መምህር! ጽፈው የመጡትን አጭር ቃለተውኔት ሚና ወክለው ለተወሰኑ ደቂቃዎች እንዲለማመዱ ያድርጉ፡፡ ከዚያም የተለማመዱትን ቃለተውኔት የተወሰኑ ተማሪዎችን በመምረጥ ተራ በተራ ተነስተው ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ያድርጉ፤ ያበረታቷቸው፡፡ተማሪዎችም እንዲያጨበጭቡላቸው ያድርጉ፡፡ በመጨረሻም ያነበቡትን ቃለተውኔት ደግመው በማንበብ ጭብጡን ጽፈው እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡አስተያየትም ይስጧቸው፡፡

**ክፍለጊዜ አስራ አንድ**

## ‹‹ተውኔት›› የሚለውን ምንባብ አንብቦ ፍሬነገሩን መጻፍ

### ተግባር ስድስት

የዕለቱ ትምህርት ‹‹ተውኔት›› የሚለውን ምንባብ አንብቦ ፍሬነገሩን መጻፍ የሚል ነው። ስለዚህ መምህር በቅድሚያ ተማሪዎች ምንባቡን ደግመው እንዲያነቡ ያድርጉ። ሲያነቡም የየአንቀጾቹን ፍሬ ሀሳቦች በአጭር በአጭሩ እንዲይዙ ያድርጉ፤ በዚህ ጊዜም ያግዟቸው፤ ይከታተሏቸው ከዚያም የያዟቸውን ፍሬ ሃሳቦች መሰረት አድርገው በራሳቸው አገላለጽ አንድ አንቀጽ ጽፈው ለእርስዎ እንዲያሳዩ ያድርጉ፤ በመጨረሻም

ለቀጣዩ ክፍለጊዜ ስለተውኔት አይነቶች ከቤተመጻህፍት አንብበው ወይም ባለሞያዎችን ጠይቀው እንዲመጡ የቤት ስራ ይሥጧቸው፡

ክፍለጊዜ አስራ ሁለት

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

ተማሪዎችይህንን ንዑስ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-

- የተለያዩ አያያዥ ቃላትን በጽሁፍ ውስጥ ይጠቀማሉ፡፡

### የተለያዩ አያያዥ ቃላትን በጽሁፍ ውስጥ መጠቀም

**መልመጃ ስድስት**

የዕለቱ ትምህርት የተለያዩ አያያዥ ቃላትን በጽሁፍ ውስጥ መጠቀም የሚል ነው፡፡ ስለአያያዥ ቃላት ምሳሌ አቅርበውላቸው ገለጻ ካደረጉላቸው በኋላ የቀረበውን መልመጃ በደብተራቸው ላይ እንዲሰሩ ይዘዟቸው፡፡ ከዚያም ከተማሪው ጋር በመሆንግብረ መልስ ይስጧቸው፡፡

## 4. ግምገማ

- ምንባቡን አዳምጠው መልዕክቱን መለየታቸውን ይከታተሉ፡፡
- በምንባቡ መሰረት ለተለያዩ ጥያቄዎች መልስ መስጠታቸውን ያረጋግጡ ጠይቀው/አንብበው ያገኙትን ለክፍል ጓደኞቻቸው ማቅረባቸውን ይከታተሉ ያዳመጡትን ቃለተውኔት መተረካቸውን ይከታተሉ፡፡
- የቃለተውኔት ፍሬነገርን መለየታቸውን ያረጋግጡ
- የተወያዩትን በቃል ማቅረባቸውን ይመልከቱ፡፡
- ለቃላት አውደዊና ተመሳሳይ ፍቺ መስጠታቸውን ይመልከቱ፡፡
- በዘይቤያዊ አገላለጾች አረፍተነገር መመስረታቸውን ይመልከቱ፡፡
- ቃለተውኔትን በራሳቸው አገላለጽ መጻፋቸውን ይከታተሉ፡፤
- የራሳቸውን ቃለተውኔት መጻፋቸውን ይመልከቱ፡፡
- የምንባቡን ፍሬ ሀሳብ በራሳቸው አገላለጽ መጻፋቸውን ይከታተሉ፡፡
- አያያዥ ቃላትን ተጠቅመው አረፍተነገሮችን ማያያዛቸውን ያረጋግጡ፡፡

# 5 የተመረጡ መልመጃዎች መልስ

## ትምህርት አንድ

### መልመጃ አንድ

**ሀ. በቃል የሚመለሱ ጥያቄዎች**

1. በነታሪኳ ቤት
2. የልጇ ሚስት
3. አቶ ቀጄላ

ሌሎቹንም በዚሁ መሰረት ያሰሯቸው፡፡

## ትምህርት ሦስት

### መልመጃ ሶስት

**ሀ. በጽሁፍ የሚመለሱ የተለያዩ ጥያቄዎች**

1. ጎበዝ
2. ተዋንያን
3. ሳር የሚግጡ ከብቶች

ሌሎቹን በዚሁ መሰረት ያሰሯቸው፡፡

**ለ. የምርጫ ጥያቄዎች**

1. ለ
2. ለ
3. ሀ
4. ሐ
5. ለ
6. ሐ

## ትምህርት አራት

### መልመጃ አራት

**ሀ. ለቃላት ከምንባቡ ፍቺ መፈለግ**

1. ተረዳድተው

2. መታገስ
3. መከራከር
4. መደናቀፍ
5. ተኅሳቅላ
6. አልሻም
7. ሳይቆዩ
8. ጠበቅ አድርጌ
9. መርዳት
10. ስቃይ

**ለ. ለቃላትና ሀረጋት አውዳዊ ፍቺ መስጠት**

1. ጊዜ የማይሰጥ
2. የትዳር አጋሬን
3. አዝነው
4. ሰምቼ
5. ይቆማሉ

## መልመጃ አምስት

**አነጻጻሪ ዘይቤ፡** 2፣4፣7

**ለዋጭ ዘይቤ፡** 1፣5፣8

**ሰውና ዘይቤ፡** 3፣6

# ትምህርት ስድስት

## መልመጃ ስድስት

1. ነገር ግን
2. ደግሞ
3. እና
4. ስለዚህ
5. እንጂ
6. እና
7. ቢሆንም፣ ግን

# ዋቢ መጻህፍት

ማረው ዓለሙ፡፡(2005)፡፡በሳል ድርሰት ማስተማሪያ፤ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ

ባየ ይማም፡፡(2004)፡፡ አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው፤አልፋ ማተሚያ ቤት

ዘሪሁን አስፋው፡፡(1996)፡፡ የስነጽሁፍ መሰረታውያን፤ንግድ ማተሚያ ቤት

2000 ዓ.ም የታተመ ኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ፣አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ 8ተኛ ክፍል፤

ሰብአዊ መብት ትምህርት ማስፋፊያ ማሕበር፡፡(2000 ዓ.ም) የህጻናት መብቶችና ኃላፊነቶች ትምህርት ማጣቀሻ መጻህፍት/ታተመ/፣አዲስ አበባ

2000 ዓ.ም የታተመ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር፣ በአማራ ብ/ክ/መ/ ትምህርት ቢሮ፣ አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ የ8ኛ ክፍል የተማሪ መጽሀፍ

# አማርኛ እንደ አፍመፍቻ ቋንቋ የ8ኛ ክፍል መርሃ ትምህርት

## መግቢያ

በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ በትምህርት አሰጣጥ ፈጣንና መሻሻል በታየበት ሁኔታ እየሰራች ነው፡፡ ልዩ ትኩረት የተሰጠው "ጥራቱ የተጠበቀና እኩል ተደራሽነት ያለውን ትምህርት ለሁሉም ማዳረስ" ላይ ነው፡፡ ይኸውም ለ21ኛው ክፍለ ዘመን እድገት እንደመሳሪያ ሆኖ በብቃት ህብረተሰቡን ወደ ፊት የሚያራምድ ነው፡፡ ይህንን ግብ ለማሳካት ትምህርት ሚንስቴር የነበረውን ክፍተት ለመሙላት ምርምሮችን በማድረግ አዲስ ስርዓተ ትምህርትን ቀርጿል፡፡ በዚህም የአፍ መፍቻ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት መሳሪያዎቹ (የይዘት ፍሰት፣ አነስተኛ የመማር ብቃትና መርሀትምህርት) በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ስርአተ ትምህርት ማእቀፍ ውስጥ ተመስርተው እንዲዘጋጁ ተደርገዋል፡፡ እነዚህ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት መሳሪያዎች ዋና መነሻቸው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ልህቀትን ለማሻሻል ሲሆን በአውድ የተደገፈ፣ በህጻናት እድገት ላይ በተደረገው የምርምር ማስረጃና በመማር ላይ የተመሰረተ ትምህርታዊ ስኬታማነትን እንዲያረጋግጡ ተደርገው ተቀርፀዋል፡፡ በአውዱ የተሰጡት መነሻ ልምምዶችም የተማሪውን መማር የመጨረሻ ግብ የሚያሳድጉ ናቸው ተብሎ ይታሰባል፡፡ የስርዓተ ትምህርት መሳሪዎች በዋናነት እንዲቀረፁ የተደረጉት የመማር ውጤት፣ ብቃት፣ ይዘት፣ የመማር ስልቶች፣ ምዘናና ለእያንዳንዱ ይዘት ጊዜ በመስጠት ነው፡፡

መርሃ ትምህርቱ የተለያዩ አገር በቀል እውቀቶችን፣ ዋና ዋና ክሂሎችን፣ ለህይወት አስፈላጊ የሆኑትንና ብርቱ ብሄራዊ ጉዳዮችንና ብቃቶችን ግምት ውስጥ በማስገባት ተዘጋጅቷል፡፡

ይህም በብሄራዊና በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ ብቁ ዜጋ ለማፍራት ታስቦ የተሰናዳ ነው፡፡ የይዘቱ ፍሰትም ከቀላል ወደ ውስብስብ፣ ከሚታወቅ ወደ ማይታወቅ፣ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የሚሄድ ሆኖ ተማሪዎቹ አውዳዊ ይዘቱን እንዲረዱ የሚያስችል ነው፡፡ መልመጃዎቹ ተማሪ ተኮር የሆኑ፣ አብዛኛውን እድል ለተማሪዎች የሚሰጡ፣ የታሰበውን የቋንቋ ክሂል ተለማምደው እንዲያሳድጉ የሚያስችሉ ሆነው በደረጃቸው የቀረቡ ናቸው፡፡

በዚሁ መሰረት የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ በክልሉ ለሚገኙ አፋቸውን በአማርኛ ቋንቋ ለፈቱ ተማሪዎች ይህን በትምህርት ሚኒስቴር የቀረበ ስርዓተ ትምህርት ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ አስማምቶ አቅርቦታል፡፡

**የአፍ መፍቻ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት ግቦችና አላማዎች**

**የአፍ መፍቻ ቋንቋ የማስተማር ግቦች ፡-**

- ከቅድመ አንደኛ ደረጃ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ያለውን የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት በስኬታማነት ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎቹ ቀጥለው ያሉትን ግቦችና አላማዎች እንዲያሳኩ ይጠበቃል፡፡

**ግቦች**

- የመሰረታዊ ፊደላትን ክሂል ማበልጸግ የተማሪውን አእምሮታዊ፣ስሜታዊና ማህበራዊ ክሂሎችን ለማሳደግ አስተዋጽኦ ያደርጋል፤
- ተማሪዎችን የቋንቋ ክህሎትና ስነልሳናዊ እውቀት ማስተዋወቅ ለተግባቦት ብቃት ማዳበር ስለሚያግዛቸው ሀሳባቸውንና ስሜታችውን በተለያዩ አውዶች ውስጥ ለመግለጽ ይረዳቸዋል፤
- ተማሪዎቹን አገር በቀል እውቀትና እሴቶችን እንዲያውቁ ስለሚያደርጋቸው በተለያዩ ማህበራዊ አውዶች ውስጥ እንዲጠቀሙባቸው ያስችላቸዋል፡፡

**አላማዎች**

**የአፍ መፍቻ ቋንቋ ማስተማርና የመማር አበይት አላማዎች፡-**

- መሰረታዊ ትምህርትን በማዳበር ተማሪዎች ለወደፊት የትምህርት ግባቸው ዝግጁ እንዲሆኑ ጽናት ይሰጣቸዋል፤
- የቋንቋውን ዋና ዋና ክሂሎች መረዳት የተግባቦት ችሎታቸውን ለማሳደግ እና ሀሳባችውንና ስሜታቸውን ውጤት ባለው መንገድ ለመግለጽ ይረዳቸዋል፤
- የቋንቋውን ንዑሳን ክሂሎች ማወቅ የተግባቦት ችሎታቸውን ለማዳበር እንደሚረዳቸው እንዲገነዘቡ ያደርጋቸዋል፤
- ከሳይንሳዊ ምርምር የተገኙትን የቋንቋና የስነልሳን ባህሪያት እንዲረዱ ያደርጋቸዋል፤
- የቋንቋ አጠቃቀምን በትምህርት፣ በማህበራዊ ኑሮና በምጣኔ ሀብት ሁነቶች ውስጥ እንዲያዳብሩ ያስችላቸዋል፤
- የአገር በቀል ቋንቋ ስልቶችን በተለያዩ የቋንቋ ይዘቶች በማቅረብ እንዲያሳድጉ ይረዳቸዋል፡፡

**ራዕይና እሴቶች**

**ራዕይ**

የአፍ መፍቻ ቋንቋ መማርና ማስተማር ለአለም ቋንቋዎች ሁሉ ዋጋ ይሰጣል ተብሎ ስለሚጠበቅ እያንዳንዱ ሰው በተለይም ህጻናት ቋንቋውን መናገር ብቻ ሳይሆን መማር በመቻል ያንን ቋንቋ በቀላሉ ይረዳሉ፡፡ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በአፍ መፍቻ ቋንቋ ጠንካራ መሰረቶች የሚኖሩ ከሆነ ተማሪዎች በተሻለ መንገድ ስርዓተ ትምህርቱን እየተረዱ እንደዚሁም አዎንታዊ አመለካከት ኖሯቸው ወደ ትምህርት ቤት ይሄዳሉ፡፡ ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ከህጻንነታቸው ጀምሮ ጠበቅ አድርገው ማወቃቸው አስፈላጊ በመሆኑ በየክፍል ደረጃው የተሻለ ጥረት በማድረግ ለውጥ ማምጣት ይችላሉ፡፡

የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት የህጻናት አእምሮ ብስለትን በማሳደግ የቋንቋ ክሂሎችን፣ ማህበራዊና ባህላዊ እሴቶችንና ሌሎች ትምህርቶችን ለመማር ይረዳቸዋል፡፡ ይህን እሳቤ ውስጥ በማስገባት የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ተምረው ያለፉ ኢትዮጵያዊ ተማሪዎች በሰላምና በመተሳሰብ አብሮ በመኖር ፡-

- ብቃት ያለው የቋንቋ ክሂል ባለቤት፣ ባህልንና ማንነትን አክባሪ፣የማሰብና የመፍጠር ባለቤት፣ በራስ የሚተማመኑ፣ ችግር ፈቺዎች፣ ትጉኃን፣ ትኩረት ሰጪዎች፣ ምክንያታዊያን ተባባሪና ራስን በመስጠት የሚሰሩ ይሆናሉ፤

**እሴቶች**

እሴቶች አስፈላጊና ፍትሃዊ ስለሆኑ ነገሮች ያሉን እምነቶች ናቸው፡፡ እሴቶች ድርጊታችንንና ውሳኔያችንን ይመራሉ፤ ስለዚህ ይህ ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት የተዘጋጀው ጽሁፍ ተማሪዎቹ፡-

አገር በቀል እወቀቶችን አክባሪና ተጠቃሚ፣ የህብረተሰቡን የግጭት አፈታት ባህሎችን የሚተገብሩ፣ የስርዓተ ጾታ እኩልነትን ተግባራዊ የሚያደርጉ፣ የመረዳዳት መንፈስ ያላቸው፣ የመቻቻል ባህል የተላበሱ፣ ብሄራዊና አለማቀፋዊ ቅርስ የሚንከባከቡ፣ በልዩነት ውስጥ አንድነት የሚቀበሉ፣ እርስ በእርስ የሚከባበሩ፣ ጠንክሮ የመስራት ባህል ያላቸው፣ በላቀ ሁኔታ የሚያስቡ፣ የፈጠራ ችሎታን የተላበሱ፣ ችግር ፈቺዎች፣ ስለአካባቢ ጥበቃ የሚያስቡ እንዲሆኑ የሚያበረታታ መሆን አለበት፡፡

## የአንደኛ መንፈቀ አመት

**ምዕራፍ አንድ ፡ የሥራ ላይ ስነምግባር (9 ክፍለ ጊዜያት)**

የሚጠበቀው ውጤት- ይህንን ምዕራፍ ከተከታተሉ በኋላ ተማሪዎች፡-

- በጥሞና አዳምጠው ምላሽ ይሰጣሉ
- የሥራ ስነምግባር ምንነትን የተመለከተ ፅንሰ ሀሳብን ያብራራሉ
- አዳዲስ ሀሳቦችን በማሰስ አንቀፅ ይፅፋሉ
- የሥራ ስነምግባር ማሳያዎችን ያመላክታሉ
- የመጀመሪያ ቋንቋ ተገቢ መዋቅሮችን ይጠቀማሉ

| ብቃቶች | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶች እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች | ምዝና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎች፡-<br>• በተከታታይ ሁነቶች ውስጥ በጥልቀት አዳምጠው በተገቢው ሁኔታ ምላሽ ይሰጣሉ<br>• ቋንቋን በተለያዩ አውዶች ውስጥ ይጠቀማሉ<br>• የፅሁፉን አጠቃላይ ሀሳብ ለማግኘት በፀጥታ ያነባሉ<br>• አዳዲስ ሀሳቦችን በማካተት አንቀፅ ይፅፋሉ<br>• በተለያዩ አውዶች ውስጥ ተዘውታሪ ቃላትን ይጠቀማሉ | ማዳመጥና መናገር<br>ማንበብ<br>ቃላት<br>መፃፍ<br>ሰዋስው | **ቅድመ ማዳመጥ፡-**<br>ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት መቀስቀስ<br>*ለምሳሌ፡- የሥራ ስነምግባር ምንድን ነው?*<br>**የማዳመጥ ጊዜ፡-**<br>መምህር/ተማሪ አጭሩን ምንባብ ያነባሉ ተማሪዎች ምንባቡን አዳምጠው ማስታወሻ ይይዛሉ ምሳሌ፡- ጠንክሮ መስራት<br>**ድህረ ማዳመጥ፡-**<br>በተለያዩ ተከታታይ አውዶች ውስጥ በጥሞና ለማዳመጥና በተገቢው ሁኔታ ምላሽ ለመስጠት ተግባራትን መከወን ቋንቋን በመጠቀም በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ጉዳዮች ላይ /የሥራ ስነምግባር፣ ጠንክሮ የመስራት ባህል/ ውይይት ማድረግ<br>**ቅድመ ንባብ፡-**<br>ስለርዕሰ ጉዳዩ ተማሪዎችን ጥያቄ መጠየቅ<br>*ምሳሌ፡ ስለሥራ ስነምግባር ምን ታውቃላችሁ?*<br>**የንባብ ጊዜ፡-**<br>ዋናውን ሀሳብ ለማግኘት ተማሪዎች በዝምታ ማንበብ<br>መምህር በደረጃው ጥያቄ መጠየቅ<br>**ድህረ ምንባብ፡-**<br>በዋናው ሀሳብ ላይ አትኩረው ምንባቡን ካነበቡ በኋላ ተማሪዎቹ ተግባራቱን መስራት<br>አዳዲስ ሀሳቦችን በማሰስ አንቀፅ መፃፍ (በሥራ ስነምግባር ላይ)<br>ተዘውታሪ ቃላትን በተለያዩ አውዶች ውስጥ መጠቀም<br>በመፃፍ ተግባር ወቅት ተገቢ የመጀመሪያ ቋንቋ መዋቅሮችን መጠቀም | ከተደመጠው ነገር ተማሪዎችን ጥያቄ መጠየቅ<br>*ለምሳሌ፡- የሥራ ስነምግባር ማለት ምን ማለት ነው?*<br>ተማሪዎች ስለጠንክሮ መስራት የተወሰነ ነገር ተራ በተራ እንዲሉ መጠየቅ<br>የስራ ስነምግባርን በተመለከተ ተማሪዎች አጠቃላይ ሀሳቡን እንዲፅፉ መጠየቅ<br>ተማሪዎቹ አንድ ድርሰት እንዲፅፉ መጠየቅ<br>ተማሪዎች ተዘውታሪ ቃላትን እንዴት በተለያዩ አውዶች መጠቀም እንደሚቻል መጠየቅ |

**ምዕራፍ ሁለት፡ ባህላዊ ቅርስ (12 ክፍለ ጊዜያት)**

ከትምህርቱ የሚጠበቀው ውጤት፡ ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተከታተሉ በኋላ፡-

- የሌሎችን ሀሳብ በጥልቀት/በትኩረት ያዳምጣሉ
- የቃላትን ፍች ከምንባቡ በመነሳት ይረዳሉ
- የባህልንና ቅርስን ፅንሰ ሀሳብ ያብራራሉ

| ብቃቶች | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶች እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች | ምዝና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎች፡-<br>• የሌሎችን ሀሳብ በትኩረት አዳምጠው ምላሽ ይሰጣሉ<br>• ውስብስብ ሁነቶችን በቅደም ተከተል ይተርካሉ<br>• የአንድን ምስል/ስዕል ሀሳብ አንብበው ዘገባ ያቀርባሉ<br>• ሦስት አንቀፆች ያሉት አመዛዛኝ ድርሰት ይፅፋሉ<br>• በተለያዩ አውዶች ውስጥ አዳዲስ ቃላትን ይጠቀማሉ | *ማዳመጥና መናገር*<br><br>*ማንበብ*<br><br>*ቃላት*<br><br>*መፃፍ*<br><br>*ሰዋስው* | **ቅድመ ማዳመጥ፡-**<br>ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት መቀስቀስ<br>*ለምሳሌ፡- ባህላዊ ቅርስ ማለት ምን ማለት ነው?*<br>**የማዳመጥ ጊዜ፡-**<br>መምህር/ተማሪ አጭር ምንባብ ያነባሉ ተማሪዎች ምንባቡን አዳምጠው ማስታወሻ መያዝ *ምሳሌ፡- የሶፍዑመር ዋሻ*<br>**ድህረ ማዳመጥ፡-**<br>የሌሎችን ሀሳብ በጥልቀት ለማዳመጥ ተግባራትን መከወን<br>ውስብስብ ሁነቶችን በቅደም ተከተል ለመተረክ እንዲችሉ ማድረግ<br>**ቅድመ ንባብ፡**ስለርዕሰ ጉዳዩ ተማሪዎችን ጥያቄ መጠየቅ *ምሳሌ፡- ስለባህላዊ ቅርሶች ምን ታውቃላችሁ?*<br>**የንባብ ጊዜ፡**<br>ዋናውን ሀሳብ ለማግኘት ተማሪዎች በምንባብ ውስጥ ያለውን ስዕል ማበብ<br>መምህር በደረጃው ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>**ድህረ ምንባብ፡-**<br>ተማሪዎች ምንባቡን ካነበቡ በኋላ የቀረበውን ስዕል ሀሳብ አስመልክቶ ተግባራትን ማከናወን<br>( እዚህ ላይ ስዕል ያስፈልጋል) ሦስት አንቀፆች ያሉት አመዛዛኝ ድርሰት መፃፍ አዳዲስ ቃላትን በተለያዩ አውዶች ውስጥ መጠቀም | **ከተደመጠው**<br>ነገር ተማሪዎችን ጥያቄ መጠየቅ<br>*ምሳሌ፡- ባህላዊ ቅርስ ማለት ምን ማለት ነው?*<br>**ተማሪዎች**<br>ስለተወሰኑ ባህላዊ ቅርሶች እንዲናገሩ መጠየቅ<br>**ተማሪዎች**<br>የባህላዊ ቅርሶች ምስሎችን በተመለከተ ማጠቃለያ እንዲፅፉ መጠየቅ<br>ተማሪዎች የቅርስ ጥበቃን በተመለከተ አመዛዛኝ ድርሰት እንዲፅፉ መጠየቅ<br>ተዘውታሪ ቃላትን እንዴት በተለያዩ አውዶች መጠቀም እንደሚቻል መጠየቅ<br>በፅሑፍ ውስጥ የአሁን ጊዜን እንዲለዩ መጠየቅ |

**ምዕራፍ ሦስት፡- ሰብዓዊ እሴቶች (12 ክፍለ ጊዜያት)**

የሚጠበቁ ውጤቶች፡ ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-

- አዳምጠው ፅሑፉን ይገመግማሉ
- የሰብዓዊ እሴቶችን ፅንሰ ሀሳብ ያስረዳሉ
- ከሌሎች ጋር ምልልስ ያከናውናሉ
- የሰብዓዊ እሴቶች አላባዊያንን ይለያሉ
- አራት አንቀፆች ያሉት ገምጋሚ አንቀፅ ይፅፋሉ

| ብቃቶች | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶች እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎች፡-<br>• የተነበበውን ምንባብ አዳምጠው መልዕክቱን ይመዝናሉ<br>• ከሌሎች ጋር ምልልስ ያደርጋሉ<br>• የፅሑፉን ሀሳብ አንብበው ከራስ ያዋህዳሉ<br>• አራት አንቀፆች ያሉት ገምጋሚ ድርሰት ይፅፋሉ<br>• ሀሳባቸውን ለመግለጽ ጥምር ቃላትን ይጠቀማሉ<br>• ነጠላና የብዙ ቁጥር ቅርፆችን በአግባቡ ይጠቀማሉ | ማዳመጥና መናገር<br>ማንበብ<br>ቃላት<br>መፃፍ<br>ሰዋስው | **ቅድመ ማዳመጥ፡-**<br>ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት መቀስቀስ<br>*ለምሳሌ፡- ሰብዓዊ እሴት ማለት ምን ማለት ነው?*<br>**የማዳመጥ ጊዜ፡-**<br>መምህር/ተማሪ አጭር ምንባብ ያነባሉ<br>ተማሪዎች ምንባቡን አዳምጠው ማስታወሻ ይይዛሉ<br>*ምሳሌ፡- ክብር መስጠት*<br>**ድህረ ማዳመጥ፡-**<br>የሚደመጠውን ፅሑፍ ለማዳመጥና ለመመዘን ተግባራትን ማከናወን<br>ሰብዓዊ እሴቶችን በተመለከተ ከሌሎች ጋር ምልልስ ማድረግ<br>**ቅድመ ንባብ፡-**<br>ተማሪዎችን የምንባቡን ርዕስ አይተው የፅሑፉን መልዕክት እንዲገምቱ መጠየቅ<br>**የንባብ ጊዜ፡-**<br>የምንባቡን ዋና ሀሳብ ከራስ ለማዋሃድ ጽሑፉን ማንበብ<br>መምህር በደረጃው ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>**ድህረ ምንባብ፡-**<br>ተማሪዎች ምንባቡን ካነበቡ በኋላ መልዕክቱን ከራሳቸው ለማዋሃድ ተግባራትን መከወን (እዚህ ላይ የቃላት ድር ያስፈልጋል)<br>አዳዲስ ሀሳቦችን በማሰስ አንቀፅ መፃፍ (በሥራ ስነምግባር ላይ)<br>አራት አንቀፆች ያሉት ገምጋሚ ድርሰት ሰብዓዊ እሴቶችን በተመለከተ መፃፍ<br>ሀሳቦቻቸውን ለመግለፅ ጥምር ቃላትን መጠቀም<br>የቃላትን ነጠላና ብዙ ቁጥር ቅርፆች መጠቀም | ተማሪዎች፡-<br>ከተደመጠው የምንባብ ፅሑፍ ጥያቄ ይጠየቃሉ<br>*ምሳሌ፡- ዕሴት ማለት ምን ማለት ነው?*<br>የተወሰኑ ሰብዓዊ እሴቶችን እንዲገልፁ መጠየቅ<br>በተለያዩ አውዶች ውስጥ ያሉ አዳዲስ ቃላትን ለይተው እንዲያወጡ መጠየቅ<br>ቢያንስ ሦስት ሰብዓዊ እሴቶችን እንዲፅፉ መጠየቅ<br>ሀሳባቸውን በመግለፅ ወቅት ጥምር ቃላትን እንዲጠቀሙ መጠየቅ<br>የብዙ ቁጥር ቅርፆችን እንዲለዩ መጠየቅ |

**ምዕራፍ አራት፡አጭር ልቦለድ (18 ክፍለ ጊዜያት)**

የሚጠበቁ ውጤቶች፡ ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-

- አዳምጠው ተመሳሳይ ታሪኮችን ይናገራሉ
- የአጭር ልቦለድ ፅንሰሃሳብን ያብራራሉ
- በፅሑፋዊ ቅርፅ ውስጥ ልማዳዊ/ባህላዊ ቃላትን ይጠቀማሉ
- የአጭር ልቦለድ አላባዊያንን ያስረዳሉ

| **ብቃቶች** | **ይዘቶች** | **የመማር ብልሃቶች እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች** | **ምዘና** |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎች፡-<br>• አዳምጠው ተመሳሳይ ታሪኮችን ይናገራሉ<br>• እርስበርስ መመሪያዎችን ይሰጣጣሉ<br>• አንብበው አዳዲስ ዘይቤያዊ አገላለፆችን ይለያሉ<br>• በፅሁፍ ውስጥ መሸጋገሪያ ቃላትን ይጠቀማሉ<br>• ለተለያዩ አላማዎች ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላትን ይጠቀማሉ<br>• ሀረጋትን በአረፍተ ነገሮች ውስጥ ይጠቀማሉ | ማዳመጥና መናገር<br><br>ማንበብ<br><br>ቃላት<br><br>መፃፍ<br><br>ሰዋስው | **ቅድመ ማዳመጥ፡-**<br>ታሪክን በመንገር/በመተረክ የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት መቀስቀስ<br>**የማዳመጥ ጊዜ፡-**<br>መምህር/ተማሪ አጭሩን ምንባብ ያነባሉ ተማሪዎች ምንባቡን አዳምጠው ማስታወሻ ይይዛሉ<br>ምሳሌ፡- አጭር ልቦለድ<br>**ድህረ ማዳመጥ፡-**<br>ተመሳሳይ ታሪኮችን ለማዳመጥና ለመናገር ተግባራትን ማከናወን<br>እርስበርስ መመሪያ ለመሰጣጠት መለማመድ<br>**ቅድመ ንባብ፡-**<br>ተማሪዎችን አዳዲስ ዘይቤያዊ አገላለፆችን ለይተው እንዲወጡ መጠየቅ<br>**የንባብ ጊዜ፡-**<br>ተማሪዎች አዳዲስ ዘይቤያዊ አጠቃቀሞችን ለመለየት ምንባቡን ማንበብ<br>መምህር በደረጃው ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>**ድህረ ምንባብ፡-**<br>ተማሪዎች አዳዲስ ዘይቤያዊ አገላለፆችን ለይቶ ለማውጣት ምንባቡን ካነበቡ በኋላ ተግባራትን መከወን (እዚህ ላይ መዝገበ ቃላት አስፈላጊ ነው)<br>በፅሑፍ ውስጥ መሸጋገሪያ ቃላት መጠቀምን መለማመድ<br>ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላትን ለተለያዩ አላማዎች መጠቀም<br>ሀረጋትን በመጠቀም አረፍተ ነገሮች መመስረት | ተማሪዎች፡-<br>ከተደመጠው የምንባብ ፅሑፍ ጥያቄ ይመየቃሉ<br>ምሳሌ፡- የአጭር ልቦለድ አላባዊን እነማን ናቸው?<br><br>የተወሰኑ የአጭር ልቦለድ አላባዊያንን እንዲያስረዱ መጠየቅ<br>አዳዲስ ዘይቤያዊ አገላለፆችን ለይተውእንዲያወጡ መጠየቅ<br>መሸጋገሪያ ቃላትን እንዲፅፉ መጠየቅ<br>ለተለየ አላማ ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላትን እንዲጠቀሙ መጠየቅ<br>በአረፍተ ነገር ውስጥ ሀረግን እንዲጠቀሙ መጠየቅ |

**ምዕራፍ አምስት፡ የህዝብ ብዛት (18 ክፍለ ጊዜያት)**

የሚጠበቁ ውጤቶች፡ ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተከታተሉ በኋላ፡-

- በንቃት በማዳመጥ የቀረበውን የተደመጠውን ፅሑፍ ይገመግማሉ
- የህዝብ ብዛት የሚለውን ፅንሰ ሀሳብ ያብራራሉ
- ተራኪ ድርሰት ይፅፋሉ
- የህዝብ ቁጥር በምጣኔ ሀብት እድገት ላይ ያለውን አንድምታ ይመረምራሉ

| **ብቃቶች** | **ይዘቶች** | **የመማር ብልሃቶች እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች** | **ምዝና** |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎች፡-<br>• በንቃት አዳምጠው ምንባቡን ይገመግማሉ<br>• ውስብስብ መረጃን ይጠይቃሉ<br>• በጥልቀት በማንበብ የመንስዔና ውጤት ግንኙነትን ከምንባቡ በመለየት ማብራሪያ ይሰጣሉ<br>• ተራኪ ድርሰትን ፅፈው ይገመግማሉ<br>• ፍላጎቶቻቸውን ለመግለፅ ፍካሬያዊ ቃላትን ይጠቀማሉ<br>• የገቢርና የተገብሮ ቃላትን በአረፍተ ነገሮች ውስጥ ይጠቀማሉ | ማዳመጥና መናገር<br>ማንበብ<br>ቃላት<br>መፃፍ<br>ሰዋስው | **ቅድመ ማዳመጥ፡-**<br>ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት መቀስቀስ<br>*ምሳሌ፡- የህዝብ ብዛት ማለት ምንድን ነው?*<br>**የማዳመጥ ጊዜ፡-**<br>መምህር/ተማሪ አጭር ምንባብ ያነባሉ ተማሪዎች ምንባቡን አዳምጠው ማስታወሻ ይይዛሉ *ምሳሌ፡- የውልደት ምጣኔ*<br>**ድህረ ማዳመጥ፡-**<br>የተደመጠውን ምንባብ መልዕክት ለመገምገም ተግባራትን ማከናወን ስለህዝብ ብዛት ያለ ፅንሰሀሳብ ላይ ውይይት በማድረግ ውስብስብ መረጃዎችን መጠየቅ<br>**ቅድመ ንባብ፡-**<br>ተማሪዎች አዳዲስ ሀሳቦችን እንዲያመነጩ መጠየቅ<br>*ምሳሌ፡- የመንስዔና ውጤት ግንኙነት*<br>**የንባብ ጊዜ፡-**<br>ተማሪዎች የመንስዔና ውጤት ግንኙነትን ከፅሑፉ ለይቶ ለማውጣት ማንበብ<br>መምህሩ በደረጃው ጥያቄዎችንመጠየቅ<br>**ድህረ ምንባብ፡-**<br>ተማሪዎች የመንስዔና ውጤት ግንኙነትን ከፅሑፉ ለይቶ ለማውጣት ምንባቡን ተከትለው የመጡ ተግባራትን መስራት (እዚህ ላይ ስዕል ያስፈልጋል)<br>ተራኪ ድርሰትን ለመፃፍና ለመገምገም መለማመድ<br>ስሜቶቻቸውን ለመግለፅ ፍካሬያዊ ቃላትን መጠቀም<br>ገቢርና የተገብሮ ግሶችን በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን መመስረት | ተማሪዎች፡-<br>ከተደመጠው ምንባብ ጥያቄ ይጠየቃሉ<br>*ምሳሌ፡- የውልደት ምጣኔ ማለት ምን ማለት ነው?*<br>ውስብስብ መረጃዎችን ከሌሎች እንዲለዩ ማድረግ<br>የመንስዔና ውጤት ግንኙነትን ለይተው እንዲያመለክቱ መጠየቅ<br>ተራኪ ድርሰትን እንዲፅፉና እንዲገመግሙ መጠየቅ<br>ስሜቶቻቸውን ለመግለፅ ፍካሬያዊ ቃላትን እንዲጠቀሙ መጠየቅ<br>ገቢርና የተገብሮ ግሶችን እንዲለዩ መጠየቅ |

# ሁለተኛው መንፈቀ አመት

**ምዕራፍ ስድስት፡ በረሃማነት (9 ክፍለ ጊዜያት)**

የሚጠበቁ ውጤቶች፡ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተካተተቱ ይዘቶችን ከተከታተሉ በኋላ ተማሪዎች፡-

- እያነበቡ ትንታኔ በመስጠት ፅሑፉን ይገመግማሉ።
- የበረሃማነትን ፅንሰ ሀሳብ ያብራራሉ።
- ምንባቡን አቀላጥፎ በማንበብ ማጠቃለያ ይሰጣሉ።
- በረሃማነት በአየር ንብረት ለውጥ ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት ይተነትናሉ።

| ብቃቶች | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶች እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎች፡-<br>• በንቃት አዳምጠው ምንባቡን ይገመግማሉ።<br>• በተሰጠው ርዕሰ ጉዳይ ላይ በራስ የመተማመን ስሜትን በተላበሰ መልኩ ንግግር ያደርጋሉ።<br>• የቀረበውን ምንባብ አቀላጥፎ በማንበብ ማጠቃለያ ይሰጣሉ።<br>• የገላጭ ድርሰትን መዋቅር ይገመግማሉ።<br>• ስሜቶቻቸውን ለመግለፅ ፍካሬያዊ ቃላትን ይጠቀማሉ።<br>• አገልግሎታዊ አረፍተ ነገሮችን ይፅፋሉ። | ማዳመጥና መናገር<br><br>ማንበብ<br><br>ቃላት<br><br>መፃፍ<br><br>ሰዋስው | **ቅድመ ማዳመጥ፡-**<br>ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት መቀስቀስ<br>*ምሳሌ፡- በረሃማነት ምንድን ነው?*<br>**የማዳመጥ ጊዜ፡-**<br>መምህር/ተማሪ አጭሩን ምንባብ ያነባሉ። ተማሪዎች ምንባቡን አዳምጠው ማስታወሻ መያዝ<br>*ምሳሌ፡ የአፈር መሸርሸር*<br>**ድህረ ማዳመጥ፡-**<br>የተደመጠውን ምንባብ መልዕክት ለመገምገም ተግባራትን ማከናወን<br>የበረሃማነትን ፅንሰሀሳብ በተመለከተ ውይይት ማድረግ በልበሙሉነት ስሜት መናገር<br>**ቅድመ ንባብ፡-**<br>ተማሪዎች የቀደመ እውቀታቸውን እየቀሰቀሱ እንዲጠቀሙ መጠየቅ<br>*ምሳሌ፡- ስለበረሃማነት ምን ታውቃላችሁ?*<br>**የንባብ ጊዜ፡-**<br>ተማሪዎች የተነበበውን ምንባብ ለማጠቃለል ፅሑፉን አቀላጥፈው ማንበብ<br>መምህሩ በደረጃው ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>**ድህረ ምንባብ፡-**<br>ተማሪዎች የተነበበውን ምንባብ ለማጠቃለል ተግባራቱን ማከናወን (እዚህ ላይ ስዕል ያስፈልጋል)<br>የገላጭ ድርሰት መዋቅርን ለመገምገም መለማመድ<br>ስሜቶቻቸውን ለመግለፅ ፍካሬያዊ ቃላትን መጠቀም<br>አገልግሎታዊ አረፍተ ነገሮችን መፃፍ መለማመድ | ተማሪዎች፡-<br>ከተደመጠው ምንባብ ጥያቄ ይጠየቃሉ።<br>*ምሳሌ፡- የአፈር መሸርሸር ምክንያቱ ምንድን ነው?*<br>በረሀማነት ስለሚያስከትላቸው የተወሰኑ ጉዳቶች እንዲገልፁ መጠየቅ<br>የመንስዔና ውጤት ግንኙነትን ለይተው እንዲያመለክቱ መጠየቅ<br>ስለበረሃማነት ማጠቃለያ እንዲፅፉ መጠየቅ<br>የተወሰኑ ነጥቦችን ስለበረሃማነት እንዲፅፉ ማድረግ<br>ገቢርና የተገብሮ ግሶችን እንዲለዩ መጠየቅ<br>ስሜቶቻቸውን ለመግለፅ ፍካሬያዊ ቃላትን እንዲጠቀሙ መጠየቅ<br>አገልግሎታዊ አረፍተ ነገሮችን እንዲፅፉ መጠየቅ |

**ምዕራፍ ሰባት፡ የህፃናት ጉልበት ብዝበዛ (9 ክፍለ ጊዜያት)**

የሚጠበቁ ውጤቶች፡ ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ትምህርት ተከታትለው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- *መረጃ ሰጭ ፅሑፍን በጥልቀት በማዳመጥ ተግባራዊ ያደርጋሉ*
- *የህፃናት ጉልበት ብዝበዛ ፅንሰሀሳብንና የሚያስከትለውን ተፅዕኖ ያብራራሉ*
- *በአንድ ጉዳይ ላይ ይደራደራሉ*
- *የአረፍተ ነገር አገልግሎቶችን ያወዳድራሉ፣ ያነጻፅራሉ*

| **ብቃቶች** | **ይዘቶች** | **የመማር ብልሃቶች እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች** | **ምዘና** |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎች፡-<br>• *መረጃ ሰጭ ፅሑፍን በጥልቀት በማዳመጥ ተግባራዊ ያደርጋሉ*<br>• በአንድ ጉዳይ ላይ ይደራደራሉ<br>• *ያልተለመዱ ፈሊጣዊ አነጋገር ገለፃዎችን ያነባሉ፣ ይጠቀማሉ*<br>• በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ የክብደት መጠናቸው እያደገ የሚሄዱ ፅሁፎችን ይፈጥራሉ<br>• *ቃላትን ከተቃራኒ ፍቻቸው ጋር ያዛምዳሉ*<br>• አገልግሎታዊ አረፍተ ነገሮችን ያወዳድራሉ፣ ያነጻፅራሉ | *ማዳመጥና መናገር*<br><br>*ማንበብ*<br><br>*ቃላት*<br><br>*መፃፍ*<br><br>ሰዋስው | **ቅድመ ማዳመጥ፡-**<br>ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት መቀስቀስ<br>*ምሳሌ፡- የህፃናት የጉልበት ብዝበዛ ማለት ምንድን ነው?*<br>**የማዳመጥ ጊዜ፡-**<br>መምህር/ተማሪ አጭሩን ምንባብ ያነባሉ<br>ተማሪዎች ምንባቡን አዳምጠው ማስታወሻ መያዝ<br>*ምሳሌ፡- የህፃናት መብቶች*<br>**ድህረ ማዳመጥ፡-**<br>የተደመጠውን ምንባብ መልዕክት ለመሄስ ተግባራትን ማከናወን<br>የህጻናት መብት ፅንሰሀሳብን በተመለከተ ውይይት ማድረግ፣ መደራደር<br>**ቅድመ ንባብ፡-**<br>ተማሪዎች የቀደመ እውቀታቸውን እየቀሰቀሱ እንዲጠቀሙ መጠየቅ<br>*ምሳሌ፡- ስለህጻናት ጉልበት ብዝበዛ ምን ታውቃላችሁ?*<br>**የንባብ ጊዜ፡-**<br>ተማሪዎች ምንባቡን በዝምታ ማንበብ<br>መምህሩ በደረጃው ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>**ድህረ ምንባብ፡-**<br>ተማሪዎች ያልተለመዱ ፈሊጣዊ ንግግሮችን ለመለየት ተግባራቱን መከወን (እዚህ ላይ የቃላት ድርና ስዕል ያስፈልጋል)<br>በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ የክብደት መጠኑ እየጨመረ የሚሄድ ፅሑፍ መፃፍ<br>ቃላትን ከተቃራኒ ፍቻቸው ጋር ማዛመድ<br>አገልግሎታዊ አረፍተ ነገሮችን ማወዳደርና ማነፃፀር | ተማሪዎች፡-<br>ከተደመጠው ምንባብ ጥያቄ ይጠየቃሉ<br>*ምሳሌ፡- የህፃናት ጉልበት ብዝበዛ መንስዔ ምንድን ነው?*<br>የተወሰኑ የህፃናት መብቶችን እንዲገልፁ መጠየቅ<br>ፈሊጣዊ አነጋገሮችን እንዲፅፉ መጠየቅ<br>ስለህፃናት መብት የተወሰኑ ነጥቦችን እንዲፅፉ መጠየቅ<br>ቃላትን ከተቃራኒ ፍቻቸው ጋር እንዲያዛምዱ መጠየቅ<br>የአገልግሎታዊ አረፍተ ነገሮችን ጥቅም እንዲፅፉ መጠየቅ |

**ምዕራፍ ስምንት፡- ሰላም (9 ክፍለ ጊዜያት)**

የሚጠበቁ ውጤቶች፡ ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ትምህርት ተከታትለው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ጽሑፍን አዳምጠው ይተነትናሉ
- የሰላምን አስፈላጊነት ያብራራሉ
- የፅሑፉን ዋና ሀሳብ አንብበው ማጠቃለያ ይሰጣሉ
- በፅሑፍ ውስጥ ተገቢ ስርዓተ ነጥቦችን ይጠቀማሉ

| ብቃቶች | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶች እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎች፡-<br>• አዳምጠው ምንባቡን ይተነትናሉ<br>• አድማጭን ለመርዳትና የሀሳብ ግልፅነትን ለመፍጠር መልሶ በማዋቀር ያብራራሉ<br>• የፅሑፉን ዋና ሀሳብ አንብበው ያጠቃልላሉ<br>• በፅሑፍ ውስጥ ተገቢ ስርዓተ ነጥቦች ይጠቀማሉ<br>• የተዘውታሪ ቃላትን አውዳዊ ፍች ይጠቀማሉ<br>• ውስብስብ አረፍተ ነገሮችን ይመሰርታሉ | ማዳመጥና መናገር<br><br>ማንበብ<br><br>ቃላት<br><br>መፃፍ<br><br>ሰዋስው | **ቅድመ ማዳመጥ፡-**<br>ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት መቀስቀስ<br>*ምሳሌ፡- ሰላም ምንድን ነው?*<br>**የማዳመጥ ጊዜ፡-**<br>መምህር/ተማሪ አጭር ምንባብ ያነባሉ ተማሪዎች ምንባቡን አዳምጠው ማስታወሻ መያዝ<br>*ምሳሌ፡- ሰላም ለእድገት የሚጫወተው ሚና*<br>**ድህረ ማዳመጥ፡-**<br>የተደመጠውን ምንባብ መልዕክት ለመተንተን ተግባራትን መከወን<br>አድማጭን ለመርዳት ሀሳቦችን መልሶ በማዋቀር ማብራራት<br>**ቅድመ ንባብ፡-**<br>ተማሪዎች የቀደመ እውቀታቸውን እየቀሰቀሱ እንዲጠቀሙ መጠየቅ<br>*ምሳሌ፡- ስለሰላም ምን ታውቃላችሁ?*<br>**የንባብ ጊዜ፡-**<br>ተማሪዎች ምንባቡን በዝምታ ማንበብ መምህሩ በደረጃው ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>**ድህረ ምንባብ፡-**<br>ተማሪዎች ዋናውን ሀሳብ ለማጠቃለል ተግባራቱን መከወን (እዚህ ላይ የስርተ ነጥብ ሰንጠረዥ ያስፈልጋል)<br>ለፅሑፍ ተገቢ የሆኑ ስርዓተ ነጥቦች መጠቀምን መለማመድ<br>የተዘውታሪ ቃላትን አገባባዊ ፍች መጠቀም<br>ውስብስብ አረፍተ ነገሮችን መመስረት | ተማሪዎች፡-<br>ከተደመጠው ምንባብ ጥያቄ ይጠየቃሉ<br>*ምሳሌ፡- ሰላም ለዕድገት ያለው ሚና ምንድን ነው?*<br><br>የተወሰኑ የሰላም ገፅታዎችን እንዲገልፁ መጠየቅ<br>ሰላምን አስመልክቶ ማጠቃለያ እንዲፅፉ መጠየቅ<br>ስለሰላም የተወሰኑ ነጥቦችን እንዲፅፉ መጠየቅ<br>የተዘውታሪ ቃላትን አገባባዊ ፍች እንዲያብራሩ መጠየቅ<br>የውስብስብ አረፍተ ነገር ክፍሎችን እንዲፅፉ መጠየቅ |

**ምዕራፍ ዘጠኝ፡- የአየር ንብረት (9 ክፍለ ጊዜያት)**

የሚጠበቁ ውጤቶች፡ ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተከታተሉ በኋላ፡-

- የፅሑፉን ሀሳብ በማዳመጥ ዋጋ ይሰጣሉ
- የአየር ንብረት ፅንሰ ሀሳብን ያብራራሉ
- ለተለያዩ አላማዎች ምንባብ ያነባሉ
- የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖን ይተነትናሉ

| ብቃቶች | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶች እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎች፡-<br>• የፅሑፉን ሀሳብ በማዳመጥ ዋጋ ይሰጣሉ<br>• በሚሰጣቸው ርዕሰ ጉዳይ ላይ በይፋ ድርድር ማድረግ ይችላሉ<br>• ለተለያዩ አላማዎች ምንባብ ያነባሉ<br>• የምስሎችን ዝርዝር ማብራሪያዎች ይፃፋሉ<br>• የአየር ንብረት ፅንሰ ሀሳብን ያብራራሉ<br>• ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላትን አገባባዊ ፍች ይጠቀማሉ<br>• ድርብ ድብልቅ አረፍተ ነገሮችን ይመሰርታሉ | ማዳመጥና መናገር<br><br>ማንበብ<br><br>ቃላት<br><br>መፃፍ<br><br>ሰዋስው | **ቅድመ ማዳመጥ፡-**<br>ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት መቀስቀስ<br>*ምሳሌ፡- የአየር ንብረት ምንድን ነው?*<br>**የማዳመጥ ጊዜ፡-**<br>መምህር/ተማሪ አጭር ምንባብ ያነባሉ ተማሪዎች ምንባቡን አዳምጠው ማስታወሻ ይይዛሉ<br>*ምሳሌ፡- የአየር ንብረት ለውጥ*<br>**ድህረ ማዳመጥ፡-**<br>የተደመጠውን ምንባብ መልዕክት ለመተንተን ተግባራትን መከወን በሚሰጥ ርዕሰ ጉዳይ ላይ በይፋ መወያየትና መደራደር/ በአየር ንብረት ለውጥ ላይ መከራከር<br>**ቅድመ ንባብ፡-**<br>ተማሪዎች የቀደመ እውቀታቸውን እየቀሰቀሱ እንዲጠቀሙ መጠየቅ<br>*ምሳሌ፡- ስለአየር ንብረት ለውጥ ምን ታውቃላችሁ?*<br>**የንባብ ጊዜ፡-**<br>ተማሪዎች ምንባቡን በዝምታ ማንበብ መምህሩ በደረጃው ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>**ድህረ ምንባብ፡-**<br>ተማሪዎች ምንባቡን ካነበቡ በኋላ የተለያዩተግባራትን መከወን (እዚህ ላይ ስዕል ያስፈልጋል)<br>የምስሎችን ዝርዝር ማብራሪያዎች መፃፍን መለማመድ<br>የተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላትን አገባባዊ ፍች መጠቀም<br>ድርብ ድብልቅ አረፍተ ነገሮችን መመስረት | ተማሪዎች፡-<br>ከተደመጠው ምንባብ /የአየር ንብረት ለውጥ/ ጥያቄ ይጠየቃሉ<br><br>የተወሰኑ የመፍትሄ ነጥቦችን እንዲገልፁ መጠየቅ /በደረጃቸው ለአየር ንብረት ለውጥ ችግሮች መፍትሄ ለመስጠት/ ስለአየር ንብረት ማጠቃለያ እንዲፅፉ መጠየቅ<br>ከስዕሉ በመነሳት ዝርዝር ነጥቦችን እንዲፅፉ መጠየቅ<br>ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላትን አገባባዊ ፍች መጠየቅ<br>የድርብ ድብልቅ አረፍተ ነገሮችን ፅንሰ ሀሳቦች መጠየቅ |

**ምዕራፍ አስር፡- ተውኔት** (12 ክፍለ ጊዜያት)

የሚጠበቁ ውጤቶች፡ ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተከታተሉ በኋላ፡-

- የሚደመጠውን ምንባብ አዳምጠው ትንታኔ ይሰጣሉ
- የተውኔትን ፅንሰ ሀሳብ በተመለከተ ያብራራሉ
- የተውኔትን አላባዊያን ይገልፃሉ
- በፅሑፍ ውስጥ የተለያዩ አያየገሮችን ይጠቀማሉ

| ብቃቶች | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶች እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች | ምዝና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎች፡<br>- ምንባብን አዳምጠው ይተነትናሉ<br><br>ቃለ ተውኔትን ይተርካሉ<br><br>ቃለ ተውኔቱን በማንበብ በሚና ጨዋታ ይሳተፋሉ<br><br>ተመሳሳይ ቃለ ተውኔትን ይፈጥራሉ<br><br>ሀሳባቸውን ለሌሎች ለመግለፅ ዘይቤያዊ አነጋገሮችን ይጠቀማሉ.<br>በምንባብ ውስጥ የተለያዩ አያያገሮችን ይጠቀማሉ | ማዳመጥና መናገር<br><br>ማንበብ<br><br>ቃላት<br><br>መፃፍ<br><br>ሰዋስው<br><br>ሰዋስው | **ቅድመ ማዳመጥ፡-**<br>ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት መቀስቀስ<br>*ምሳሌ፡- ተውኔት ምንድን ነው?*<br>**የማዳመጥ ጊዜ፡-**<br>*መምህር/ተማሪ አጭር ምንባብ ያነባተማሪዎች ምንባቡን አዳምጠው ማስታወሻ መያዝ ምሳሌ፡- አጭር ተውኔት*<br>**ድህረ ማዳመጥ፡-**<br>የተደመጠውን ምንባብ መልዕክት ለመተንተን ተግባራትን ማከናወን<br>የቃለ ተውኔቱን ክፍል መተረክ<br>**ቅድመ ንባብ፡-**<br>ተማሪዎች የቀደመ እውቀታቸውን እየቀሰቀሱ እንዲጠቀሙ መጠየቅ<br>*ምሳሌ፡- ስለተውኔት ምን ታውቃላችሁ?*<br>**የንባብ ጊዜ፡-ተማሪዎች**<br>ምንባቡን በዝምታ ማንበብ መምህሩ በደረጃውጥያቄዎችን መጠየቅ<br>**ድህረ ምንባብ፡-**<br>ተማሪዎች ምንባቡን ካነበቡ በኋላ በሚና ጨዋታ ውስጥ መሳተፍ (እዚህ ላይ የተለያዩ ቃለ ተውኔቶች ያስፈልጋሉ) ተመሳሳይ ቃለ ተውኔት መፃፍን መለማመድ ተውኔትን ከጓደኞቻቸው ጋር በመሆን ማብላላት<br>ሀሳባቸውን ለሌሎች ለመግለፅ ዘይቤያዊ አነጋገሮችን መጠቀም<br>የተለያዩ አያያዥ ቃላት በፅሑፍ ውስጥ መጠቀም | ተማሪዎች፡-<br>ከተደመጠው ምንባብ /የአየር ንብረት ለውጥ/ ጥያቄ ይጠየቃሉ<br>*ምሳሌ፡- የተውኔት አይነቶች እነማን ናቸው?*<br>ጥያቄዎችን መልሳሉ<br>የተወሰኑ የተውኔት ክፍሎችን እንዲተርኩ መጠየቅ<br>የተውኔት አይነቶችን እንዲዘረዝሩ መጠየቅ<br>ጭብጡን እንዲፅፉ መጠየቅ<br>ዘይቤያዊ አነጋገሮችን በመጠቀም ሀሳባቸውን ለሌሎች እንዲገልፁ መጠየቅ<br>ስለአያየገሮች መጠየቅ |